# የእግዚአብሔር መልእክት ለእግዚአብሔር ሰዎች

LAPSLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
1701 N. GREENVILLE AVE. ST. 810
RICHARDSON, TEXAS 75081, USA

# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| 1. የእግዚአብሔር መልእክት ለእግዚአብሔር ሰዎች | 1 |
| የትምህርት አሰጣጥ መንገድ | 2 |
| የአብርሃም መጠራት | 3 |
| ፲፪ቱ የያዕቆብ ልጆችና የዮሴፍ ታሪክ | 6 |
| በግብፅ የነበረው ጭቆና | 8 |
| ፋሲክና የሲና ኪዳን | 10 |
| 2. እስራኤልና አሕዛብ | 12 |
| የዓለም ሕዝብ | 13 |
| እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለምን እንደመረጠ | 18 |
| ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ | 20 |
| ሞዓባዊቱ ሩት | 23 |
| የዮናስ ትንቢት | 25 |
| የዛሬይቱ እስራኤል | 28 |
| 3. የድሮው እስራኤል መቅረት | 29 |
| በዓለ ሃምሳ (ጰንጠቆስጤ) | 32 |
| ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን | 33 |
| ወንጌል እንዴት እንደተሰራጨ | 35 |
| 4. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ | 35 |
| አለመግባባት የነበረው የጉባኤ ጊዜ | 37 |
| የማርቲን ሉተር መነሣት | 39 |
| በሮም የተደረገው ለውጥና ሄንሪ የእንግሊዝ ንጉሥ | 41 |
| 5. የዘመናችን የወንጌል አስተማሪዎች ማኅበር | 43 |
| የዳዊት ሊቪንግስቶን ወደ አፍሪቃ መምጣት | 44 |
| ሐድሰን ቴለርና ኤስ አይ ኤም | 47 |
| ኤስ አይ ኤም ከ፲፱፻፵ ዓ. ም. በፊት | 49 |
| 6. ኤስ አይ ኤም በኢትዮጵያ | 51 |
| ከጣላት ወረራ በፊት | 51 |
| በጣላት ዘመን | 53 |
| የኤስ አይ ኤም ሥራ በኢትዮጵያ | 55 |
| የኤስ አይ ኤም የሥራ አመራር ዘዴ | 58 |

# የእግዚአብሔር መልእክት ለእግዚአብሔር ሰዎች

## የተመረጡት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ፦

የአብርሃም መጠራት አሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች በግብፅ የደረሰባቸው ጭቆና ፋሲካና በሲና ተራራ የተሰጠ ቃል ኪዳን ።

## እስራኤልና አሕዛብ ፦

እግዚአብሔር እስራኤልን ለምን እንደ መረጠ ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዮናስ ትንቢትና የሩት መጽሐፍ ።

## የዛሬይቱ እስራኤል ፦

አሮጌው አልፎ አዲሱ ተጀመረ ፤ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የተፈጸመው ታላቅ ተግባር ።

## የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፦

የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት የቤተ ክርስቲያን መማክርት ዘመናት ሮምና የማርቲን ሉተር መነሣትና ሮም የእንግሊዝን ንጉሥ ሄንሪን እንደተቃወመች ።

## ዘመናዊው የወንጌል ሥራ ፦

ዳዊት ሊቪንግስቶን በአፍሪካ ሐድሰን ቴለር በቻይና የኤስ አይ ኤም መቋቋምና የኤስ አይ ኤም የወንጌል ሥራ በኢትዮጵያ ።

# የትምህርት አሰጣጥ መንገድ

<u>አንደኛ ተርም ፡—</u> በእግዚአብሔር ስለተመረጡት ሰዎች ።
እስራኤልና አሕዛብ ።
የዛሬይቱ እስራኤል ።

<u>ሁለተኛ ተርም ፡—</u> የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ።
የወንጌል አስተማሪዎች በየክፍለ ዓለማቱ መሠራጨት ።

<u>ሦስተኛ ተርም ፡—</u> የሚስዮናውያንና የቤተ ክርስቲያን ኅብረት ።
የሚስዮናውያን የሥራ አመራርና ያስተዳደር ዘዴ ።

<u>መነበብ ያለባቸው መጻሕፍት ።</u>

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በጭሩ
ስድስት ሚስዮናውያን በአፍሪቃ
ማርቲን ሉተር
አብርሃም
የእግዚአብሔር ሃሳብ ስለ ቤተ እስራኤል
የዓለም ታሪክ (ከክበደ ሚካኤል)

<u>ማስታወሻ</u>

በዚህ መጽሐፍ በተለይ እንድናጠና የታቀደው የቀድሞዎቹ እስራኤል የእግዚ አብሔርን ቃልና ሕጉን ለዓለም ሕዝብ ማዳረስ ሲገባቸው በለማመን ምክንያት ሳያዳርሱ መቅረታቸውን የሚያስረዳ ታሪካዊ ጉዞ ነው ። የድሮው እስራኤልና ዛሬ እስራኤላውያን ተብለው የሚጠሩት አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙት ለማሰማት ላልደረሰቸው የማዳረስ አደራ ተጥሎባቸዋል ።

የዛሬውን እስራኤል (የአማኞችን) እንቅስቃሴና እርምጃ ለንገምት የምንችለው ቤተ ክርስቲያን ባለፉት ዘመናት ያሳየችውን እድገት ስንመለከት ነው ። በየዘመናቱ በተነሱት አዳዲስ ትምህርተ ሃይማኖት ምክንያት ቤተ ክርስቲያን አርቶዶክስ ካቶሊክ እንግሊካንና ፕሮቴስታንት በመበል ስትከፋፈል ልዩ ልዩ የሆኑትም የሚስዮን ማኅበሮች ወደ መታወቅ መጥተዋል ።

በመጨረሻም የተለያዩ ሚስዮናውያን ትምህርተ ሃይማኖት መታወቅና ልዩ ልዩ ዓይነት የጸሎት ቤቶች የሃይማኖት ሥርዓቶች ሊታወቁ ችለዋል ።

# የብሉይ ኪዳን መሠረተ መነሻ

## እግዚአብሔር የመረጣቸው ሕዝቦች ።

## የአብርሃም መጠራት ።

የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ፡— ዘፍጥረት ፲፩ ፡ ፴፩ — ፲፪ ፡ ፱
ዘፍጥረት ፲፮ ፡ ፲፭ — ፲፯ ፡ ፰
ሮሜ ፬ ፡ ፩ — ፳፭

ጥያቄዎች

1. ካርታ አዘጋጅ ፡ ይኸውም የሚከተሉትን ሥፍራዎች የሚያመለክት መሆን አለበት ። ዑር ፡ ካራን ፡ ሴኬም ፡ ቤቴል ፡ ግብፅ ፡ የዮርዳኖስ ወንዝ ፡ ኢየሩሳሌም ታላቁ ባሕር ።



2. ታራ ፡ ሎጥና አብራም ካራን እንደደረሱ ምን ሆኑ ?
3. አብራም ለእግዚአብሔር መሠዊያ የሠራባቸውን ሁለት ሥፍራዎች ጥቀስ ፡
   1.__________ 2.__________
4. የእስማኤል እናትና የአባቱን ስም ጻፍ ። __________
5. እስማኤል ከተወለደ በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ሳያናግረው ስንት ዓመት ቆየ ? __________
6. ዘፍጥረት ፲፯ ፡ ፯ ላይ ያለውን ጥቅስ ጻፍና በቃልህ አጥና ። __________
7. አብርሃም ጻድቅ ተብሎ ለመቆጠር እንደምን በቃ ? __________

8· ለአብርሃም ጽድቅ የተቆጠረለት ከመገረዙ በፊት ነው ወይስ በኋላ ?

______________________________________________

9· የግዝረት ጥቅሙ ምንድር ነው ? ______________________

10· እውነተኛዎቹ የአብርሃም ዘሮች እነማን ናቸው ? (ገላትያ ፫ ፥ ፩ — ፱)

______________________________________________

<u>የአብርሃም መጠራት ፡</u> አብርሃም ከሴም ወገን ነው ። የአባቱም ስም ታራ በመባል ይታወቃል ። ታራም ቤተ ሰቦቹን ይዞ ወደ ከነዓን አገር ለመሄድ ተነስቶ ሳይደርስ በፊት ከራን በተባለው ሥፍራ ጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ ሞተ ።

ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ጥሪ ወደ አብርሃም መጣ ። ይኸም ከአገሩ ፥ ከዘመዶቹ ከአባቱ ቤት ተለይቶ እግዚአብሔር ወደሚያሳየው አገር እንዲሄድ ነበር ። (ዕብ· ፲፩ ፡ ፰) አብርሃምም እግዚአብሔርን ማመኑን በመታዘዙ ገለጸ ። ከነዓንም እንደደረሰ ሴኬም በሚባለው ሥፍራ እግዚአብሔር እንደተናገረው መሠዊያን ሠራ ። አብርሃም ጉዞውን ወደ ደቡብ ቀጥሎ ቤቴል ወደሚባል ሥፍራ ደረሰ ። ቤቴል ማለትም «የእግዚአብሔር ቤት» እንደሆነ ይታሰባል ። አብርሃም በቤቴል ደግሞ መሠዊያ ሠራ ። አብርሃም ጉዞውን በመቀጠል ግብፅ አገር በደረሰ ጊዜ ምንም መሠዊያ አለመሥራቱን መገንዘብ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም ። ለዚህም ምክንያት የሆነው እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ሂድ ሲለው ባለመታዘዝ ወደ ግብፅ በመሄዱ ነው ። በመጨረሻ አብርሃም ከግብፅ አገር ወደ ከነዓን ተመለሰ ። እንደገናም በቤቴል መሠዊያ ሠራ ። (ዘፍጥረት ፲፪ ፡ ፲ — ፲፫ ፡ ፬)

<u>ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ ፡—</u> እግዚአብሔር ለአብርሃም ወንድ ልጅ እንደሚሰጠውና ዘሩንም እንደሚያበዛለት ተስፋ ሰጥቶት ነበር ። ነገር ግን አብርሃም ሽምግሎ ሚስቱም ሣራ አርጅታ ስለነበር ልጅ ለመውለድ ያላቸው ተስፋ የመነመነ ሆኖ ታያቸው ። ስለዚህ ሚስቱ ሣራ አብርሃም ከአገልጋይቱ ከአጋር ጋር ቢተኛ ልጅ እንደሚወልድ ነገረችው ። አብርሃም ያኔ የ፹፮ ዓመት ሰው ነበረ ። የሚስቱን ቃል ሰማ ። በእግዚአብሔር ላይ የነበረ እምነቱን ችላ አለ ። ከአጋርም ጋር ተኛ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወንድ ልጅ ወለደ ። የልጁንም ስም እስማኤል ብሎ ጠራው ። እንግዲህ አሁን የአብርሃም አለመታዘዝ ያስከተለው ጉዳት ቀላል አልነበረም ። እስማኤል ሲወለድ ገና የ፹፮ ዓመት ሰው ነበር ። ነገር ግን ፺፱ ዓመት እስኪሞላው ድረስ እግዚአብሔር አላናገረውም ነበር ። (ዘፍ· ፲፮ ፥ ፩) ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ያስከተለውን ውጤት በዮናስ ሕይወት ታሪክ ውስጥ እንመለከታለን ። እግዚአብሔር ዮናስ ተነስቶ ወደ ነነዌ ከተማ እንዲሄድ ነግሮት ነበር ። ነገር ግን ዮናስ የጥሪ ቃሉን ሰምቶ ከመታዘዝ ችላ በማለት ወደተርሴስ ከተማ በፊቃዱ ተጓዘ ። ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት መኮብለሉን በቆመ ጊዜ እንደገና እግዚአብሔር ዮናስ ሆይ ፥ ተነሥተህ ወደ ነነዌ ከተማ ሂድ ሲል ተናገረው ። (ዮናስ ፩ ፥ ፩ — ፫ ፤ ፫ ፥ ፩ ፥ ፪)

እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር እንደሚለን መዘንጋት ደግሞ የለብንም ። በእርግጥ አብርሃም ታማኝነቱን ባጎደለ ጊዜ እግዚአብሔር ደስ አልተሰኘም ። ይሁን

እንጂ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠበቀ ። ስለዚህም ሊባርከው ፈለገ ። እግዚአብሔር የሚባርከን ለእርሱ ፍጹም ታዛዦች ስንሆን አይደለም ። ነገር ግን በደላችንን ይቅር እያለ በረከቱን ያትረፈርፍልናል ። ስለዚህም በዘፍጥረት ፲፯ እግዚአብሔር ለአብርሃም አዲስ ስም እንደሰጠው እናነባለን ። ይኸውም አብርሃም የሚል ሲሆን ትርጓሜውም የትልቅ ሕዝብ አባት ማለት ነው ። ይህም የሚያሳስበን እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን እንደሚጠብቅ ነው ። ከዚህ የተደጋገመ የተስፋ ቃል በኋላ እግዚአብሔር ለአብርሃም የግዝረትን ምልክት ሰጠው ። (ዘፍ. ፲፯ ፥ ፱ — ፲፬)

<u>የግዝረት ምልክት ፦</u> ግዝረት ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠ ምልክት ነው ። እያንዳንዱም ልጅ በተወለደ በስምንተኛ ቀን መገረዝ ነበረበት ። ይህም የግዝረት ምልክት እስራኤላውያን የሚገዟቸውን ባሮች እንኳ ሳይቀሩ የሚመለከት ነበር ። በዚህም እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳን ዘሩን እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ምድር አሸዋ እንደሚያበዛለት ነበር ። ማስተዋል ያለብን እግዚአብሔር አብርሃምን የባረከው ልጆቹን ስለገረዘ አለመሆኑን ነው ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሊባርከው ተስፋ ስለሰጠው ልጆቹን ገረዘ ።

ከዚህ ጋር ማስተዋል ያለብን የእስማኤልን መገረዝ ነው ። (ዘፍ. ፲፯ ፥ ፳፭) አረቦችም እስከ ዛሬ ድረስ የግዝረትን ሥርዓት ይጠቀሙበታል ። ይሁን እንጂ ይህ አድራጎት እስራኤላውያን ሊያደርጋቸው አይችልም ። እግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ከገባላቸው ሰዎች ክፍል አንድነትን ማግኘት አይችሉም ።

ስለዚህ ግዝረት ለሰው የተለየ በረከትን የሚሰጥና የእግዚአብሔር ተከታይ ሊያደርግ የሚችል አይደለም ። አብርሃም ለምን ተባረከ ? እግዚአብሔርን በማመኑ አይደለምን ? እግዚአብሔርም እንደሚባርከው አመነ ። እኛንስ ቢሆን እግዚአብሔር መቼነው የሚባርከን ? ስንገረዝ ሳይሆን እምነትን ስንታዘዘው ነው ። እስራኤላዊ ለሆነው ሰው የሥጋ ግዝረት መውሰድ አስፈላጊው ነበረ ። ዛሬ ግን ለእኛ የሚያስፈልገን የሥጋ ግዝረት ሳይሆን የልብ ግዝረት ነው ።

«የሥጋንም ሰውነት በመገፈፍ ፥ በክርስቶስ መገረዝ ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ ።» (ቆላ. ፪ ፥ ፲፩)

መገረዝ በዛሬ ዘመናችን የእግዚአብሔርን በረከት ለመቀበል የሚያበቃ አይደለም ። ብንገረዝ እግዚአብሔርን የምንጠቀምበት ባንገረዝ ደግሞ የምናጎድለው ነገር ከቶ የለም ። እግዚአብሔር ዛሬ ከእኛ የሚሻው እምነትን እንድንታዘዘው ብቻ ነው ። እምነታችንን በእግዚአብሔር ላይ አድርገን በሥጋ ብንገረዝ በእውነት የአብርሃም ልጆች ለመባል እንችላለን ፥ የሥጋ ግዝረት ቢኖረንና በእግዚአብሔር የማናምን ከሆነ እንደ እስማኤል ዘር እውነተኛው የአብርሃም ዘር አንሆንም ።

«በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና ።» ገላ. ፭ ፥ ፮

## አሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆችና የዮሴፍ ታሪክ ፦

የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ።

ኦሪት ዘፍ. ፴፯ ፥ ፳፯ — ፴፯
ኦሪት ዘፍ. ፵፪ ፥ ፩ — ፵፪
ኦሪት ዘፍ. ፵፭ ፥ ፩ — ፵
ኦሪት ዘፍ. ፶ ፥ ፲፭ — ፳፩
ማቴዎስ ፳፯ ፥ ፲፩ — ፲፰

### ጥያቄዎች

1. ያዕቆብ ከማን ጋር ታገለ ?
2. ያዕቆብ የሚለው ቃል ፍችው ወይም ትርጓሜው ምንድር ነው ? እስራኤል ለሚለው ቃል ትርጉም ስጥ ።
3. የዮሴፍ ወንድሞች ለምን እንደጠሉት ሦስት ምክንያቶች ስጥ ።
   ሀ. ____________________
   ለ. ____________________
   ሐ. ____________________
4. ዘፍጥረት ምዕራፍ ፶ ፥ ፳ን ከዚህ በታች በለው መስመር ላይ ጻፍና በቃል ሀ አጥና ። ____________________
   ____________________
5. የዮሴፍና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ታሪክ የሚመሳሰሉበትን ስድስት ነገሮች ጻፍ ።
   1. ____________________
   2. ____________________
   3. ____________________
   4. ____________________
   5. ____________________
   6. ____________________
6. ዮሴፍ እንዳይገደል የሞከረው ወንድም ስም ማን ነው ? ____________________
7. በሰባቱ የረሃብ ዘመናት ግብፃውያንን ከረሃብ ለማዳን ዮሴፍ ያወጣው አቅድ ምን ነበር ? ____________________

አሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ፦ በዛሬው ዘመናችን እስራኤል ስንል ስለ አገሪቱ የምንናገር እንኳን ቢመስል ከአንድ አራት ሺህ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ያዕቆብን በመምረጥ እስራኤል በማለት ሌላ ስም እንደሰጠው መዘንጋት የለብንም ።

ያዕቆብ የይስሐቅ ልጅ የአብርሃም የልጅ ልጅ ሲሆን የስሙም ትርጓሜ የሚያሰናክል ማለት ነው ። ወንድሙን ዔሳውን ሁለት ጊዜ አሰናክሉታል ። በመጀመሪያው ጊዜ ወንድሙ አደን ውሎ ተርቦ መጣ ። ምግብም ቢጠይቀው ብኩርናህን ሽጥልኝ አለው ። ያዕቆብም በምስር ወጥ ብኩርናውን ገዛ ። ሁለተኛ ጊዜ ደግሞ አባታቸው ሸምግሎ ልጆቹን ሊባርክ ሲል እኔ ዔሳው ነኝ በማለት ያዕቆብ የወንድሙን በረከት ለመውሰድ ቻለ ። (ዘፍ· ፳፭ ፡ ፳፱ ፴፬ ፤ ፳፯ ፡ ፩ — ፵)

እግዚአብሔር ግን ያዕቆብን ለወጠው ። ያዕቆብ ወንድሙ ዔሳውን ፈርቶ ሸሸ ። በላባን ቤት በካራን አገር ብዙ ጊዜ ቆየ ። ያዕቆብ ወንድሙን ዔሳውን ከማግኘቱ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር ሌሊቱን ሁሉ ታገለ ። በረከቱንም እስኪያገኝ ድረስ ከመታገል አልተቆጠበም ። ያዕቆብ የዔሳውን ብኩርናና በረከቱን ቀማ ። ነገር ግን በሕይወቱ የእግዚአብሔርን በረከት እንዳጣ ትመለከታላችሁን ? ሰውን ሊያረካውና ብቃቱም ለመሆን የሚችለው የእግዚአብሔር በረከት ብቻ ነው ።

ስለዚህም ያዕቆብ እስራኤል ተባለ ። አሥራ ሁለት ልጆችም ወለደ ። የልጆቹም ስም ሮቤል ፣ ስምዖን ፣ ሌዊ ፣ ይሁዳ ፣ ዳን ፣ ንፍታሌም ፣ ጋድ ፣ አሴር ፣ ይሳኮር ፣ ዛብሎን ፣ ዮሴፍና ብንያም ይባሉ ነበር ። ዮሴፍንና ብንያምን ከራኄል ወለደ ። ደግሞም የመጨረሻ ልጆች ስለነበሩ አባታቸው ያዕቆብ ከሌሎቹ ሁሉ አብልጦ ይወዳቸው ነበር ። ከዕለታት አንድ ቀን አባታቸው ያዕቆብ ለዮሴፍ ብቻ አንድ ዝንጉርጉር የሆነች ጥብቆ ገዛለት ። በዚህን ጊዜ የቀሩት ወንድሞች ሁሉ በዮሴፍ ላይ ቀኑበት ። በጥላቻም መንፈስ ተነሣሡበት ። ከዕለታት አንድ ቀን ዮሴፍ ሕልም አለመ ። የሕልሙም ትርጓሜ ዘመዶቹ ሁሉ ለዮሴፍ እንደሚሰግዱለት የሚያስረዳ ነበር ።

<u>የእስራኤል ነገድ ወደ ግብፅ መግባት ፡—</u> እግዚአብሔር ለዓለም የተሟላ አቅድ አለው ። የመስቀሉም ነገር በዚህ ዓላማ ውስጥ ያለ ነው ። ለእስራኤላውያን የመስቀሉን ነገር ለማሳሰብና የመዋጀቱን ትርጉም ለማስረዳት በግብፅ አገር ባሮች እንዲሆኑ ፈቀደ ። ስለዚህም ወንድሞቹ ዮሴፍን እንዲጠሉትና ለግብፅ አገር ነጋዴዎች እንዲሸጡት አደረገ ። ዮሴፍም ለጲጥፋራ በተሸጠ ጊዜ እግዚአብሔር ይጠብቀው ነበር ። በእስር ቤት በነበረ ጊዜ እንኳን አልተለየውም ። ወንድሙ ሮቤል ከመገደል አተረፈው ። ፈርዖን ሕልም እንዲያልም ያደረገው የእንጀራ አበዛና ጠጅ አሳላፊው አብረው ከዮሴፍ ጋር በእስር ቤት እንዲሆኑ ያደረገው እግዚአብሔር ነው ።

ዮሴፍ ለፈርዖን ሕልሙን በመፍታት ለእግዚአብሔር ክብር እንደሚሰጥ ይታመንበት ነበር ። ያለ አንዳች ጥፋት ለብዙ ዓመታት እስር ቤት ቆየ ። ይሁን እንጂ ያኔም ቢሆን እንኳ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ዝግጁ ነበር ። ስንቶች ናቸው ያለ ጥፋታቸው ስለታሰሩ የሚማረሩት ? ዮሴፍ ግን የተማረረ አልነበረም ። ዮሴፍ ሕልሙን ተረጎመ ። በሚመጡትም ሰባት የረሃብ ዘመናት የሚሆን እህል እንዲያከማች ምክር ሰጠ ።

ዮሴፍ እንዳለው እንዲያከናውን ተደረገ ። ዮሴፍም የዚህን ሥራ ኃላፊነት እንዲወስድ ሥልጣን ተሰጠው ፤ ሰባቱም የረሃብ ዘመናት መጡ ። በከነዓንና በእስራ

ኤል ሁሉ ላይ ደረሰ። እስራኤልም ልጆቹን ወደ ግብፅ ሄደው እህል እንዲገዙ ሰደዳቸው። እጅ የነሱት ሰውዬም ዮሴፍ ነበር። እግዚአብሔር እንዳቀደው ሆነ። ወንድሞቹ ሞቶአል ብለው ያሰቡት ሰው አሁን ገዢና ታላቅ ሰው ሆኖ አገኙት።

ተመሳሳዩም ሁኔታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ደርሶአል። ወገኖቹ ወደ ሆኑት ወደ እስራኤላውያን መጣ። አልተቀበሉትም። እንዲያውም በቅናት በመስቀል ላይ እንዲሞት አደረጉ። የሞተና ተስፋም የሌለው መሰላቸው። እርሱ ግን ሕያው ሆነ። አንድ ቀንም ጉልበት ሁሉ ለዚህ መድኅን ይንበረከክለታል።

<u>በግብፅ የነበረ ጭቆና ፦</u> ምንባብ ዘጸአት ፩ ፥ ፩ — ፲፬
ዘጸአት ፪ ፥ ፳፫ — ፫ ፥ ፲ እና የሐዋ. ሥራ ፯ ፥ ፲፯ ፥ ፴
ዘጸአት ፱ ፥ ፲፫ — ፲፮ እና ሮሜ ፱ ፥ ፲፬ — ፲፰

## <u>ጥያቄዎች</u>

1. ከያዕቆብ ቤተሰቦች ስንቶቹ ወደ ግብፅ ወረዱ ? ____________________
2. ግብፃውያን እስራኤላውያንን ለምን ይፈሩአቸው ነበር ?____________________
3. ዘጸአት ፩ ፥ ፲፪ በቃልህ አጥናና እዚህ ላይ ጻፍ። ____________________
____________________________________________
4. ሙሴ በፈርዖን ቤተ መንግሥት ስንት ዓመት ተቀመጠ ?____________________
   ሀ) የአማቹን በጎች ለስንት ዓመታት ጠበቀ ? ____________________
   ለ) እስራኤላውያን በግብፅ ስንት ዓመታት ቆዩ ? ____________________
5. እግዚአብሔር በቁጥቋጦ ውስጥ ሲያናግረው ሙሴ ምን አደረገ ? ለምን ?
____________________________________________
6. እግዚአብሔር የሕዝቤን ጭንቀት ሰምቻለሁ ጩኸታቸውንም አድምጫለሁ እንዳለ እናነባለን። ይህንን በሰማ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገ ?
____________________________________________
____________________________________________
7. እግዚአብሔር ሙሴ ሕዝቡን ይዞ ከግብፅ እንዲወጣ አዘዘው። ሙሴ ስለ ታዛዥ ____________________ ልንለው እንችላለን ?____________________
____________________________________________
8. እግዚአብሔር ፈርዖንን ለምን አስነሣው ? ____________________
9. ኢሳይያስ ምዕ. ፵፬ ፥ ፳፬ — ፵፯ ፥ ፯ አንብብና ስለ ቂሮስ የምታውቀውን ጻፍ። እነዚህ ቁጥሮች በምድር ላይ ስለሚሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ያስተምሩናል ?____________________
____________________________________________
____________________________________________

<u>እስራኤል በግብፅ አገር ፡</u> እግዚአብሔር አብርሃምን ከአገሩ ከካራን ወጥቶ ወደ ከነዓን አገር እንዲሄድ ጠራው ። ነገር ግን በእስራኤላውያን ታሪክ ውስጥ የመ ስቀሉን ታሪክ ለማኖር እግዚአብሔር ከባርነት ሊያወጣቸው ወደደ ። የዮሴፍን ወን ድሞች ጥላቻና ምቀኝነት እግዚአብሔር ዮሴፍን ወደ ግብፅ በመውሰድ ምክንያት አድርጎ ተጠቀመበት ። የመጣውንም የረሃብ ዘመን ወንድሞች ወደ ግብፅ ለመውሰ ድ ምክንያት ሆነ ። ስለሆነም ሰባ የሚያህሉ ሰዎች ወደ ግብፅ ወረዱ ።

እግዚአብሔር ዘርህን አበዛዋለሁ ብሎ ለአብርሃም የሰጠው የተስፋ ቃል ከለፈ ብዙ ዘመን ሆነ ። ወደ ግብፅም የወረዱት ሰባ ሰዎች ብቻ ነበሩ ። ሆኖም ከዓመት ወደ ዓመት ቁጥራቸው እየጨመረ ሄደ ። በመጨረሻም ለአብርሃም የተሰጠው የተ ስፋ ቃል እንደተፈጸመ በግልጽ እየታየ ሄደ ።

<u>የጭቆናው ዘመን ፡—</u> እስራኤላውያንን ከግብፅ አገር አውጥቶ ወደ ከነዓን አገር እንዲገቡ የእግዚአብሔር ፍላጎት ነበረ ። እስራኤላውያን በግብፅ አገር ሲኖሩ የግብፃውያን የምግብ ዓይነት በመልመድ ወደዱት ። (ዘኍ. ፲፩ ፡ ፬ — ፮) ታዲያ ለምን መውጣት አስፈለጋቸው ? ዘመኑ እያለፈ ሲሄድ የዮሴፍን ወሮታ የማያውቅ ዳግማዊ ፈርዖን ተነሣ ። የእስራኤላውያን ቁጥር እየበዛ ስለሄደ አንድ ቀን እንኳን ጦርነት ቢነሣ በማሸነፍ አገሪቱን የሚወስዱ መስሎ ታየው ። እስራኤላውያንም በሰው ሐገር እንደ እንግዳ መታየታቸው ቀርቶ ባሮች ሆኑ ።

እስራኤላውያን በባርነት ተይዘው በነበሩበት ዘመን ሙሴ ተወለደ ። ሕይወቱም በእግዚአብሔር ጠባቂነት በፈርዖን ልጅ ተይዞ ነበር ። በቤተ መንግሥትም የግብፃ ውያንን ጥበብ ሲማር ለአርባ ዓመታት ያህል ቆየ ። (የሐዋ. ሥራ ፯ ፡ ፳፪) ሙሴ በጥበብና በእውቀት እያደገ ሄደ ። ኃይለኛና ብርቱ ሰው መሆኑም አንዱን የግብፅ ዘበኛ በመግደሉ ለመታወቅ ተችሏል ። ይህንንም ክፉ አድራጎት በመፈጸሙ ከአገሩ እንዲሸሽ ተገደደ ።

ለአርባ ዓመታትም ያህል በሲና ተራራ አጠገብ በጎችን ሲጠብቅ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቁ ይሆን ዘንድ ትሕትናንና ትዕግሥትን እየተማረ ቆየ ። እግዚአብሔ ርም ይህን ሰው ለመንፈሳዊ ሥራ እያዘጋጀው ሰማንያ ዓመት አለፈ ። በእነዚህም ሰማንያ ዓመታት አይሁዶች በጭቆና ውስጥ ስለነበሩ ልመናቸውን ወደ እግዚአብ ሔር አቀረቡ ። በመጀመሪያም እግዚአብሔር ጩኸታቸውን የሰማቸው መስሎ አል ታያቸውም ። ብዙም አይሁዶች እግዚአብሔር ሙሴን ለመሪነት እንዳዘጋጀላቸው ሳያዩ ሞተዋል ። ይሁን እንጂ በመጨረሻ ሕዝቡን ከግብፅ የጭቆናና የባርነት ቤት ለማውጣት እግዚአብሔር ያሰበ መሆኑን እየነደደ ከልተቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ ሙሴን አናገረው ።

እግዚአብሔር እንደዚህ ባለ አኳኋን ለሙሴ ለምን እንደተገለጠለት አናው ቅም ። ነገር ግን አንድ ትልቅ ኃይል የሚነሣው አንድን ነገር ለማጥፋት ብቻ እንዳ ልሆነ ለሙሴ ለማስረዳት ነበር ።

## ፋሲካና የሲና ኪዳን ።

ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፦ ዘጸአት ፲፪ ፥ ፩ — ፳፰
ዘጸአት ፳፬ ፥ ፩ — ፰
ዕብራውያን ፱ ፥ ፲፩ — ፳፰ ፤ ፲ ፥ ፩ — ፬

**ጥያቄዎች**

1. እስራኤላውያን ይሠውት ስለነበረው በግ አጭር መግለጫ ስጥ ። ________________

2. የበጉን ደም ምን ላይ ይረጩት ነበር ? ________________
3. እስራኤላውያን ፋሲካን የሚበሉት በእንዴት ያለ አኳኋን ነበር ? ________________

4. እርሾ ከእስራኤላውያን ቤት እንዲወገድ ለምን ተደረገ ? ________________

5. ሀ) ወደ ግብፅ የወረዱት እስራኤላውያን ስንት ነበሩ ? ________________
   ለ) ግብፅን ትተው የወጡትን እስራኤላውያን ቁጥር ጻፍ ። ________________
   ሐ) በግብፅ አገር ስንት ዓመታት ተቀመጡ ? ________________
6. ዘጸአት ፳፬ ፥ ፫ በቃልህ አጥናና እዚህ ላይ ጻፍ ። ________________

7. ሙሴ በዘጸአት ፳፬ እንደምናነበው የደሙን የመጀመሪያና ሁለተኛ እኩሌታ ምን አደረገው ? ________________
8. አሮን በሬንና ፍየሎችን ስለ እስራኤል ኃጢአት መሥዋዕት ያቀርብ ነበር ። ይህ መሥዋዕት የኃጢአት ይቅርታ ይሰጥ ነበር ? ________________
9. ክርስቶስ ምንን መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ ? ________________
10. ዕብራውያን ምዕራፍ ፲ ፥ ፬ን በቃልህ አጥና ። ________________

## ፋሲካና ክርስቶስ ።

የእስራኤላውያን ከግብፅ አገር መውጣት ክርስቶስ አንድ ቀን ለሚያወርሳቸው መንግሥት የሚያዘጋጃቸው መሆኑን ያሳስባል ። በግብፅ ባሮች እንደነበሩ ልክ እንደ ዚሁ ደግሞ ለኃጢአት ባሮች ሆኑ ። ራሳቸውን ከፈርዖን የጭቆና እጅ ማውጣት እንዳቃታቸው ሁሉ በኀይላቸውና በብርታታቸው ራሳቸውን ከኃጢአት ማዳን አልቻሉም ። የበጉም ደም መፍሰስ እንደነበረበት እንዲሁም የክርስቶስ ደም መፍሰስ አስፈላጊ ሆነ ። ግብፅን ትተው እንደወጡ እንዲሁም ከዓለማዊነት ባሕርይ በመለየት ክርስቶስን መከተል ነበረባቸው ።

እስከ ዛሬ ፋሲካ በአይሁድ ዘንድ ታላቅ በዓል ነው ። በቤታቸው እርሾ እንዳይገኝ ያደርጋሉ ። የተጠበሰ በግ ይበላሉ ። በመጽሐፍ ቅዱስ እርሾ የኃጢአት ምሳሌ

ነው ። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሾን የመንግሥት ሰማያት ምሳሌ አድርጎ ተና ግሮአል ። ትምህርቱም አንድ ብርቱ ክርስቲያን በምስክርነቱ በአካባቢው ላሉት ነዋ ሪዎች ጥሩ ምሳሌ ለመሆን እንደሚችል ለማሳሰብ ነው ።

ዛሬ እንኳን አይሁዶች መራራ ቅጠል ይበላሉ ። ይህንንም የሚያደርጉት በግ ብፅ የነበሩበትን የባርነት ጊዜ ለማስታወስ ነው ። እግዚአብሔር ግን የክርስቶስን መከራ ምሳሌ አድርጎ እንደሰጣቸው አላስተዋሉም ።

አይሁዶች ይበሉት የነበረው በግ ወይም ፍየል አንድ ዓመት የሞላው መሆን ነበረበት ። ይህም በግ ወይም ፍየል ነውር የሌለው ከመሆኑም በላይ በሽታ እንዳ ለው ወይም እንደሌለው ለማወቅ ለአራት ቀናት በተለየ ሥፍራ ይቀመጣል ። ከዚ ያም በጉ ይታረድና ደሙ በበራቸው ላይ ይቀባል ። ይህን በማድረጋቸው ለእግዚ አብሔር መታዘዛቸውን ቤታቸውን የሚጎበኙ ሁሉ ያውቃሉ ። መልአኩ ደሙን በበራፉ ግራና ቀኝ ባለው እንጨት ላይ ተረጭቶ ሲያይ ለእግዚአብሔር እንደታዘዙ ይመለከት ነበር ።

ምንም እንኳን እስራኤላውያን ከግብፅ ለመውጣት የተከፈተ በር ባይታያቸ ውም በእምነት ከአምላካቸው በሚያገኙት ፈቃድ እንደሚወጡ ያምኑ ስለ ነበር ልብ ሳቸውን ለብሰው ለመውጣት ተዘጋጅተው ፋሲካን በሉ ። እግዚአብሔርም ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ አምላክ ስለሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከግብፅ መውጣት ቻሉ ። ዮሴፍ በሥልጣን በነበረበት ዘመን ወደ ግብፅ የወረዱት እስራኤላውያን ቁጥር ሰባ ብቻ ነበር ። አሁን ግን ብዛታቸው ስድስት መቶ ሺህ ወንዶች ሲሆኑ ከሴቶችና ከሕፃናት ጋር ወደ አንድ ሚሊዮን ደረሱ ። ቁጥራቸው እስከዚህ ሊደርስ የቻለው በ፬፻፴ ዓመታት ውስጥ ነው ። ይህን ሁኔታ ሲያይ ፈርዖን ፍርሃት አደረበት ።

<u>በሲና ተራራ የተሰጠ ቃል ኪዳን ፦</u> እስራኤላውያን ጌታ የቱን ያህል አስፈላ ጊያቸው እንደሆነ ከማወቃቸው በፊት ኃጢአት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ ነበረባቸው ። ስለዚህም ወደ ከነዓን ከመግባታቸው አስቀድሞ እግዚአብሔር ሕግን ሰጣቸው ፣ ሕጉን ሲቀበሉ ያለ አንዳች ስሕተት የሚፈጽሙ መስሏቸው «እግዚአብ ሔር ያለውን ሁሉ እናደርጋለን» አሉ ። (ዘጸአት ፲፱ ፣ ፰ እና ፳፬ ፣ ፯) እግዚአብ ሔር ከእኛ ከሰዎች ምን እንደሚጠብቅ አልተረዱም ። ሕግ የተሰጠበት ምክንያት እኛ ኃጢአተኞች መሆናችንን እንደመስታወት ለማሳየት ነበር ።

ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤልያስ ተገለጠለት ። ይህም ኃይሉንና ምሕረቱን ለማሳየት ነበር ። እግዚአብሔርም ለኤልያስ በተገለጠ ለት ጊዜ ታላቅ አውሎ ነፋስ የመሬት መንቀጥቀጥና እሳት ሆነ ። ወዲያው ይህ ሁኔታ ተለወጠና ጸጥታ የተሞላበት ጊዜ መጣ ። በዚህ ረገድ እግዚአብሔር በቁጥ ቋጠ ውስጥ የተገለጠው ለሙሴ ትምህርት ለመስጠት ሳይሆን አይቀርም ። ሙሴ በቁጥቋጠ የሚነደውን እሳት በማየት የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደሰማ ፊቱን በመሸፈን እኛ ኃጢአተኛና እርሱ ቅዱስ መሆኑን አስገነዘበ ። በተጨማሪ ኢሳይያስ

ምዕራፍ ፯ እና ዘዳግም ፬ ፥ ፲፬ ተመልከት ። እግዚአብሔር ሙሴን እንዳናገረው የእስራኤላውያንን ችግርና መከራ ያየና የተመለከተ መሆኑን ገለጸለት ። ለማዳን የመጣ መሆኑንም ገለጸለት ። እስራኤላውያንን ለማዳን በባሪያው በሙሴ በኩል ተጠቀመ ። ሙሴ የእግዚአብሔር ወዳጅ ፥ (ዘጸ. ፴፫ ፥ ፲፩) የእግዚአብሔር ባሪያ (ዘኁ. ፲፪ ፥ ፯) ነቢይ (ዘዳ. ፴፬ ፥ ፲) በመባል በብዙ ስሞች ሲጠራ ነበር ። የእግዚአብሔር መልእክተኛ (ዘጸ. ፫ ፥ ፲)

<u>እግዚአብሔር የሁላችን አምላክ ነው ፡—</u> ከፈርዖን ታሪክ የምናገኘው ትምህርት እግዚአብሔር የሁሉ በላይ ጌታ መሆኑን ነው ። አንዳንዶች በፍቅር አንታዘዝም ቢሉም እንኳን በግድ ይታዘዙለታል ። ፈርዖን የእስራኤላውያን ቁጥር እየበዛ ስለ ሄደ አንድ ቀን የበላያችን በመሆን ይገዙናል በማለት በጣም ፈራ ። ስለዚህም እስራኤላውያንን መጨቆን ጀመረ ። እግዚአብሔር የፈርዖንን የጭቆና አገዛዝ ለመልከም በማድረግ ለሕዝቦቹ ያለውን ዓላማ ዘረጋበት ።

እግዚአብሔር ሰዎች በክፋት መንፈስ ተነሣስተው ለመጉዳት ሲያስቡ ለመልከም እንደሚለውጠው የሚያሳስቡትን ክፍሎች ወደፊት በሰፊው እንመለከታለን ። ይሁዳ አስቆሮቱ ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ መስጠትን ብምርጫው የወሰነ ቢሆንም እግዚአብሔር ያንን ምርጫ ለዓላማው መፈጸሚያ አድርጎ ተጠቅሞበታል ። የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ (ኢሳ. ፵፬ እና ፵፭ ዕዝራ. ፩ ፥ ፩) የማረካቸውን እስራኤላውያን ወደ አገራቸው መመለስ መልከም የአስተዳደር ዘዴ መስሎት እርምጃ ቢወስድም እግዚአብሔር ይህን ውሳኔ ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ በማድረግ ዓላማውን ፈጸመበት ። በዚህም እግዚአብሔር ከሁሉ በላይና እርቆ ተመልካች መሆኑን ለመረዳት እንችላለን ። (ኤፌ. ፩ ፥ ፳፪) ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ፥ ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው ።

<u>እስራኤልና አሕዛብ ።</u>

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለምን እንደመረጠ ።

ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፡— ዘኁልቁ ፲፭ ፥ ፲፩ — ፴፩
ዘሌዋውያን ፲፱ ፥ ፴፫ — ፴፯
ዘጸአት ፲፪ ፥ ፵፫ — ፵፱
ኢሳይያስ ፵፱ ፥ ፩ — ፲፪
ዘጸአት ፳ ፥ ፰ — ፲፩

<u>ጥያቄዎች</u>

1. ዘኁልቁ ምዕራፍ ፲፭ ፥ ፲፯ እዚህ ላይ ጻፍና በቃልህ አጥና ። ____________

____________________________________________

2. አንድ እስራኤላዊ ሳያውቅ በስሕተት ኃጢአት ቢሠራ ከሀኑ መሥዋዕት የሚያቀርበው ለማን ነው ? ____________________________

3· አንድ እስራኤላዊ አውቆ በድፍረት ኃጢአት ቢሠራ ምን ይደርስበታል ? ______________________

4· እስራኤላውያን እንግዶችን፣ መጻተኞችን ተቀባይ እንዲሆኑ መምሪያ ለምን ተሰጣቸው ? ______________________

5· እንግዳ የሆነው ሰው በፋሲካው በዓል ተካፋይ ለመሆን ከፈለገ ምን ማድረግ አለበት ? ______________________

6· በሰንበት ቀን ማድረግ የሌለባቸውን ሰባት ነገሮች ጻፍ ። ______________________

7· እግዚአብሔር ለባሮቹ ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ተግባር ምንድር ነው ? ኢሳ· ፵፱ ፣ ፩ ፣ ፮ ______________________

## የዓለም ሕዝብ ።

**የሚነበቡ የመጽሐፍ ክፍሎች ፦** አሪት ዘጸአት ፱ ፣ ፲፫ — ፲፮ ፤ ሮሜ ፱ ፣ ፲፬ — ፲፰ ፤ ኢያሱ ፮ ፣ ፲፭ — ፳፮ ፤ ፩ኛ ነገሥት ፲፮ ፣ ፳፱ — ፴፬

**ጥያቄዎች**

1· እግዚአብሔር በፈርዖንና በሕዝቡ ላይ መቅሰፍትን የላከ ምን እንዲያውቁ ነበር ? ______________________

2· እግዚአብሔር ፈርዖንን ያስነሣው በምን ምክንያት ነበር ? ______________________

3· የሚከተሉትን ጥቅሶች ሙላቸው ፦

ሀ· የምምረውን ሁሉ ______________________ ለምራራለትም ሁሉ

ለ· ምሕረት... ወይም

አይደለም ከሚምር ______________________ ነው እንጂ

ሐ· ብርና ወርቅ ሁሉ የናስና የብረትም ዕቃ ______________________

መ· ኢያሪኮን ለመሥራት የሚነሣ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ______________________

4· ሀ· አክዓብ የማን ልጅ ነበረ ?

ለ· ምን ያህል ጊዜ በእስራኤል ላይ ነገሠ ? ______________________

ሐ· መናገሻ ከተማው ማን ይባላል ? ______________________

5· የሚከተሉትን ጥቅሶች ሙላቸው

አክዓብም ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ______________________

6. ሀ. ማን ነበረ ኢያሪኮን ያሠራው ? ____________________

ለ. በኩር ልጁስ ማን ይባላል ? ____________________

ሐ. የታናሹ ልጁስ ስም ማን ነው ? ____________________

1. እግዚአብሔር በፈርዖን እንደተጠቀመበት ።

ቤተ እስራኤል አንድ ሰባ ነፍሳት ሆኖ ወደ ግብፅ እንደወረደ በሰላምና በደስታ ሊኖር ቻለ ፤ ይኸውም ፈርዖን ስለ ዮሴፍ ጥበብና በጎ አስተዳዳሪነቱን በማስተዋል ነው ። የሆነ ሆኖ እዚያም በግብፅ አገር እንዲቀመጡ የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነበረም ፤ ለእነርሱ የተሰጠ አገር ከነዓን ነውና ።

በዚህም መሠረት እንግዲህ እግዚአብሔር ዮሴፍን ያላወቀ ሌላ ንጉሥ ማለት ፈርዖንን አስነሣው ። የእርሱም ጭከና የታወቀ መሆኑን በማስተዋል አነገሠው ። ሕዝቡም ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ ጩኸታቸውን ሰማ ፤ የሚያመልጡበትንም መንገድ አዘጋጀላቸው ። ፈርዖን እንግዲህ ምንም እንኳን እግዚአብሔርን ባያውቅ የእግዚአብሔርን አሳብ መፈጸም ግድ ሆነበት ።

2. የእግዚአብሔር ሃሳብ ስለ ኢያሪኮ ።

የእስራኤል ሕዝብ ወደ ከነዓን እንዳይገባ የኢያሪኮ ንጉሥ ከነወታደሮቹ ከከተማው ገብተው በሮችን ሁሉ ዘጉባቸው ። ልክ እንዲሁ አማኞች ወደ ተስፋው አገር እንዳይገቡ ማለት ልባቸውን ለእግዚአብሔር እንዳይሰጡ ሰይጣን መንገዱን ሊዘጋባቸው ይሞክራል ። ሆኖም ሊከለክለን የሚችል ማንም የለም ።

እግዚአብሔር ኢያሱን ፤—

ተመልከት ኢያሪኮንና ንጉሥዋን ጽኑዓን ኃያልዋንም በእጅህ ሰጥቻለሁ ። ኢያሱ ፮ ፤ ፪

ነገር ግን ረዓብ የምትባለዋ ምንም እንኳ ከኢያሪኮ ሕዝብ መካከል አንድዋ ብትሆን ከዚህም በላይ ደግሞ ጋለሞታ ብትሆን ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የመተባበር ምኞት ስለነበራት እግዚአብሔር ምሕረቱን አደረገላት ።

ኢያሪኮ ራሷ ግን የተረገመች ከተማ ሆነች ፤ ከዚህም ዘመን በኋላ በአክዓብ ዘመነ መንግሥት አኪኤል ምናልባት ከተማይቱ የተረገመች መሆኗን እግዚአብሔር ረስቶአል በማለት ከተማይቱን እንደገና አሠራት ። ልክ ኢያሱ እንዳለ በበኩር ልጁ መሠረቱን አኖረ ፤ በታናሹ ልጅ ደግሞ በሮችዋን አቆመ ።

3. የአክዓብ ጥፋት ።

አክዓብ ከእስራኤል ነገሥታት ሁሉ ይልቅ እጅግ በጣም ከፉ ኃጢአት እንደ ሠራ መጽሐፍ ቅዱሳችን ያወሳል ፤ ሌሎች ነገሥታት ኃጢአትን እንደሠሩ እርሱ ደግሞ ኃጢአትን ሠራ ። እንዲያውም ከዚያም በላይ የሚያስደንቀው ከሲዶን አገር በዓል የተባለውን ጣዖት ወደ እስራኤል አገር ማምጣቱ ነው ። ያመጣውን ጣዖት

ከሰገደለት በኋላ ሌሎችም የእርሱን ዓላማ እንዲከተሉ አደረገ፡ እንዲሁም የሲዶንን ንጉሥ ልጅ ማለት የኢትበአልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባት ።

ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፡ ለሦስት ዓመታት ያህል ዝናብ አልነበራቸውም፣ ሁሉም እንደበረሃ ሆነ። ኤልያስ ግን በቀርሜሎስ ተራራ የበዓልን ነቢያቶች ሁሉ ድል አድርጎ የበላይነቱን ስላሳየ አክዓብ በፍርሃት ምክንያት ወደ መናገሻ ከተማው ወደ ሰማርያ መሸሽ ግድ ሆነበት፣ ኤልዛቤል ግን ሳትፈራም ሆነ ሳትጸጸት ኤልያስን ለማስፈራራት ሞከረች ።

የአክዓብ ጥፋት እንግዲህ ግልጽ ሆኖ ይታያል፡ እነሆ በመጀመሪያ ያላመነች ሴት በሚስትነት በማግባቱ ሁለተኛ ደግሞ የሌሎችን አማልክት በማምለኩ ነው። የእስራኤልም ሕዝብ ከአክዓብ መጥፎ አካሄድ ወርሰው በሃይማኖታቸው መጠራጠርን ጀመሩ። ወደማይገባቸውም ክፉ ነገር ሁሉ ማምራት ጀመሩ ።

የዓለም ሕዝብ እንደዚህ ያለውን ችግር በእስራኤል ላይ እንደሚያመጡ እግዚአብሔር ስላወቀ ፈጽመው እንዲያጠፉአቸው አዘዛቸው። ልክ ሳአል ለአጋግና ለሕዝቡ እንደራራ እንዳላጠፉቸውም እንደዚሁም የእስራኤል ሕዝብ ጠላቶቻቸውን ለማጥፋት አልቻሉም። ለምሳሌ፣— ይሁዳ በሸለቆው የነበሩትን ሕዝቦች ሊያወጣቸው አልቻለም፡ ምናሴም ከነዓናውያኖችን አላስወገዳቸውም። መሳፍንት ፩፣ ፲፱ እና ፳፯ ከነዓናውያንም ደግሞ በኤፍሬም መከከል ተቀመጡ፣ ግብርም የሚገብሩላቸው ሆኑ። መሳፍንት ፩፡ ፴

ይህም ለእኛ ማስጠንቀቂያ ነው፣ ኃጢአትን ከሕይወታችን ማስወገድ ይገባናል። ብንራራለት ግን ለእኛና ለቤተ ሰቦቻችን በቤተ ክርስቲያናችንም ሁሉ እንቅፋት ሊሆንብን ይችላል ።

## የእግዚአብሔር ሃሳብ ስለ አሕዛብ ።

<u>የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣—</u> ዘኁልቁ ፲፰፣ ፲፩ — ፴፩
ዘሌዋውያን ፲፱፣ ፴፫ — ፴፯
ዘጸአት ፲፪፣ ፵፫ — ፵፱ እና ፳፣ ፰ — ፲፩
ኢሳይያስ ፵፱፣ ፩ — ፲፪

<u>ጥያቄዎች</u>

1. ዘኁልቁ ፲፫፣ ፲፯ ጻፍና በቃልህ አጥናው። ______________________________

______________________________________________

2. ከአይሁዶች መከከል አንድ ሰው ሳያውቅ ኃጢአትን የሠራ እንደሆነ ማን ነበር ሥርየትን የሚያስገኝለት ?______________________________

3. ይህን ያደረገው በምን ምክንያት ነበር ?______________________________

4. ሰው አውቆ ኃጢአትን ከሠራ ምን ይሆናል ? ______________________

5. በመካከላቸው የሚገኙት እንግዶች ወይም መጻተኞች እንደ አገሩ ልጆች ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለምን አዘዛቸው ? ________

______________________________________________

6. አንድ እንግዳ በፋሲካ ተካፋይ ለመሆን ሲፈልግ ምን ማድረግ አለበት ?

______________________________________________

7. በሰንበት ምንም ሥራ እንዳይሠሩ በተለይ ሰባት ሰዎች ተጠቅሰዋል ። እነርሱስ እነማን ነበሩ ?

ሀ. ______________________ መ. ______________________

ለ. ______________________ ሠ. ______________________

ሐ. ______________________ ረ. ______________________

ሰ. ______________________

8. በኢሳይያስ ፶፮ ፥ ፮ ፥ ፯ እንደምናገኘው እግዚአብሔር ለአይሁዶች የሰጠው ልዩ ሥራ ምን ነበር ? ______________________

## ማስረጃ

እግዚአብሔር አብርሃምንና የአብርሃምን ዘር የመረጠው በዓለም ሁሉ እንደ ብርሃን እንዲሆኑ ነው ።

እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ
ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ፤ ይላል እግዚአብሔር ። ኢሳ ፵፱ ፥ ፮

በዚህም መሠረት እግዚአብሔር አይሁዶችን በተለይም በሁለት በኩል አከበራቸው ፣ ቃል ኪዳኑን ለአይሁዶች ሰጠ ። ሮሜ ፫ ፥ ፪ ቀጥሎም ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ መጣላቸው ፣ በዘሩ በኩልም ማለት በሥጋዊ በሕርዩ ፍጹም አይሁዳዊ ነበር ። ሮሜ ፱ ፥ ፭ በእግዚአብሔር አስተያየት በኢየሩሳሌም የተቋቋመችን ቤተ መቅደስ ለዓለም ሕዝብ ሁሉ የጸሎት ቤት ነበረች ። ኢሳይያስ ፶፮ ፥ ፯

### አሕዛብ በቃል ኪዳኑ ስለ መግባታቸው ።

ከአሕዛብ መካከል ማንኛውም ሰው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለመተባበር ቢፈልግ ኖሮ አንድ ሥርዓት ፣ አንድ ሕግ ፣ አንድ ፍርድ መቀበል ነበረበት ። ከፋሲካው ተካፋይ ለመሆን ከፈለገ ደግሞ እንደ ሕጉ መገረዝ ነበረበት ። ይህም ግዝረት ለአብርሃም የተሰጠው የቃል ኪዳን ማረጋገጫ ነው ። ግዝረት ለማንኛውም አይሁድ ከዓለም ርኩሰት ሁሉ ይለይ ዘንድ የተሰጠ ማስታወሻ ነበር ፣ ማስታወሻነቱም አሕዛብ ለነበረው ሰው አስፈላጊ ምልክት ነበረ ። እንዲሁም ለአማኞች የተሰጠው ጥምቀት ለደኅንነታችን ምልክት እንጂ ደኅንነትን የምናገኝበት ሥርዓት አይደለም ። ቢሆንም በብሉይ ኪዳን ዘመንም ሆነ በአዲስ ኪዳን ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ከዓለም

ከፋት የተለዩ መሆናቸውን ያውቁ ዘንድ አስፈላጊ ነው ። መገረዝ ለአብርሃም ወይም ለአይሁዶች ከዚያም በላይ አሕዛብ ለነበሩት ሰዎች የደኅንነት ምሳሌ እንጂ ራሱ ደኅንነት የሚሰጥ አልነበረም ። አብርሃም ጻድቅ ሆኖ ተቆጠረ የተባለው እምነ ሳይ ገረዝ በፊት ነበረ ። በብሉይ ኪዳን ግዝረት በአዲስ ኪዳንም ጥምቀት እንዲፈጸም የተወሰነው ለዚህ ማስታወሻ ነው ። ቆላ. ፪ ፥ ፲፩ ፥ ፲፪ ደግሞ ሮሜ ፬ ፥ ፩ ፲፩

ክርስቶስ በሥጋ በዓለም ውስጥ በነበረ ጊዜ አይሁዶች ምን አሉ ? አሕዛብ የሚድኑት በመገረዝ ብቻ ሳይሆን በመጠመቅ ጭምር ነው ይሉ ነበር ። በዚህም ረገድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኒቆዲሞስ ጋር ሲነጋገር ፥ ሰው ዳግመኛ የሚወለ ደው በውኃ (ማለት በጥምቀት) እና በደም (ማለት በመገረዝ) ሳይሆን በመንፈስ እንዲወለድ ያስፈልጋል ብሎ አስተማረው ። የዮሐንስ ወንጌል ፫ ፥ ፩ — ፯

በብሉይ ኪዳን ዘመን ግን እንግዳ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እንዲተባበር ከፈ ለገ ሥርዓት ፥ ሕግና ፍርድ ለእርሱም ሆነ ለአይሁዶች አንድ ነበር ። ሕጉን ባለማወቁ ምናልባት በስሕተት ኃጢአት ይሠራል ፥ በማለት እግዚአብሔር በደላቸው እንዲሰ ረይ ለሰውየውና ለሕዝቡ ሁሉ አንድ መንገድ አዘጋጀላቸው ። ቄሱ መሥዋዕቱን አቅርቦ ሥርየት አደረገ ፥ ይህም የሆነበት ሁሉ ኃጢአት ያደረገው ሰውዬ ሳያውቅ ነበር እንጂ እያወቀ ስላልነበረ ነው ። ማንኛውም ሰው እያወቀ ኃጢአት ከሠራ ከሕ ዝቡ እንዲወገድና የሞት ፍርድ እንዲፈጸምበት ግዴታ ነበር ። ቄሱ መሥዋዕት ያቀ ረበው ለአንድ ሰው ብቻ ሳይሆን ለሕዝቡ ሁሉ ነበር ፥ ይኸውም ያንድ ሰው በደል በሁሉ ላይ ኩነኔን ስለሚያመጣ ነው ። ኢያሱ ፯ ፥ ፩ — ፳፮ ተመልከት ።

በይተዋር የሆነ ሁሉ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ሊተባበር ሲፈልግ ሦስት ነገሮችን መቀበል ነበረበት ፥ እነርሱም ሥርዓት ሕግና ፍርድ ናቸው ። ተመልከት ፥— ሥርዓትና ሕግ ብቻ ሳይሆን እንደ ሌሎች ፍርድ መቀበል አስፈላጊው ነበር ። ስን ትና ስንት ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚገኙትን መልካም በረከቶች ሲፈልጉ አብረው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለመተባበር ስደት ፥ መከራ ፥ ችግር ስለሚመጣባቸው በረ ከትን ትተው እንደገና ወደኋላ ማለት ወደ ዓለም ፍላጎት ይመለሳሉ ። ማቴዎስ ፲፱ ፥ ፲፮ — ፳፪ ተመልከት ።

## በሕዝቡ መካከል ስላለው እንክርዳድ ።

ወደ እግዚአብሔር የሰገዱት ሁሉ የእርሱ ምርጦች አልነበሩም ፥ በሁለተኛ ነገሥት ፲፯ ፥ ፳፬ — ፵፩ እንደምናገኘው እስራኤላውያን ከተማረኩ በኋላ የአሶር ንጉሥ በእነርሱ ፈንታ ልዩ ልዩ አሕዛብን ተከለ ። ወደ ሰማርያ እንደደረሱ ደግሞ እግዚአብሔር አንበሳዎችን ሰደደባቸው ። ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁ እንደመሆናቸው መጠን እንደ አምላክ አድርገው ሰገዱለት ፥ ሆኖም እንደ በፊቱ ደንባቸው ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለቀድሞ አማልክቶቻቸው ጭምር ሰገዱላ ቸው ። የእግዚአብሔርን ቁጣ ቢፈሩም እንኳ የሐሰት አማልክቶቻቸውን ቁጣም ከመፍራት አልተመለሱም ነበር ።

አይሁዶች እንዲህ ይሉ ነበር ፡ እነዚህ ሰዎች ያመኑ አናብስትን ስለፈሩ ነው በማለት «አናብስት ከሐዲዎች» ብለው ጠሩአቸው ።

እርግጥ ነው ፡ ሰው ሲጨነቅ ችግሩ እንዲቀነስለት ለማመን ፈቃደኛ ይሆናል ። ነገር ግን ሕይወቱ ያልተስተካከለ ሊሆን ይችላል ። እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ማንኛውም እንግዳ ሰው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በእውነት ለመተባበር ፈቃደኛ ከሆነ ለበረከት ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ለጊዜው ተወስኖ የመለየት አምሮት ሳያድርበት ለበረከትም ሆነ ለስደት ለአሁንም ሆነ ለዘለዓለም መተባበር ግድ አለበት ።

## እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለምን እንደመረጠ ።

እግዚአብሔር አብርሃምን በመምረጥ ለራሱ የተለየ ሕዝብ እንደሚያደርገው ቃል ኪዳን ገባለት ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ይህን ቃል ኪዳን ለአብርሃም ሲገባለት የቀሩትን ሕዝቦች ችላ ማለቱ ሳይሆን እስራኤላውያን የእግዚአብሔር መልእክተኞች በመሆንና መልክም ምስክርነት በማሳየት ለአሕዛብ ብርሃን እንዲሆኑ ነበር ።

«እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ
ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ።» ኢሳ. ፵፱ ፡ ፮

እስራኤላውያን ሁለት ስጦታዎች ተሰጥቶአቸዋል ። የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ነው ። በሮሜ ፫ ፡ ፪ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ እንደተሰጡአቸው ሲገልጽ በሮሜ ፱ ፡ ፭ ደግሞ ክርስቶስም በሥጋ ከእነርሱ ወገን የመጣ መሆኑን ጳውሎስ ያሳስበናል ።

እስራኤላውያን እነዚህን ስጦታዎች ከተቀበሉ በኋላ ለዓለም ሕዝብ እንዲያደርሱ ይፈለግባቸው ነበር ። በኢሳይያስ ፶፮ ፡ ፩ — ፰ እግዚአብሔር ለአሕዛብ የሰጣቸው የተስፋ ቃል አለ ። ይኸውም ኪዳኑን ቢጠብቁና እግዚአብሔር የሚደሰትበትን ነገር ቢያደርጉ እንደ እስራኤላውያን እንደሚመለከታቸው ግልጥ ነበር ። ይህም መሥዋዕታቸው ተቀባይነት እንደሚያገኝ ጸሎታቸው እንደሚሰማ ያረጋግጥልናል ። የእግዚአብሔር ቤት ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ነው ። ኢየሱስ ክርስቶስ የጸሎት ቤት የነበረውን የአባቱን ቤት እስራኤላውያን የንግድ ቤት ስላደረጉት እንደ ወቀሳቸው መገንዘብ ያስፈልጋል ። ማቴ. ፳፩ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫

## ቃል ኪዳን መግባት ።

አሕዛብ እንዴት የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን ይችላሉ ? ከአሕዛብ መካከል አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ለመተባበር ቢፈልግ አንድ ሥርዓት ፡ አንድ ሕግ ፡ አንድ ፍርድ መቀበል ነበረበት ። በዘኁልቁ ፲፭ ፡ ፲፬ — ፲፮ ለአሕዛብ የተለየ ሕግ እንደሌላቸው ያሳስበናል ።

የፋሲካንም በዓል ለማክበር ከፈለገ መገረዝ ነበረበት ። ግዝረት እግዚአብሔር ለአብርሃም ለሰጠው ቃል ኪዳን ምልክት ነበር ። ዘፍ. ፲፯ ፡ ፱ — ፲፬ ግዝረት እያንዳንዱ አይሁዳዊ ከዓለም እርኩሰት ሁሉ ተለይቶ ለእግዚአብሔር እንዲኖር የተሰጠ

ማስታወሻ ነው ። ይህም ማስገንዘቢያ ለአሕዛብም ያስፈልግ ነበር ። በዚህ አንጻር በአዲስ ኪዳን ለክርስቲያኖች የተሰጠው ማስገንዘቢያ ጥምቀት ነው ። መገረዝ ለአብርሃም ጻድቅነት የሚሰጥ አልነበረም ። የግዝረትንም ሥርዓት የወሰደው በእግዚአብሔር አምኖ ጽድቅም እንደሆነ ከተቈጠረለት በኋላ ነው ። እንደዚሁም ከመንን በኋላ የም ንጠመቅ ስለሆነ ጥምቀት አያድነንም ። ይሁን እንጂ በብሉይ ኪዳን የግዝረትም ሆነ በአዲስ ኪዳን የጥምቀት አስገንዛቢነት ከዓለም ተለይተን ለጌታ በመገዛት እንድንኖር የተሰጠ ምልክት ነው ። ቆላ. ፪ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡ ሮሜ ፮ ፡ ፩ ፲፩ አይሁዶች አሕዛብ መጠመቅ ብቻ ሳይሆን መገረዝም ጭምር አለባቸው ብለው አስተማሩ ። በዚህ ረገድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኒቆዲሞስ ጋር ሲነጋገር ሰው ዳግመኛ መወለድ የሚገባው ከውኃ ማለት (በጥምቀት) ና በደም ማለት (በመገረዝ) ሳይሆን በመንፈስ እን ዲወለዱ ያስፈልጋል በማለት አስተማረ ። ዮሐ. ፫ ፡ ፩ — ፰

ልናስተውለው የሚገባ ዋና ነገር በብሉይ ኪዳን አንድ አሕዛብ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ለመተባበር ቢፈልግ ለሕጉና ለሥርዓቱ ለመገዛት ሐሳቡን መቁረጥ አለበት ። ሕጉ ወይም ደንቡ ለአይሁድ ሆነ ለአሕዛብ አንድ ነው ። ዘኍ. ፲፭ ፡ ፲፬ ፲፮ ይሁን እንጂ ለእስራኤላውያን ሁሉ ይህ ግልጽ አልነበረም ። ቢሆንም እነርሱ በግ ብፅ እንግዶች ሆነው ሳለ በሰው አገር መሆን ያለውን ችግር ስለሚያውቁት እነዚህ አዲስ አማኝ በሆኑት አሕዛብ እንዳይታዘዙ ነግረዋቸው ነበር ። አሕዛብ የሆነው ሰው የእግዚአብሔርን ሕግና ሥርዓቱን ሲያጠና ብዙ ጊዜ አብሮት እንደቆየው እንደ እስራኤላዊው ሊያውቅ አይችልምና በቀላሉ ይሳሳታል ። ይህም ከሆነ ካህኑ ለሕዝቡ ኃጢአት ማስተሰርያ ያቀርባል ። ከማኅበርተኞቹ ውስጥ አንዱ ኃጢአት ቢሠራ ቤተ ሰቡና አባል የሆነበት ቤተ ክርስቲያንም እንደሚጎዳ ማስታወስ ጠቃሚ ነው ። የሐዋ. ሥራ ፭ ፡ ፩ — ፲፩ ፤ ኢያሱ ፯ ፡ ፩ — ፳፮ ከዚህ ጋር መገንዘብ የሚገባን አንድ ሰው ኃጢአት መሆኑን እያወቀ በድፍረት ቢሠራ ኃጢአቱ በመሥዋዕት ይቅር አይባልለትም ። ባለማወቅ ሳይሆን በማወቅና በድፍረት ስለሠራ ከሕዝቡ ተወግዶ የሞት ፍርድ ይፈረድበታል ። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ኅብረት ከፈለገ እንደ ጸሎት መሥዋዕትና የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ብቻ ሳይሆን ኃጢአት ቢሠራ ፍርድም እንዳለበት ማወቅ ይገባዋል ። እንደዚሁም በዘመናችን የምንኖር ክርስቲያ ኖች ከእግዚአብሔር እጅ በረከት መቀበል ብቻ ሳይሆን ቅጣቱንም በደስታ መቀበል ይገባናል ።

<u>አፋዊ ክርስቲያን</u> ።

የእግዚአብሔርን ስም የሚጠሩት ሁሉ እውነተኞች አማኞች ናቸው ማለት አይቻልም ። በሁለተኛ ነገሥት ፲፯ ፡ ፳፬ — ፵፩ በእስራኤላውያን ምትክ በሰማርያ እንዲኖሩ የተላኩት አሕዛብ ባለመታዘዛቸው አንበሶች ተሰደዱባቸው ። በዚህም እግዚአብሔር እንደ ተቆጣቸው ለመረዳት ቻሉ ። ስለዚህም የአሶር ንጉሥ ሄዶ የሚያስተምራቸውን ካህን ሰደደላቸው ። ካህኑም ከሰጣቸው ትምህርት ጋር የቀድሞ

ሃቸን ጣዖታት በማጣመር አቀላቅለው ማምለክ ጀመሩ ። በእርግጥ የእግዚአብሔርን ቁጣ ፈርተው ነበር ። ይሁን እንጂ ፍርሃታቸው የቀድሞ ጣዖት አምልኮአቸውን እስከመተው አላደረሳቸውም ። እስራኤላውያንም እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ስም የሚጠሩትና አማኝ የሚመስሉት የአናብስት ፍርሃት ይዟቸው ነው በማለት ይዘብቱባቸው ነበር ።

አሁን ብዙ ጊዜ ሰዎች ችግር ሲደርስባቸው ወደ እግዚአብሔር ይሮጣሉ ። ችግራቸው ሲያልፍ ግን የኃጢአተኛነት ኑሮአቸውን ይቀጥላሉ ። እንደ እነዚህ ያሉትን ሰዎች አፋዊ ክርስቲያን እንጂ እውነተኛ አማኝ ብለን አንጠራቸውም ። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር የኖሩት አሕዛብ ሊያደርጉት የሚገባ ሌላ ነገር ነበር ። ያውም እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ በቃል ኪዳኑ ሥር መኖር ነበር ።

## ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ።

ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፦ ፪ኛ ነገሥት ፲፱ ፥ ፩ — ፲
ኤርምያስ ፴፰ ፥ ፩ — ፲፫
የሐዋርያት ሥራ ፰ ፥ ፳፮ — ፵
፩ኛ ነገሥት ፲ ፥ ፩ — ፲፫

### ጥያቄዎች

1. ንጉሥ ሕዝቅያስን የአሶሩ ንጉሥ ባስፈራራው ጊዜ መልእክተኛውን ወዴት ላከ ? ______
2. ቲርሐቅ የኢትዮጵያውን ንጉሥ ምን አደረገ ? ______
3. ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በሚመለከት ጉዳይ የኤርምያስ ትንቢት ምን ነበር ? ______
4. አቤሜሌክ ኢትዮጵያዊው ኤርምያስን ከጉድጓድ እንዴት እንዳወጣው ግለጽ ። ______
5. እግዚአብሔር የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን ስለ አደረገው ነገር የሰጠው ምክንያት ምን ነበር ? ______
6. ፊሊጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ሊገናኝ የመጣው ከየት ነበር ? ______
7. የትኛውን የመጽሐፍ ክፍል ያነብ ነበረ ? ያልተረዳው ምን ነበር ? ______

## ኢትዮጵያና መጽሐፍ ቅዱስ ።

ኢትዮጵያ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል ። በጣም የታወቀውም ጥቅስ በመዝሙረ ዳዊት ፷፯ (፷፰) ፥ ፴፩ የተመለከተው ነው ። ይህም ጥቅስ ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ከሚገዙት ሰዎች ወገን መሆኗን ያሳስበናል ።

ኢትዮጵያ የሚለው ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዘኁልቁ ፲፪ ፥ ፩ ላይ ነው ። በዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሙሴ ኢትዮጵያዊት ሚስት እንደነበረችው እናነባለን ። ማርያምና አሮን በዚህ ያልተደሰቱ ቢሆኑም እግዚአብሔር አልሰማቸውም ። ከዚህ ሌላ የኢትዮጵያ ወታደሮች የአሶር ንጉሥ ሕዝቅያስን በኢየሩሳሌም ሊወጋ በተነሣ ጊዜ እርዳታ አድርገዋል ። የኢትዮጵያ ወታደሮች ከአሶርያውያን ወታደሮች ጋር ውጊያ ገጠሙ ፥ ኢትዮጵያውያን በውጊያው በማሸነፍ ኢየሩሳሌምን አስለቀቁ ። እግዚአብሔር ይህችን ኢትዮጵያ የምትባለውን አገር እንደሚወዳት የሚያሳስቡ ሦስት ታሪኮች አሉ ። እነዚሁም የንግሥት ሳባ ታሪክ ፥ በጉድጓድ የተጣለው የኤርምያስ ታሪክና የጃንደረባው ታሪክ ናቸው ።

## ንግሥት ሳባ ።

የንግሥት ሳባን ታሪክ የምናገኘው በ፩ኛ ነገሥት ፲ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መምጣቷን ተናግሮላታል ። በዚህም ኢየሱስ ከሰሎሞን እጅግ የሚበልጥ ሲሆን ወደ እርሱ ባለመምጣታቸው ፈሪሳውያንን ወቅሶአቸዋል ።

ንግሥት ሳባ ስለ ሰሎሞን ዝና በሰማች ጊዜ ሽቱና እጅግ ብዙ ወርቅ የከበረም ዕንቁ አስጭና ከታላቅ ጓዝ ጋር ወደ እርሱ ሄደች ። ንግሥት ሳባ በእርግጥ ለስጦታ ወርቅ ይዛ የሄደች እንኳን ቢሆን እርሱ ብዙ ወርቅ ስላለው እንደ ትልቅ ነገር አልቆጠረውም ። ለሰሎሞን ትልቁ የነበረው ስጦታ ግን ሽቱ ነበር ። ሉቃስ ፯ ፡ ፴፯ — ፶ እና ፳ ፡ ፯ — ፲ አንብብ ። ኢየሱስ ራሱን ከሰሎሞን ጋር ሲያወዳድር ሽቱው ምን ያስስባል ? ትክክለኛ መሥዋዕትና ጸሎትን ነው ። ለኢየሱስ ገንዘብ ልንሰጠው አንችልም ። ገንዘብ የሚሰጠን እርሱ ነውና ፡ ነገር ግን ፍቅራችንንና ጸሎታችንን ልናቀርብ እንችላለን ።

## አቤሜሌክና ኤርምያስ ።

ነቢዩ ኤርምያስ ትልቅ መልእክት እንዲያደርስ ተነግሮት ነበር ። ለእስራኤላውያን ጠላት መጥቶ የኢየሩሳሌምን ከተማ እንደሚይዝ መንገር ነበረበት ። ሊያመልጡም የሚችሉበት መንገድ እጃቸውን ለባቢሎናውያን እጅ አሳልፈው በመስጠት ብቻ ነበር ። ኤርምያስም ይህንን መልእክት ሲናገር ማንም ያደመጠው አልነበረም ። ንጉሡ ሰዴቅያስ ኤርምያስ በእስር ቤት እንዲቆይ ትእዛዝ አስተላለፈ ። በእስር ቤት ሳለ ውኃ በለው ጉድጓድ መቆየት ነበረበት ። ይሁን እንጂ ኤርምያስ በተጣለበት ጊዜ በጉድጓዱ ጭቃ እንጂ ውኃ አልነበረም ።

ይህ በዚህ እንዳለ እግዚአብሔር በንጉሥ ሴዴቅያስ ቤት ኢትዮጵያዊ የሆነ ብሪያውን አስቀምጦ ነበር ። ስሙም አቤሜሌክ ሲሆን ትርጓሜውም «የንጉሥ ባለሟል» ማለት ነው ። ሆኖም አቤሜሌክ የንጉሡ አገልጋይ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርም ባሪያ ነበር ። የኤርምያስን መታሰር በሰማ ጊዜ ከንጉሡ ፈቃድ ጠይቆ አሸለቀቀው ። አቤሜሌክ እንዴት አስተዋይ እንደነበር ተመልከት ። ወደ ጉድጓድ አል

ሮጠም ፥ ነገር ግን ኤርምያስን የሚያወጣበትን መንገድ ፈለገ ። አዎን ገመድ ያስፈልግ ነበር ። ኤርምያስ በጭቃው ውስጥ ስለነበር በገመድ ብቻ ሊያወጣው ቢሞክር ሊጎዳ ይችላል ። ስለዚህ አሮጌ ጨርቅና አላቂውን ልብስ በገመድ ከብብቱ በታች እንዲያደርግ ነገረውና በገመድ ጎትተው ከጉድጓድ አወጡት ። በከተማውም የሚበላ ነገር አልነበረም ። ይሁን እንጂ አቤሜሌክ እንዲህ ባለ ሁኔታ የኤርምያስን ሕይወት ሊያድን ቻለ ።

እግዚአብሔር አቤሜሌክን አልረሳውም ፥ የኤርምያስ ትንቢት ሲፈጸም ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ ስትወድቅ ሕይወቱ እንደሚተርፍ ነግሮት ነበር ። ኤር· ፴፱ ፥ ፲፭ — ፲፰

## ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ፊልጶስን ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የሚያነበውን መጽሐፍ ትርጉም እንዲያብራራለት እንደላከው እናነባለን ። ከብዙ ዓመታት በፊት ንግሥት ሳባ ኢየሩሳሌምን እንደጎበኘች ይህም ጃንደረባ ኢየሩሳሌም ድረስ መጥቶ ነበር ። ጃንደረባው በሰረገላው ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲያመራ መጽሐፍ ቅዱሱን ያነብ ነበር ። በእርግጥ አዲስ ኪዳን ያኔ ገና ስላልተጻፈ ብሉይ ኪዳን ይዞ ነበር ። ገና የእምነትን ትርጉም ያልተረዳ ስለነበር ኢሳይያስ ስለራሱ ይሆን ወይም ስለ ሌላ ሰው መናገሩን አላወቀም ። የሚያነበውም ክፍል ኢሳይያስ ፶፫ ፥ ፯ ፥ ፰ ያለውን ነበር ።

ቀናም ብሎ አሻቅቦ ሲመለከት ፊልጶስን አየ ። ፊልጶስም ወደ ጃንደረባው ቀረብ ብሎ የምታነበውን በእውነት ታስተውለዋለህን ? አለው ። እርሱም የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል ? አለው ። ፊልጶስም አፉን ከፈተ ፥ ከዚያ መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት ። በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውኃ ደረሱ ። ጃንደረባውም እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው ? አለው ። ፊልጶስም በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው ። መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ አለ ። ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ ። ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም ። ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ወደ ሌላ ቦታ ወንጌልን እንዲሰብክ ጠርቶ ወሰደው ። ከዚህ በኋላ ጃንደረባው ምን አደረገ ? በደስታ በመሞላት መንገዱን ቀጠለ ። አሁን እንግዲህ ክርስቲያን ሆነ ። ሕይወቱ ተለወጠ ። አብ በስሙ የላከው መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምረዋል ። መጽሐፉንም ሲያነብ ይገልጥለታል ። ዮሐ· ፲፬ ፡ ፳፮

በዚህ ክፍል በማንበብ የምናገኘው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ የእስራኤላውያን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ፥ የግብፅ ፥ የባቢሎን ፥ የግሪክና የሮምም እንደ ሆነ ነው ። የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እነዚህ አገር ሰዎች ሊደርስ የቻለው በእስራኤላውያን በኩል ነው ።

## <u>ሞዓባዊቱ ሩት ።</u>

ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፡— ዘፍጥረት ፲፱ ፡ ፴ — ፴፰
ዘዳግም ፳፫ ፡ ፫ — ፮
መሳፍንት ፫ ፡ ፲፪ — ፲፱
መጽሐፈ ሩት

### <u>ጥያቄዎች</u>

1. የሎጥ ልጆች ከአባታቸው የወለዱዋቸውን የሁለቱን ወንዶች ልጆች ስም ጻፍ ። ____________________
2. ሞዓባውያን ወደ እስራኤል ጉባኤ እንዳይገቡ የተከለከሉት ለምንድር ነው ? ____________________
3. የእስራኤል ልጆች የሞዓብን ንጉሥ ለስንት ዓመታት አገለገሉ ? ____________________
4. ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ ።
   የሩት የባልዋ አባት ____________________
   የሩት የባልዋ እናት ____________________
   የሩት የባልዋ ወንድም ሚስት ____________________
   የሩት የመጀመሪያ ባልዋ ____________________
5. ሩት ፪ ፡ ፲፩ — ፲፫ ጻፍና በቃልህ አጥና ። ____________________

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የመረጣቸው ለዓለም ሁሉ መልእክተኞቹ እን ዲሆኑ ነው ። የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በአንተ ይባረከሉ ሲል ለአብርሃም ቃል ኪዳን የገባለት ለዚህ ነው ። ዘፍ. ፳፪ ፡ ፲፰ በእርግጥ ኢየሱስም በሥጋ ወደ ዓለም የመ ጣው ከእስራኤል ዘር ነው ። ሮሜ ፱ ፡ ፭ ኢየሱስም በሥጋ ወደ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ብዙዎቹ የዓለም ሕዝቦች ተባርከውበታል ። ከእነዚህም ከተባረኩት ሕዝቦች አንዱ ሞዓብ ነበር ።

የሞዓባውያን አባት የሆነው ሞዓብ ለሎጥ ከሴት ልጁ የወለደው ዘሩ ነው ። የሎጥ ዘሮች ከጨው ባሕር በስተምስራቅ በኩል ይኖሩ ነበር ። እስራኤላውያንም ከግብፅ ወጥተው በኢያሱ መሪነት ወደ ከነዓን በሚጓዙበት ጊዜ በሞዓብ አገር አል ፈው እንዳይሄዱ ከለከሉአቸው ። መሳ. ፲፩ ፡ ፲፯ በለዓምንም እስራኤላውያንን እንዲ ረግምላቸው ጠየቁት ። ዘኍ. ፳፪ ፡ ፩ — ፮ በለዓምም እስራኤልን ሊረግም ሲሄድ አህያዋ ዘለፈችው ። ዘኍ. ፳፪ ፡ ፳፩ — ፴ ይህም እስራኤላውያን ከግብፅ ተነስተው ወደ ከነዓን ሲያመሩ በጉዞቻቸው በመርዳት ፈንታ ሊረግሙአቸውና ሊያጠፉአቸው ፈለጉ ።

## የሩት ታሪክ ።

በመሳፍንት ዘመን እስራኤላውያን እንደ ሞዓባውያን ያሉ ብዙ ጠላቶች ሲኖራቸው እግዚአብሔር ኢሁድ የተባለውን መሪ በማስነሣት አዳናቸው ። በፓለስቲና ታላቅ ረሃብ በሆነ ጊዜ አቤሜሌክና ባለቤቱ ኑኃሚን መሐሎንና ኬሌዎን ከተባሉት ሁለት ልጆቻቸው ጋር ወደ ሞዓብ አገር ሄዱ ። እነዚህ ልጆች የሞዓባውያን ሴቶች ልጆችን አገቡ ። መሐሎን ሩትን አገባ ፤ ኬሌዎን ዖርፋንን አገባ ። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ መሐሎንና ኬሌዎን እንደሞቱ፥ አቤሜሌክም ተከትሎ ሞተ ። እንደዚህ ባለ ሁኔታ ሦስቱ ሴቶች ያለ አንዳች ረዳት ቀሩ ።

ስለዚህ በከነዓን ቀድሞ ይኖሩበት ወደ ነበረው ወደ ቤተ ልሔም ከተማ ለመመለስ አሰቡ ። ኑኃሚን የልጆቿን ሚስቶች በሞዓብ ከአገራቸው ሕዝብ ጋር እንዲቆዩ አበረታታቻቸው ። ዖርፋ ስትመለስ ሩት ግን አገርዋን ፣ ጓደኞቿን ፣ ዘመዶቿንና አማልክቶችዋን ሁሉ ጥላ

> ወደምትሄጂበት እሄዳለሁና
> በምታድሪበትም አድራለሁና
> ሕዝቦችሽ ሕዝቦቼ
> አምላክሽም አምላኬ ይሆናል አለቻት ።

እንደሴት ሊኖሩ ይችላሉ ? ሩት ከኑኃሚን ጋር ወደ ቤተ ልሔም ሄደች ። ከዚያም ሩት ቃርሚያ ለመቃረም ወደ ሜዳ ወጣች ። እንዲህም ባለ መንገድ ስትሠራ እግዚአብሔር በጣም ባረከት ። በዔዝም ወደሚባል ሰው እርሻ መጣች ። ይህም ሰው የኑኃሚን ዘመድ ነበረ ። የቅርብ ዝምድና ቢኖራቸውም በሕጋቸው መሠረት ይህ ሰው ሩትን በማግባት አቤሜሌክ በረሃቡ ዘመን ሊሸጥ ያቀደውን መሬት ማስቀረት ይችል ነበር ። ይህ የቅርብ ዘመድ ባለመፍቀዱ በዔዝ መብቱን እንዲወስድ ተደረገ ። ሩት በዔዝን አገባች ። ልጅም ወለዱ ። የልጁም ስም ኢዮቤድ ነበር ። ኢዮቤድም የእሴይ አባት ሲሆን እሴይም የዳዊት አባት ነው ። ይህም ከዳዊት ዘር የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ከሩት ዘር መሆኑ ነው ። ማቴ. ፩ ፣ ፫

## ከታሪኩ የምናገኘው ትምህርት ።

ሞዓባይቱ ሩት የክርስቶስ ቤተሰቦች ከሆኑት ሰዎች እንደ አንዷ የምትቆጠር ናት ። ስለዚህ ራኬብ የበዔዝ እናት የአገራቸውን ሰው በመለየት እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር ። ኢያሱ ፪ ፡ ፰ — ፲፬

በዔዝ ሩትን እንዲህ አላት ፦ «እግዚአብሔር እንደ ሥራሽ ይስጥሽ
ከክንፉም በታች መጠጊያ እንድታገኝ
በመጣሽበት በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ዘንድ
ደመወዝሽ ፍጹም ይሁን ።» ሩት ፪ ፣ ፲፪

ከእስራኤላውያን ከሚጠበቁት ተግባሮች አንዱ ለቀረው ለዓለም ሕዝብ በረከት መሆን ነው ። በእግዚአብሔር ላይ ያመጸው ሞዓብ እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ በማግኘት በረከቱን ለመቀበልና ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፏዋ ሥር እንደምታስጠልል በእስራኤል አምላክ ክንፍ ሥር መጠጊያ ሊያገኝ ይችላል ።

ይሁን እንጂ ማቴ ፳፫ ፡ ፴፯ — ፴፱ ስለ እስራኤል ምን ይነግረናል ? ________

## የዮናስ ትንቢት ።

<u>ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፡—</u> ዮናስ ምዕራፍ ፩ እና ፪
መዝሙር ፻፴፰ (፻፴፱) ፡ ፯ — ፲፪
ማቴዎስ ፲፪ ፡ ፴፰ — ፵፩

ጥያቄዎች

1. በካርታው ላይ እነዚህን ቦታዎች አመልክት ፡—
ነነዌ ፡ ጠርሴስ ፡ ኢዮጴ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሮሜ ፡ ትልቁ ባሕር ።



2. ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት ሲሸሽ ለምን ወደ መርከቢቱ ታችኛ ክፍል ወረደ ?
3. የባሕሩን ማዕበል ለማስታገስ ሰዎቹ ያደረጉትን ሦስት ነገሮች ጻፍ ።
ሀ. ________
ለ.
ሐ. ________
4. የነነዌ ሰዎች በፍርድ ዕለት ባላመኑት ሰዎች ላይ ለመፍረድ ይችላሉ ?

________

## ለዓለም ሕዝብ የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆነችው እስራኤል ።

እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘር እባርከለሁ ሲል ለአብርሃም በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት በዓለም ያሉትን ሰዎች እባርከለሁ ማለቱ ነው ። ዘፍ. ፲፪ ፣ ፪ እና ፳፪ ፡ ፲፯ — ፲፰ እግዚአብሔር ከአይሁድ ጋር ለሚኖረው ሕዝቡ ከመልካም ነገር እንደማይጎድልባቸው ቃል ኪዳን ሰጥቶታል ። ዘኁ. ፲፭ ፣ ፲፬ — ፲፮ ለምሳሌም ያህል ከተመረጡት ወገኖች እስራኤላውያን ያልሆኑት እነሞዓባውያን የእግዚአብሔርን በረከት ከእስራኤላውያን እኩል ተቀብለዋል ። ዘዳ. ፪ ፣ ፱ እና መጽሐፈ ሩት ።

## በነነዌ የዮናስ መልእክተኛነት ፣—

እግዚአብሔር አይሁዳዊ የነበረውን ዮናስን ለነነዌ ሕዝብ መልእክተኛ አድርጎ መረጠው ። የነነዌ ሕዝቦች ኃጢአት ስለሠሩ እግዚአብሔር ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ ስለፈለገ ዮናስን ላከው ። ብዙዎቹ ሰዎች እግዚአብሔር ሲልካቸው እምቢ እንደሚሉ ሁሉ ዮናስም ለፈቃዱ ታዛዥ ሆኖ አልተገኘም ። በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን ጠራው ። ሙሴ ግን በመጀመሪያ ጊዜ ታዛዥ ሆኖ መገኘት አዳገተው ። ዘጸ. ፬ ፣ ፲፫ ኤርምያስ የተባለውም ነቢይ እግዚአብሔር ወደሚልከው ሕዝብ ወዲያው ሄዶ መናገር አልደፈረም ። ኤር. ፩ ፣ ፮ ሙሴና ኤርምያስ በለመታዘዛቸው ከእግዚአብሔር ሲከራከሩ ዮናስ ግን ከነጭራሹ ኮበለለ ፤ ሙሴም ፈርዖን ፊት ከመቅረብ ሸሽቶ ወደ ሲና ተራራ ሄደ ። ዘጸ. ፪ ፣ ፲፭ ኤልያስም ኤልዛቤልን ፈርቶ ኮበለለ ። ፩ኛ ነገ. ፲፱ ፣ ፫ — ፰ ዳዊት ከራሱ ልጅ ከአቤሰሎም ሸሸ ። ፪ኛ ሳሙ. ፲፭ ፣ ፲፫ — ፲፰ ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር ሸሽቶ ማምለጥ የሚችል ማነው ? በመዝሙረ ዳዊት ፻፴፰ (፻፴፱) ፣ ፰ ላይ ሰው ወደ ሲኦል እንኳን ቢወርድ ከእግዚአብሔር ሊያመልጥ እንደማይችል እናነባለን ። ኢየሱስ ወደ ሲኦል ወረደ ። (የሐዋ. ሥራ ፪ ፣ ፳፬ — ፴፪) በወኅኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው ። ፩ኛ ጴጥ. ፫ ፣ ፲፰ — ፳

ስለዚህ ዮናስ ወደ መርከቡ ውስጠኛ ክፍል የገባ ቢሆን እንኳን የእግዚአብሔር ዓይን ወደ እርሱ ሆኖ ይመለከተው ነበር ። ዮናስም በመርከቢቱ ላይ ታላቅ ነፋስ የመጣው በእርሱ አለመታዘዝ ምክንያት መሆኑን ተናገረ ። በእግዚአብሔር ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው ። የዮናስ አለመታዘዝ በመርከበኞቹ ላይ ችግር ፈጠረ ። መርከበኞቹ ፈሩ ። እያንዳንዱም ወደ አምላኩ ጮኸ ። መርከቢቱም እንድትቀልልላቸው በውስጥዋ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕር ጣሉት ። ወደ ምድርም ሊመለሱ አጥብቀው ቀዘፉ ። ዳሩ ግን ባሕሩ እጅግ አብዝቶ ይናወጥባቸው ነበር ። ይህ ሁሉ አድራጎታቸው የእግዚአብሔርን ዓላማ አላቃወሰውም ። እግዚአብሔርም ዮናስን የሚውጥ ትልቅ ዓሣ አሰናዳ ።

## ዮናስ በመፍራቱ የደረሰበት ችግር ።

ዮናስ ከተኛበት ሲነቃ ወደ አምላኩ መጸለይ አቃተው ። አዎን ዮናስ እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ሰው ነበረ ። (፩ ፣ ፱) ነገር ግን ፍርሃቱ እግዚአብሔ

ርን እሺ ብሎ የሚያገለግል ሳይሆን አለመታዘዝን ስለሚያሳይ ትክክል አልነበረም ። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ። ይህም ፍርሃት እግዚአብሔርን መታዘዝና ማገልገል ነው ። መዝ. ፻፲ (፻፲፩) ፣ ፲

የዮናስ በዓሣ ሆድ ውስጥ ።

ዮናስ በለመታዘዙ ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ ። በመርከበኞቹም ላይ ችግር ጣለባቸው ። ወደ ባሕርም ሲጥሉት እግዚአብሔር የሚ ውጠውን ዓሣ አዘጋጀለት ። በዚህም እግዚአብሔር የሰውን አለመታዘዝ ወደ እርሱ ፕላን እንደሚቀይረው እንመለከታለን ። የዮናስ በዓሣ ሆድ ውስጥ ለሦስት ቀናት መቀመጥ ክርስቶስ በመቃብር ሦስት ቀን እንደቆየ የሚያሳስብ ነው ። ይህም ምል ክት የተሰጠው ለአይሁዶች ነበር ። ዮናስ በዓሣ ሆድ ውስጥ እንዳልቀረ ሁሉ እንዲ ሁም ክርስቶስ ከመቃብር ሞትን ድል አድርጎ ተነስቶአል ።

የዮናስ ጸሎት ።

ዮናስ በመሸሽ ላይ በነበረበት ጊዜ ተደብቆ ተኛ እንጂ ጸሎት አላደረሰም ። መሸሹን ሲያቆም ግን ጸሎት ጀመረ ። ዮናስ ፪ ፣ ፩ — ፲ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ዮናስ ወደ ባሕሩ ሲጣል የነበረበትን የተስፋ መቁረጥ ሁኔታና ምሬት ይገልጻል ። በባሕሩ ውስጥ ያሉት አንዳንድ ሣሮች እስኪጠመጠሙበት ድረስ ወደ ውኃው ጥልቅ ወረደ ። የሞተ መስሎ ታየው ። እንዲህም ባለ ተስፋ በሌለው ሁኔታ ላይ ሳለ ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ጀመረ ። የኢየሩሳሌምን መቅደስ እንደገና የሚያይ አልመሰለውም ። ታሪኩ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ ከግራና ከቀኝ የተሰቀ ሉትን የሁለት ወንበዴዎች ሁኔታ ያሳስበናል ። ወንበዴዎቹ ምንም እንኳን በሞት አፋፍ ላይ ቢሆኑም ኃጢአታቸውን ለመናዘዝ ጊዜ ነበራቸው ። አንደኛው በጊዜው ተጠቅሞበት ሲድን ሌላው ግን አሻፈረኝ በማለት የኃጢአት ይቅርታ ሳያገኝ ሞተ ። ሉቃስ ፳፫ ፣ ፴፱ — ፵፫

ቁጥር ፯ — ፱ ዮናስ ወደ እግዚአብሔር የጮኸው በፈዘዘና ራሱን በደንብ ማወቅ በተሳነው ጊዜ ነበር ። ምንም እንኳን አፈፍኪኹ ያነሰ ቢሆንም ከባሕር ሥር ከጥልቁ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ደርሶአል ። ብዙ ጊዜ እኛም እንደ ዮናስ መጸለይ ሲሳነን በውስጣችን የሚያድረው መንፈስ ቅዱስ ይጸልይልናል ። ሮሜ ፰ ፣ ፳፮ በሕመምና በድካም ያልጠየቅነው ነገር ቢኖር በእኛ ፈንታ ሆኖ ይለምንልናል ። የዮናስ ጸሎት ኑዛዜን ጭምር ያዘለ ነበር ። ዮናስ ለጣዖት የሚሰጠውን ክብር ያህል እንኳን ለእግዚአብሔር አልሰጠም ። (ኢ.ሳ. ፵፬ ፣ ፱ — ፳) ጣዖት አይንቀሳቀስም ፤ አይናገርም ፣ አይሠራም ፣ የሰማዩ አባታችን ግን ይሰማል ፣ ያያል ፣ ያዝንልናል ፣ ያፈ ቅረናል ፣ እንድንታዘዝለትም ይፈልግብናል ። ዮናስም ከተናዘዘና ከጸለየ በኋላ ለእ ግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት አቀረበ ። ወደ ነነዌ በደስታ ያላንዳች ቅሬታ ሄዶ ለመስበክና በዚህም ለእግዚአብሔር ታዛዥነቱን ለማሳየት ወሰነ ። (የሐዋ. ሥራ. ፭ ፣ ፵ — ፵፪) ሐዋርያት ግርፋት ደርሶባቸው ነበር ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ስለ ኢየ ሱስ ስም ስለ ደረሰባቸው በደስታ ተቀበሉት ።

የሐዋርያው የጳውሎስን መልእክት ወደ ቆላስይስ ሰዎች አንብብና ደስታ ወይም ምስጋና የሚሉትን ቃላት እየለቀምህ አውጣ ።

## የዛሬይቱ እስራኤል ።

### የድሮው ቀርቶ አዲሱ ተጀመረ ።

ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፦ ፪ኛ ነገሥት ፲፯ ፥ ፩ — ፲፰ ፥ ፳፫ ፥ ፲፰ — ፳፭ ፥ ፲፪
ሮሜ ፲፬ ፥ ፲፫ — ፳፫ ፥ ፲ ፥ ፩ — ፳፩

### ጥያቄዎች

1. የመጨረሻው የእስራኤል ንጉሥ ስም ማን ነበር ? ____________
2. ሰማርያን የያዘው የአሶርያ ንጉሥ ስም ማን ነበር ? ____________
3. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን መጥላታቸውን የሚያሳስብ አራት ነገሮች ጻፍ ።
   ሀ.
   ለ. ____________
   ሐ. ____________
4. የመጨረሻው የይሁዳ ንጉሥ ስም ማን ነበር ? ____________
5. ኢየሩሳሌምን ከበ የነበረውን የባቢሎን ንጉሥ ስም ጻፍ ። ____________
6. የኢየሩሳሌም ሰዎች ከተማቸው በተያዘ ጊዜ ምን ሆኑ ? ____________
7. ሮሜ ፲ ፥ ፲፪ ጻፍና በቃልህ አጥና ____________
8. ጳውሎስ አብርሃምን የሁላችን አባት ብሎ ለምን ጠራው ? ____________

____________

## የአሥሩ ነገድ መጨረሻ ።

ሳኦል የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ነበረ ። ከእርሱም በኋላ የነገሠው ዳዊት ሁለተኛው ንጉሥ ሲሆን ልጁ ሰሎሞን ደግሞ ሦስተኛ ንጉሥ በመሆን በእስ ራኤል ላይ ነግሦአል ። ከሰሎሞን በኋላ የእስራኤል መንግሥት ተከፈለ ። ኢዮርብ ዓም እስራኤል የተባሉትን አሥር ነገዶች ሲገዛ ይሁዳና ብንያም የተባሉትን ደግሞ ሮብዓም ይገዛ ነበር ።

የእስራኤላውያንን ነገሥታት ታሪክ ስናነብ መጽሐፍ ቅዱስ አንዳቸውን እንኳን መልካምና ቅን እንደነበሩ አይናገርም ። የእስራኤል ሕዝቦችም በመሪዎቻቸው የወጡ በመሆናቸው እግዚአብሔርን በመተው ጣዖታትን ማምለክ መረጡ ። (፩ኛ ነገ. ፲፪ ፥ ፳፭ — ፴፫) ጎረቤቶቻቸው የሚያመልኳቸውንም እንደ በዓል ላሉት ጣዖት ይሰግዱ ነበር ። (፩ኛ ነገ. ፲፮ ፥ ፳፱ — ፴፬) የእግዚአብሔር ነቢያት የነበሩትን

የኤልያስንና የኤልሳዕን መልእክት ሰምተን አንታዘዝም ስላሉ በ፪ኛ ነገሥት ፲፯ እንደ ምናነበው ከንጉሣቸው ከሆሴዕ ጋር በአሶር እጅ በምርኮ ወደቁ ። የአሶሩ ንጉሥ ሰል ምናሶር በምትካቸው ሌሎችን ነዋሪዎች በሰማርያ አኖረ ። አሥሩ ነገድ እግዚአብ ሔርን አልታዘዝም ስላሉ እግዚአብሔር ቀጣቸው ። ከዚህ አሳዛኝ ከሆነው ታሪክ ት ምህርት ልናገኝ እንችላለን ። ይኸውም ትምህርት ቤተ ክርስቲያንም ብትሆን በኀጢ አት እየጸናች የምትሄድ ከሆነ እግዚአብሔር ይፈርድባታል ። በኤፌሶን ላለችው ቤ ተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲህ ሲል ጻፈ ።

«እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውን ሥራህን አድርግ አለዚያ እመጣብሃለሁ ፤ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከሥፍራው እወስዳለሁ ።» ራእይ ፪ ፥ ፭

## የይሁዳና የብንያም መማረክ ።

እስራኤል በኃጢአቷ የደረሰበትን በመመልከት ይሁዳም በአመፅ ተግባር መቀ ጠሏ ማንንም ሳያስገርም አይቀርም ።

«ይሁዳም ደግሞ እስራኤል ባደረጋት ሥርዓት ሄደ እንጂ
የአምላኩን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አልጠበቀም ።» (፪ኛ ነገ ፲፯ ፡ ፲፱)

እስራኤል በ፯፻፳፪ ዓ. ዓ. በግዞት ስትወድቅ በ፭፻፹፮ ዓ. ዓ. ከአንድ መቶ ሠላሳ ዓመታት በኋላ ማለት ነው ። ይሁዳ በባቢሎን ንጉሥ በናቡከደነፆር ተማረከች ። ንጉሥዋ ሴዴቅያስን ዓይኑን አውጥተው በምርኮ ወደ ባቢሎን ወሰዱት ።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለአብርሃም በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት በዙፋን ላይ አንድ እስራኤላዊ ተወላጅ እንደማይጠፋ ነግሮታል ። ይህም የተስፋ ቃል ሊጸና የሚችለው በእስራኤላውያን ታዛዥነት ነው ። (፩ኛ ነገ. ፪ ፥ ፬) ሌላው ጽኑ ተስፋ ደግሞ የመሢሕ መምጣት ነው ። እስራኤላውያን በባቢሎን ምርኮ በነበሩ ጊዜ መሢሑ ለመምጣት አልተቻለውም ። ስለዚህም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከባቢሎን ምርኮ ለማውጣት ቂሮስ የተባለውን ንጉሥ አስነሣ ። (ዕዝራ ፩ ፥ ፩ — ፬)

በነህምያና በዕዝራ ከምርኮኞቹ አንዳንዶቹ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። ሌሎቹ ግን ሊመለሱ ያልወደዱት መንገዱ በጣም ሩቅ ስለነበርና በኢየሩሳሌም ኑሮ የሚያ መች ስላልነበረ ሳይሄዱ ቀሩ ። በመጨረሻም ከእነዚህ ከሁለቱ ነገዶች ፈቃደኞች ብቻ የሆኑት እግዚአብሔርን ማገልገል ተማሩ ።

## የድሮው እስራኤል መቅረት ።

እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው አልኖሩም ። ክርስቶስም በመጣ በት ዘመን ሕዝቦቹ የሮም አገር ተገዥዎች ነበሩ ። መሪዎቻቸውም በመንግሥቱ የአስተዳደር ዘዴ ተከፋይ ነበሩ ። በከንፈራቸው እንጂ በእውነትና በመንፈስ እግዚ አብሔርን አያመልኩም ነበር ። ልባቸው ከእግዚአብሔር የራቀ የሰውም ሥርዓት

የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩት ነበር ። (ማቴ ፲፭ ፥ ፩ — ፱) መሢሑም በመጣ ጊዜ አልተቀበሉትም ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር የእምነት መንገድ አሸፈረኝ በማለት ስለራቁ እግዚአብሔር እንደተዋቸው ይናገራል ። ይህንንም ለማብራራት ሐዋርያው የበረሃ ወይራና መልካም ወይራ በማለት ምሳሌ አድርጎ ይናገራል ። ከመልካሙ ወይራ ላይ ቅርንጫፉ ተቆርጦ በበረሃው ወይራ ግንድ ላይ እንደተተከለ ይናገራል ። መልካም ወይራ የተባለው የእስራኤል ሕዝብ ሲሆን የበረሃው ወይራ ደግሞ አሕዛብ ነው ።

ጳውሎስ መልካሙ የወይራው ዛፍ ባለማመን ምክንያት እንደተቆረጠና የበረሃው ወይራ እንደተተከለ እንደዚሁም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እግዚአብሔር የበረሃውን ወይራ ቆርጦ በመጣል መልካሙን ወይራ እንደሚተክ ይናገራል ። ይህም የሚያሳስበን ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር የማትታዘዝ ብትሆን የድሮዎቹን እስራኤላውያንን ይመልሳቸዋል ማለት ነው ።

የእስራኤል ሕዝብ ስለተጣሉ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን ቀረ እንበልን ? እርግጥም በመጀመሪያ ጊዜ የእስራኤላውያን መጣል ጊዜያዊ ነበር ። (ሮሜ ፲፩ ፥ ፪ ፤ ፲፩ ፥ ፲፯ — ፴፪) ሁለተኛ እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች በሥጋ ከእርሱ ዘር የተወለዱት ሳይሆኑ ነገር ግን እንደ አብርሃም እግዚአብሔርን ወድደው አምነው የሚታዘዙቱ ናቸው ።

<u>የዛሬይቱ እስራኤል ተግባር ።</u>

የድሮ እስራኤል ተግባር በአካባቢያቸው ለሚገኙት አሕዛብ ብርሃን መሆን ነበር ። የእግዚአብሔርንም ቃል ለዓለም ሕዝብ እንዲያዳርሱ ተነግረው ነበር ። ከእነርሱም ዘር መሢሕ እንደሚመጣ ተነግሮ ነበር ። እንደተባለውም መሢሑ መጣ ። አልተቀበሉትም ። በመጨረሻም በመስቀል ላይ ቸነከሩት ። በዚያን ጊዜ ለእስራኤል የተሰጠው ትእዛዝ ዛሬም የዛሬይቱ እስራኤል ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ተሰጥቶአል ።

> «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ ፤ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ። እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ ።» ማቴ ፳፰ ፥ ፲፱ ፥ ፳

<u>የክርስቶስ ትእዛዝና በዓለ ሃምሳ (ጰንጠቆስጤ)</u>

ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፥— ማቴ ፳፰ ፥ ፲፯ — ፳
የሐዋ ሥራ ፩ ፥ ፩ — ፰
የሐዋ ሥራ ፪ ፥ ፩ — ፲፩
ዘሌዋውያን ፳፫ ፥ ፱ — ፳፩

## ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ወንጌልን እንዲያስፋፉ ትእዛዝ ሊሰጣቸው የት ሆኖ ነበር ? ________________________

2. በዚህ ትእዛዝ መሠረት ደቀ መዛሙርቱ እንዲሠሩ የተናገራቸው ሦስት ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

   ሀ. ________________________

   ለ. ________________________

   ሐ. ________________________

3. ከትንሣኤው በኋላ ጌታ ለምን ያህል ጊዜ በዓለም ቆየ ? ________________________

   ________________________

4. የሐዋ. ሥራ ፩ ፡ ፰ን በቃልህ አጥናና እዚህ ላይ ጻፍ ።

   ________________________

5. በበዓለ ሃምሳ ዕለት መንፈስ ቅዱስ እራሱን በምን ዓይነት ምሳሌ ለደቀ መዛሙርቱ እንደገለጸ ጻፍ ።

   ሀ. ________________________

   ለ. ________________________

6. በበዓለ ሃምሳ ቀን ሐዋርያት ምን ብለው አስተማሩ ? ________________________

   ________________________

## የክርስቶስ ሞት ።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሞተው ለአይሁዶች ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ለዓለምም ሁሉ ኃጢአት ነው ። (፩ኛ ዮሐ. ፪ ፡ ፪) እግዚአብሔር አይሁዶችን ብቻ ሳይሆን ዓለምን በሙሉ ይወዳል ። (ዮሐ. ፫ ፡ ፲፮) ክርስቶስ በሞቱ በምድር ያሉትን ብቻ ሳይሆን በሰማያት ያሉትን ሁሉ ዋጅቷል ። (ቆላ. ፩ ፡ ፳)

ሰው ካልነገራቸው ሰዎች እንዴት ስለ ክርስቶስ ሊያውቁ ይችላሉ ? እግዚአብሔርስ ካላከቸው ሰዎች እንዴት ብለው ይሄዳሉ ? (ሮሜ ፲ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭) ነገር ግን እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከመስደዱ በፊት እንኳን ትእዛዙን ለደቀ መዛሙርቱ ሰጥቶ ነበር ። እርሱ ያዘዛቸውን ሁሉ እያስተማሩ ደቀ መዝሙር እንዲያደርጓቸው ነበር ። ይህንንም የሰጣቸውን ሥራ በደንብ ለማከናወን እንዲችሉ እስከ መጨረሻ ድረስ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ በማለት ሥልጣንና ኃይል እንደተሰጣቸው አስታወቃቸው ። በዚያ ደቂቃ ይህ የክርስቶስ የሥልጣኑ ኃይል የተሰጣቸው አልመሰላቸውም ። ይህንንም ማወቅ የምንችለው ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ አይሁዶችን ፈርተው በአንድ ቤት በመሰብሰባቸው ነው ። ሆኖም በበዓለ ሃምሳ ቀን ለምስክርነታቸው የሚያስፈልጋቸውን ኃይል ተቀበሉ ።

ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ እየታያቸው አርባ ቀናት ያህል ቆየ ። ከማረጉ በፊት ሁለት ትእዛዛት ሰጣቸው ። ይኸውም ፦

ሀ· በኢየሩሳሌም ፡ በይሁዳ ፥ በሰማርያና እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቹ እንዲሆኑ ፤

ለ· መንፈስ ቅዱስ ሳይወርድ ከኢየሩሳሌም ወጥተው ሥራቸውን እንዳይጀምሩ የሚል ነበር ።

ደቀ መዛሙርቱም ወደ ገሊላ ተመለሱ ። (ማቴ· ፳፰ ፥ ፲፯) ኢየሱስ ካረገ በኋላ የነበሩትን አሥር ቀናት በጸሎት በመትጋት አሳለፉት ። (የሐዋ· ሥራ· ፩ ፥ ፲፬) ፋሲካ ባለፈ በሃምሳኛው ቀን የሚውለው በዓል በዓለ ሃምሳ ይባላል ። ይህ በዓል በግሪክ ጴንጠቆስጤ ሲባል ትርጓሜውም ሃምሳ ማለት ነው ። በአይሁዶች ዘንድ የሰበቱ ሱባኤና የመከር በዓል በመባል ይታወቃል ። (ዘጸ· ፴፬ ፥ ፳፪ ፤ ፳፫ ፥ ፲፯) ይህ በዓል የመከር መጀመሪያ ስለሆነ የፍሬው በኩር ለእግዚአብሔር ይቀርብ ነበር ። ከአዲሱ እህል ሁለት ዳቦ ይጋገርና ለመሥዋዕት ይቀርብ ነበር ። በዚህ በበኩራት ቀን ክርስ ቶስ መንፈስ ቅዱሱን ለደቀ መዛሙርቱ ስለ ሰደደ የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዋ ቀን እንደሆነ ይታሰባል ። (ሮሜ ፰ ፥ ፱) የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም ። በዚህ ምክንያት ደቀ መዛሙርቱ የሚያትማቸውን የእርሱ ለመሆናቸው የሚያረጋግጥላቸው መንፈስ ቅዱስ እስኪወርድ ድረስ በኢየሩሳ ሌም መጠበቅ ነበረባቸው ። (ኤፌ· ፩ ፥ ፲፫ ፥ ፲፬ ፤ ፬ ፥ ፴)

በዓለ ሃምሳ (ጴንጠቆስጤ)

መንፈስ ቅዱስ ነፋስ ወይም እሳት አይደለም ። ነገር ግን ለደቀ መዛሙርቱ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ ። ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው ። እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው ። አውሎ ነፋስ ኃይሉን ያሳያል ። አውሎ ነፋስ ጣራን ግንጥሎ መርከቦችን እንደሚገለብጥና ተራራን እንደሚንድ ሁሉ (፩ኛ ነገ· ፲፱ ፥ ፲፩) እንዲሁም የእግዚአብሔር መንፈስ ድንጋይ የሆነውን የሰውን ልብ ይሰብራል ። እሳቱ የእግዚአብሔርን ጻድቅነት ያሳስበናል ። እሳት ወርቅንና ብርን እንደሚያነፃ (መዝ· ፲፩ (፲፪) ፥ ፮) መንፈስም እንዲሁ ኃጢአ ተኝነታችንን ገልጾ ያሳየናል ። (ዮሐ· ፲፮ ፥ ፮)

ደቀ መዛሙርቱ ለመመስከር የቻሉት መንፈስ ቅዱስ በወረደባቸው ጊዜ ነው ። ጴጥሮስ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ሳይቀበል በፊት አንዲት ገረድ ፊት ክርስቶስን ካደ ። (ማር· ፲፬ ፥ ፷፯ ፥ ፸፪) በሃምሳኛው ቀን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልቶ ሲናገር ግን የሊቀ ካህናቱን ዛቻና ማስፈራራት ከምንም አልቆጠረም ። (የሐዋ· ሥራ ፬ ፥ ፲፩) ሁላችንም ልናስተውለው የሚገባ አንድ ነገር አለ ። ይኸውም እግዚ አብሔር በመንፈሱ በሚሰጠን ኃይል በኢየሩሳሌም (በቤታችን) በይሁዳ (በጎረቤታ ችን በመንደራችን ወይም በከተማችን ወይም በትምህርት ቤታችን) በሰማርያ (ለጠላ ቶቻችን) እና እስከ ዓለም ዳርቻ እንኳን ሄደን ታላቅነቱን ልንናገር እንችላለን ።

ትእዛዙ ለሁላችንም ነው ። የሥራው ተካፋይ በመሆን መልእክቱን ብናደርስ የክርስ ቶስ መልእክተኞች እንሆናለን ።

## ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ።

ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፦ የሐዋርያት ሥራ ፩ ፥ ፩ — ፲
፪ ፥ ፲፬ — ፵፪
፫ ፥ ፩ — ፲
፲ ፥ ፩ — ፵፰
፲፫ ፥ ፩ — ፫

## ጥያቄዎች

1. የሐዋርያት ሥራ ፩ ፡ ፰ን በቃልህ አጥናና እዚህ ላይ ጻፍ ።

   ____________________

2. ሊቀ ካህናቱና ሰዱቃውያን ሐዋርያትን ለምን አሰሩአቸው ? ____________________

   ____________________

3. እግዚአብሔርም ሐዋርያትን ከእስር ቤት ሲለቃቸው ለማስተማር ወደ ምኩ ራብ የሄዱት መቼ ነው ? ____________________
4. እንደ የሐዋ. ሥራ ፪ ፥ ፴፰ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው ለማን ነው ? ____________________

   ____________________

5. ስለ ገማልያል የምታውቀውን ሦስት ነገሮች ጻፍ ።

   ሀ. ____________________

   ለ. ____________________

   ሐ. ____________________

6. ስደት ሲነሳ ተሰዳጆቹ ምን ያደርጉ ነበር ? ____________________
7. እግዚአብሔር ለጴጥሮስ በራእይ እንስሳና አራዊት የሚንቀሳቀሱም የሰማይ ወፎች ሲያሳየው ምን ሊያስተምረው ፈልጎ ነው ? የሐዋ. ሥራ ፲ ፥ ፴፬

   ____________________

8. እግዚአብሔር ለሥራው ሳኦልንና በርናባስን ምረጡልኝ ሲል ደቀ መዛሙ ርቱ በአንጾኪያ ምን ያደርጉ ነበር ? ____________________

ክርስቲያን መሆን ለማንኛውም ሰው የሚያስደስት ነገር ነው ። ይሁን እንጂ ሰው ክርስቲያን ስለሆነ ለራሱ በመደሰት እንዲሁ መቀመጥ የለበትም ። ኢየሱስ ምስክሮቹ አድርጎናል ። ሐዋርያት በኢየሩሳሌም (በቤታችን የሐዋ. ሥራ ፪ ፥ ፵፪) በይሁዳ (በአገራችን) በሰማርያና (ለጠላቶቻችን) እስከ ዓለም ዳርቻ ምስክሮቹ እንዲ ሆኑ ነግሮአቸዋል ። እስራኤላውያን ግን ሥራውን ስለተው ዛሬ የኛ ሆኖ ተገኝ ቶአል ።

ሆኖም እግዚአብሔርን ለማገልገል ስንነሣ ተቃዋሚዎች ደግሞ ይነሱብናል። ብዙ ጊዜ ተቃዋሚዎቻችን የሃይማኖት ሰዎች ሆነው ይገኛሉ። ምስክርነታችንን ያንቋሽሻሉ። ይሁን እንጂ ደቀ መዛሙርቱ ተመሳሳዩ ሁኔታ በደረሰባቸው ጊዜ «እግዚአብሔርን መታዘዝ ይገባናል» እንዳሉ ማስተዋል ጠቃሚ ነው።

<u>የመታዘዝ አስፈላጊነት።</u>

እግዚአብሔርን የምናምነው ከሆነ እንደምንታዘዘውም የታወቀ ነገር ነው። ኢየሱስም ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ ሲል ተናግሮአል። (ዮሐ ፲፬ ፣ ፲፭) ፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርቱን ስለ ኢየሱስ አትናገሩ በማለት እየከለከሉ ሲያስፈራሩአቸው ከመመስከር ሳይቆጠቡ በቤተ መቅደስ ለብዙ ሰው በመመስከር ላይ ይገኙ ነበር። ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወረደ፣ ክርስቶስን ሰበከላቸው። (የሐዋ ሥራ ፰ ፣ ፭) የጌታም መልአክ ፊልጶስን ተነስተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደሆነው መንገድ ሂድ ሲለው እሺ በማለት ታዘዘ። (የሐዋ ሥራ ፰ ፣ ፳፮ ፣ ፳፯) ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም የክርስትናን እምነት ሊቀበል የቻለው በዚህ ሰው ምክንያት ነው። ጴጥሮስ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የወሰነበት ጊዜ ትንሽ አልነበረም። በሐዋርያት ሥራ ፲ ፣ ፲፬ እግዚአብሔርን አልታዘዘም። በአይሁድና በአሕዛብ መካከል የነበረው ልዩነት በክርስቶስ እንደቀረ ገና መማር ነበረበት። እንደ እስራኤላውያን ቅዱስ ሕዝብና እንደ አሕዛብ የተጣለ ወገን የሚባል እንደሌለና ለሁሉም የጸጋው ወንጌል መድረስ እንዳለበት ተረዳ።

የጸሎት አስፈላጊነት።

እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እየፈለግን ብዙ ጊዜ ምን ማድረግ እንደሚገባን ሳናውቅ ቀርተን ግራ ይገባናል። በሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያው ጥቂት ምዕራፍ የጸሎት አስፈላጊነት ስንት ጊዜ እንደተጠቀሰ እስቲ አስተውል።

የሐዋ ሥራ ፩ ፣ ፲፬ በአንድ ልብ ሆነው በጸሎት ይተጉ ነበር።
፩ ፣ ፳፬ በይሁዳ ፈንታ ስለሚተካው ደቀ መዝሙር ጸለዩ።
፪ ፣ ፵፪ ሐዋርያት በጸሎት ይተጉ ነበር።
፫ ፣ ፩ ጴጥሮስና ዮሐንስ በጸሎት ጊዜ ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር።
፬ ፣ ፳፫ — ፴፩ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከእስር ቤት ከተለቀቁ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ሲጸልዩ ያሉበት ቤት ተናወጠ።
፮ ፣ ፬ ሐዋርያት የጸሎትና ቃሉን የማገልገል ጊዜአቸውን በሌላ ነገር ላይ አላዋሉትም።
፲ ቆርኔሌዎስና ጴጥሮስ ሁለቱም የጸሎት ሰዎች ስለሆኑ እንደተገናኙ አትዘንጋ።

የሐዋርያት ሥራ ከምዕራፍ አንድ እስከ አሥራ ሁለት ስታነብ ጸሎት የሚለውን ቃል በጥንቃቄ እየተመለከትህ አስምርበት። ጸሎት እንዳናደርስ ብዙ ጉዳዮች

ያጋጥሙናል ። ሐዋርያት በጸሎት ስለነበሩ እግዚአብሔርም ምስክሮቹ ይሆኑ ዘንድ ረዳቸው ።

ወንጌል እንዴት እንደተሠራጨ ።

እግዚአብሔር ለሥራው አመራር አቅድ ያለው አምላክ ነው ። ጴጥሮስ ለአይሁድ ወንጌልን እንዲሰብክ ሲያደርግ ጳውሎስ ደግሞ ለአሕዛብ አስተማሪ አድርጎ አስነሣው ። (ገላ. ፪ ፣ ፫ — ፲) ምንም እንኳን የሮሜ መንግሥት ጳውሎስን ለወንጌል ሥራ ያስቸገሩት ቢሆንና ጴጥሮስን ደግሞ የአይሁድ አለቆች ቢያስቸግሩትም በመጨረሻ በማስተማር ሥራቸው ምክንያት የሞት ፍርድ ሲፈረድባቸው በእግዚአብሔር በመታመንና በመታዘዝ ኖረዋል ። እነርሱ ሲሞቱ የወንጌሉ ቃል በሮማ ግዛት በሙሉ ተሰራጭቶ ነበር ።

እግዚአብሔር ዓላማ ያለው አምላክ ነው ። ወንጌሉ ለዓለም እንዲደርስ ፈቃዱ ነው ። እያንዳንዱም ክርስቲያን በዚህ በመሰማራት የሥራው ተባባሪ እንዲሆን ይፈለግበታል ።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ።

ዝግጅት ፡— ሰሜን አፍሪካ ፡ ፍልስጥኤምን ፥ መካከለኛው ሩሲያን ፡ ግሪክን ፡ ፡ የኢጣሊያንና የስፓኝን አካለ ምድር የሚያሳይ ካርታ ሠርተህ ኢየሩሳሌም ፡እስክንድርያን፡አንጾኪያን ፣ አቴናን ፡ ኤፌሶንና ሮሜ የተሰኙትን ከተማዎች በውስጡ አስፍር ።

የሐዋርያት ዘመን ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» አለ ። (ማቴ. ፳፰ ፡ ፲፱) በተጨማሪም .... በኢየሩሳሌም ፣ በይሁዳ ፡ በሰማርያና እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ምስክሮቹ እንደሚሆኑ ነግሮአቸዋል ። (የሐዋ. ሥራ ፩ ፣ ፰)

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሐዋርያት ለዚህ ሥራ ታዛዥ መሆናቸውን ይገልጻል ። ሐዋርያት የምስክርነት ሥራቸውን የጀመሩት በበዓለ ሃምሳ ወይም በጰንጠቆስጤ ቀን እንደሆነ የታወቀ ነው ። (የሐዋ. ሥራ ፪ ፣ ፩ — ፵፪) በመጀመሪያው ቀን ምስክርነታቸው ሦስት ሺህ ሰዎች ለመዳን ችለዋል ። ይኸው መጽሐፍ ከምዕራፍ ፩ — ፯ በኢየሩሳሌም የተደረገውን የምስክርነት ሥራ ሲገልጽ በተለይ ገኖ የሚታየው የእስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ መሞት ነው ። ከዚህ ጋር በሐዋ. ሥራ ፰ ፣ ፩ ክርስቲያኖች በደረሰባቸው የግፍ ብዛት ወደ ይሁዳና ሰማርያ ሲበታተኑ በጋለ መንፈስ ቃሉን ማስተማራቸው አስደናቂ ሳይሆን አልቀረም ። ፊልጶስ በሰማርያ ሲያስተምር ጴጥሮስ ደግሞ በልዳ ፣ በኢዮጴና በቂሣሪያ ወንጌልን ያስፋፋ ነበር ። (የሐዋ. ሥራ ፰ ፣ ፲)

ይሁን እንጂ ክርስቶስ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ ያለው ቃል ሊፈጸም የቻለው እግዚአብሔር በሚያስገርም አኳኋን ቅዱስ ጳውሎስን ለሥራው በጠራው ጊዜ ነው ። በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራው ጳውሎስ ወንጌልን እያስተማረ ከምሥራቅ እስከ መካከለኛው እስያ ድረስ በምዕራብ ደግሞ እስከ ሜቄዶንያ ፡ ግሪክ ፡ ሮም ፥ እስጳንያ ተዘዋወረ ። (ሮሜ ፲፭ ፡ ፳፬ ተመልከት ።)

## የኢየሩሳሌም መውደቅና የሮም መግነን ።

የቤተ ክርስቲያን መስፋፋት በጀመረበት ዓመት የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን በገናናነት የሚበልጥ አንድም አልነበረም ። በሌሎች አማኞች ላይ ስደት በተነሣ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በዚህ ከተማ ተገኝተዋል ። (የሐዋ. ሥራ ፰ ፡ ፩) የመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለምክር የተሰበሰቡት በኢየሩሳሌም ከተማ ነበር ። (የሐዋ. ሥራ ፲፭ ፡ ፩ — ፳፱) እ. ኤ. አ. በ፸ ዓ. ም. አይሁዳውያን በሮም ገዥዎች ላይ ስለተነሳሱ ንጉሥ ቲቶ ኢየሩሳሌምን እንዳልነበረች አደረጋት ። በዚህን ጊዜ መጠጊያ ለመፈለግ ጥቂት ክርስቲያኖች ወደ ምድረ በዳ ሸሹ ። (ማር. ፲፫ ፡ ፲፬) ከዚያ ወዲያ ክርስቲያኖች የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን መምሪያ መጠየቅ ተውና ዓይናቸውን ወደ ሮም አነሡ ፤ ጳውሎስም እዚያው ስለነበረ በዚያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን መምሪያ በመስጠት ረድታለች ። ሌሎች ታላላቅ ቤተ ክርስቲያናት ናቸው ተብለው የሚገመቱት የአንጾኪያ የአሌክሳንድርያና ሐዋርያው ዮሐንስ ብዙ ዓመታት ኖረበት ተብላ የምትገመተው የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ናት ።

እ. ኤ. አ. በ፷፯ ዓ. ም. ውስጥ ጳውሎስ በሮማ ሲገደል ከሠላሳ በማይበልጥ ዓመታት ውስጥ ደግሞ ዮሐንስ እንደሞተ ይታመናል ። በምትካቸው መንፈሳዊውን ሥራ ለማካሄድ ከያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የተውጣጡ የታወቁ ሰዎች ተነሡ ። እነዚህም ሰዎች በሊቀ መንበርነት ማዕረግ በመጀመሪያ ጊዜ ስብሰባዎቹን ሲመሩ ከቆዩ በኋላ በፕሬዚዳንትነት ደረጃ ለሌሎች ክርስቲያኖች ትእዛዝ ያስተላልፉ ነበር ። የከተማይቱም አብያተ ክርስቲያናት ዋና ሹም ኤጲስ ቆጶስ የአያሌ አማንያን ዋና ሹም በመሆኑ እንደ ሊቀ ጳጳስ ይታይ ነበር ።

## የክህደት መመንጨት ።

የቀድሞ ክርስቲያኖች ብሉይ ኪዳንን መመርመርና የጳውሎስን መልእክቶች ከአራቱ ወንጌላት ጋር በማስተያየት ማጥናት ከጀመሩ ወዲህ የእምነታቸው አቋዋም በምን ላይ እንደተመሠረተ ለማወቅ ቻሉ ። ሆኖም በጥናት ምርመራቸው ላይ እንዳሉ አያሌ አስቸጋሪ ጉዳዮች መጡባቸው ። ከእነዚህም አስቸጋሪ ነገሮች አንዱ ክርስቶስ ማን ነው ? የሚል ነበር ። እርሱ እግዚአብሔር ነው ብለው ቢያምኑ እግዚአብሔር ለራሱ እንዴት ይጸልያል ? ብለው በማሰብ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩሌታ እንደሌለው ገመቱ ። ሌላ አስቸጋሪ ነገር ደግሞ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ ያለው ተስፋ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ላይ እንዳሠፈረው ከሆነ መንፈስ ራሱ

አምላክ ሲሆን በክርስቶስ መላኩ ታናሽነቱን ይገልጻል በማለት የተዘበራረቁ ሐሳበ ችን መሰብሰባቸው ስለ ምስጢረ ሥላሴ ትልቅ ውዝግብን አመጣባቸው ። በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም እንኳን አጥጋቢ ገለጻን መስጠት ባይችሉም ሰዎች ሊያምኑ የሚች ሉበትን የተለያየ መንገድ ፈጠሩ ። አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር አብ ሥጋን ለብሶ በምድር እንደተመላለሰና በመጨረሻም እንደተሰቀለ ያምናሉ ። የዚህም ዓይነት ትም ህርት ተከታይ የነበሩት ፖትርፖሲያንስ ሲባሉ ትርጓሜውም «አባት ገዳዮች» ማለት ነው ። ጥቂቶች ደግሞ አብ ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የአንድ አካል ልዩ ልዩ መለክ ቶች ናቸው ብለው ያምናሉ ። ይህንንም ትምህርት የሚከተሉት ወገኖች «መጸሊስ ችስ» ወይም «አስመሳዮች» ይባላሉ ። እነዚህ ወገኖች የእግዚአብሔር አብን በብ ሉይ ኪዳን መገለጽ የወልድን በወንጌላት መነገርና የመንፈስ ቅዱስን በቤተ ክርስቲ ያን መታወቅ ይደግፋሉ ።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት የክህደት ትምህርቶች በያለበት ስለመነጩ አብ ያተ ክርስቲያናት ተሰብስበው በጉዳዩ መመከከርና መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል የሚያ ስተምራቸውን የማያደናቅፍ የእምነት ዋልታዎች መሰብሰብ ግድ ሆነባቸው ። የሆነ ሆኖ በእነዚህ ትምህርተ ሃይማኖት ላይ መስማማት በአንዳንዶች ላይ በመታየቱ ለአብያተ ክርስቲያናት መለያየት ምክንያት ሆነ ።

አለመግባባት የነበረው የጉባኤ ጊዜ ።

ዝግጅት ፡— አጭር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከተሰኘው መጽሐፍ ላይ ከገጽ ፲ — ፲፪ ያለውን ክፍል ከቆላስይስ ፪ ፡ ፮ — ፳፫ ጮኾ አንብብ ።

ጥያቄዎች

1. በቀድሞው የክርስትና ዘመን አድናቆትን ያተረፉትን ሁለት አብያተ ክርስቲ ያናት ጥቀስ ።
2. አራቱን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ስማቸውንና የተሰበሰቡበትን ቀን ጮኾ ዘርዝር ።

________________________________________

3. ጳጳስ ሲባል ትርጉሙ ምንድር ነው ? ____________
4. ትምህርተ ሃይማኖታችንን ያገኘነው ከየት ነው ? ____________
5. በቆላስይስ ምዕራፍ ሁለት ላይ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን የሚያመለክተውን ቁጥር አውጥተህ ከጻፍከው በኋላ በቃልህ አጥናው ። ____________

የቀድሞ ክህደት ።

ሁለተኛው ዓይነት ትምህርት ከገባባቸው አብያተ ክርስቲያናት አንደኛይቱ የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን ነበረች ። በዚያም ያሉ ክርስቲያኖች በትምህርት በመብሰላቸው እግዚአብሔርን በቀጥታ ከማምለክ ይልቅ መላእክትን አማላጅ በማድረግ ማምለክ ቀና መሰላቸው ። ከሁሉም የሚያስገርመው ዓለምን እንደ እርኩስ መቁጠራቸውና ምን ዓይነት ምግብ እንደሚመገቡና ምን ዓይነት መጠጥ እንደሚጠጡ እንኳን ደንብና ሥርዓት ማውጣታቸው ነው ። እነሆ ይህ ዓይነት የክህደት ትምህርት ኖስትስዝም ወይም ውስጣዊ ጥበብ ይባላል ። ጳውሎስ የከሃዲነት ትምህርት ተከታዮችን እንደገሰጸ ለቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልእክቱ እናነባለን ።

ሌላው ክህደት ደግሞ አርያንዝም ሲሆን ስሙ የመጣው ትምህርቱን ካስተማረው አሪያስ ከተባለው ሰው ነው ። አሪያስ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ያንሳል ፤ ሆኖም ከሰው ይበልጣል በማለት አስተማረ ። እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ ከሰው መንፈስ ብልጫ ያለው ከክርስቶስ ግን የሚያንስ ነው ብሎ አስተምሮአል ። ትምህርቱን በማጠቃለል ሲናገር አንድ እግዚአብሔር መኖሩንና ወልድ ከአብ መንፈስ ቅዱስም ከወልድ የማይተካከል መሆኑን ሲገልጽ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ዘላለማዊ አለመሆን ተናግሮአል ። ሦስተኛው የክህደት ትምህርት ምስጢረ ሥላሴን የሚቃወምና እግዚአብሔር አንድ ነው በማለት ትምህርቱን የመሠረተ ሞናርኪይዝም የተባለ ነው ። እነዚህ ወገኖች ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን እምነት ሲሰጡ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ሆኖ ሳለ በልዩ ልዩ መልክ ራሱን ገልጿል ይላሉ ። ይኸውም በፈጣሪነት አብን በመሆን ፣ በቤዛነቱ ወልድን በመምሰል ፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ ራሱን እንደ መንፈስ ቅዱስ ይገልጻል ብለው ያምናሉ ። ይህ ዓይነቱ ትምህርት በውኑ እርግጥ አለመሆኑን ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ያረጋግጣሉ ። እንዲህማ ከሆነ እግዚአብሔር አብ እንደ እግዚአብሔር ወልድ በራሱ ቀኝ ተቀመጠ ማለት ነው ? በጭራሽ አይደለም ፤ (ሉቃስ ፳ ፥ ፵፩ ፥ ፵፬ ፤ ማር. ፲፩ ፥ ፴፪ ፤ ሉቃስ ፳፪ ፥ ፴፱ ፤ ዕብ. ፩ ፥ ፫ ፤ ፲ ፥ ፲፪ ፤ ቆላ. ፫ ፥ ፩ ፤ ሮሜ ፰ ፥ ፴፬) ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ብሎ የጸለየው እግዚአብሔር አብ እንደ ወልድ ከሆነ እግዚአብሔር አብ ለራሱ ጸለየ ለማለት እንችላለን ? ከቶ አንችልም ። (ማቴ. ፳፯ ፥ ፵፮ ፥ ፵፯ ፤ ሉቃስ ፳፫ ፥ ፵፬ — ፵፯ ተመልከት ።) ጉባኤዎቹ ልዩ ልዩ ዓይነት የሃይማኖት ትምህርት በየሥፍራው ስለተሰራጨ ክርስቲያኖች ትክክለኛውን ትምህርት ለይተው ማስተማር ግድ ሆነባቸው ።

እ. ኤ. አ. በ፫፻፳፭ ዓ. ም. በቢታንያ ውስጥ ኒሴ በምትባለው ሥፍራ የመጀመሪያው ጉባኤ ተደርጎ የአሪያስ የክህደት ትምህርት ተጠንቶ ተቀባይነት ባለማግኘት ተደምስሶአል ።

እ. ኤ. አ. በ፫፻፹፩ ዓ. ም. ሁለተኛው ጉባኤ ከኒሴ ምንም ያህል በማትርቅ በኮንስታንቲኖፕል ተደርጎ አርያንዝም ጨርሶ እንዲጠፋና የኒሴም እምነት ከነዝርዝሩ እንዲጸና ተደረገ ።

እ· ኤ· አ· በ፬፻፴፩ ዓ· ም· ሦስተኛው ጉባኤ በኤፌሶን ሲሆን በስብሰባውም የፒላገስ ትምህርት ተወገዘ ። ትምህርቱም ሰው ያለ እግዚአብሔርን ሊታዘዝ ይችላል የሚል ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሰው በእግዚአብሔር ጸጋ ካልዳነ በስተቀር የኃጢአት ባርያ እንደሆን ይናገራል ።

እ· ኤ· አ· በ፬፻፶፩ ዓ· ም· አራተኛው ጉባኤ በቻልስዶን ተደረገ ። ይህም የጉባኤ ስብሰባ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት አሌክሳንደሪያን እንደ መሪ በመውሰድ የምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ሮማን እንደ መሪ በመቁጠር ስለ ክርስቶስ ባሕርይ በተደረገው ውሳኔ ተከፋፈሉ ። ክርስቶስ የሰውና የአምላክነት ባሕርይ አለው ወይስ ሁለቱንም ባሕርይ በአንድ ጊዜ ይዞአል ? የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት የክርስቶስን ሰብዓዊና መለኮታዊ ባሕርይ ሲደግፉ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ግን ሐሳቡን ተቃወሙ ። በዚህን ጊዜ በሁለቱ ወገኖች መካከል አለመግባባት ተፈጠረ ። ይሁን እንጂ አንድ ተፈጥሮ እንዳለው መገመቱ የሚሻል ቢመስልም የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስ መለኮታዊ ባሕርይ ብቻ አለው ብንል እንዴት ሰው ሊሆን ይችላል ? የሰውስ ባሕርይ ብቻ ካለው እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል ? ክርስቶስ መለኮታዊን ከሰብዓዊ ባሕርይ ጋር አስተባብሮ ይዞአል ለሚለው ሐሳብ ደግሞ ይህ ኃጢአት ሳይነካው እንዴት ሊኖር ይችላል ? በሚለው ሐሳብ ጉባኤው ሳይስማማ ተበተነ ። ግሪክ ፡ ሶርያ ፡ ግብፅና ኢትዮጵያ ሞኖፊሳይት በመባል ሲጠሩ ሮምና አውሮጳ ደግሞ ዳዮፊሳይት በመባል ይታወቃሉ ።

## የቤተ ክርስቲያን መለያየት ።

የቤተ ክርስቲያን መለያየት ምዕራብና ምሥራቅ በመባል ብቻ ሳይሆን የበላይ ገዢያቸውን ፓትሪያሪክ በማድረግ በአምስት ተከፋፍለዋል ። እነርሱም ሮም ቆንጠንጢኒያ ፡ አሌክሳንደሪያ ፡ አንቲዮክና ኢየሩሳሌም ናቸው ።

በ፫፻፵ ዓ· ም· ገደማ ፍሬምናጦስና ኤድስዮስ በቀይ ባሕር ዳርቻ እንደተገኙ በሽፍታ ሳይገደሉ ወደ ቤተ መንግሥት ተወሰዱ ። በዚያም የክርስትናን እምነት ለንጉሡ ኢዛና ማድረስ ቻሉ ። ፍሬምናጦስና ኤድስዮስ ወንድማማቾች ሲሆኑ የመጡትም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ክፍል ከሆነችው ከሶርያ ግዛት ነው ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፍሬምናጦስ ወደ አሌክሳንደሪያ በመሄድ ፓትሪያርኩ አጥናቴዎስ ለኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲልኩ ጠየቀ ። አጥናቴዎስም ፍሬምናጦስን የአክሱም ጳጳስ በማድረግ ሾሙት ። ፍሬምናጦስም የጵጵስናውን ማዕረግ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጣ ።

## የማርቲን ሉተር መነሣት ።

<u>ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ፡</u>— ማቴ· ፳፫ ፡ ፩ — ፫

ማርቲን ሉተር ከተባለው መጽሐፍ ከገጽ ፴ — ፴፩ ያለውንና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ባጭሩ ከተባለው መጽሐፍ ከገጽ ፴ — ፴፪

ጥያቄዎች

1. የፈሪሳውያን ዋና ስህተት ምንድር ነው ? ____________________
2. አስተማሪያችን ማን ነው ? ____________________
   አባታችን ማን ነው ? ____________________
   ይህ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና አባቶች ጠባይ ምን ትምህርት ይሰጣል ? ____________________
3. ማቴ. ፳፫ ፡ ፲፪ን ጻፍና በቃልህ አጥናው ። ____________________
4. ከሞት በኋላ ስላለው የነፍስ ሁኔታ የሮማውያን ትምህርት ምን ይላል ?
5. ለኃጢአት ይቅርታ ይሆናል የሚሉትን ወረቀት ለመሸጥ ሮማውያን ለምን ተነሳሱ ? ____________________
6. ማርቲን ሉተር የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን በመቃወም ስንት አንቀጾችን ጻፈ ? ከጻፈስ በኋላ ወረቀቱን የት ላይ ለጠፈው ? ____________________
7. ማርቲን ሉተር ከጳጳሱ ቁጣ እየሸሸ ያከናወናቸውን ነገሮች ጻፍ ። ____________________

አብያተ ክርስቲያናት የምዕራብና የምሥራቅ በመባል ከተከፋፈለች ወዲህ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ገናና ሆነች ። ወዲያው የሮማው ጳጳስ የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ተከታይ አድርጎ ራሱን በመቁጠር ክርስቲያኖች ሁሉ በእርሱ ሥልጣን ሥር እንዲተዳደሩ መልእክት አስተላለፈ ። ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ለማንበብ ይፈሩ ስለነበር ማንን ማመን እንዳለባቸውና ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ቄሶቹን ይጠይቁ ነበር ። ዶክተሮችና የሥነ ፍጥረት ሊቃውንት እንኳን ጳጳስ ከቤተ ክርስቲያን ያወግዘናል በማለት በፍርሃት ይኖሩ ነበር ። አውሮጳ በጨለማ ግዛት ውስጥ ገባ ፤ ማርቲን ሉተር ሰው በእምነት እንጂ በሥራ እንደማይጸድቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደተረዳ የጨለማው ዘመን አለቀ ። ማርቲን ሉተር አዋቂ የጀርመን መነኩሴና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ነበር ። ትምህርቱን ለማዘጋጀት መጽሐፍ ሲያጠና የካቶሊክ ቄሶችና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማይስማማ ሆኖ አገኘው ። የጳውሎስን መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎችና ገላትያ እንዲሁም ሌላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሲያጠና (ሲኦል) ለጊዜው የነፍሳት ማረፊያ ስፍራና ቀሳውስቱ ለኃጢአት ይቅርታ ይሆናል በማለት የሚሸጡት ወረቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሌለ ተረዳ ።

በእነዚህ ጊዜያት ሮም ታላቅ ከተማ ነበረች ። የሮማም ጳጳሳት የሚኖሩት ባማረ ሥፍራና በክብር ነበር ። በዚያን ጊዜ ታላቅ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ስለሚሠራ ስለዚህ ጳጳሱ ገንዘብ የሚያገኝበትን መንገድ መፈለግ ግድ ሆነበት ።

ስለዚህም አንድ ሰው ሲሞት ነፍሱ በመሠቃየት በሲኦል ትቆያለች ፤ ከዚህ ከሥቃይ ሥፍራ ግን ለመውጣት የምትችለው ለኀጢአቷ ይቅርታ የሚሆነውን ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን ወይም ከቀሳውስቱ ለአንዱ ሰው ሲከፈልላት ነው ። ገንዘቡም ከተከፈለ ቄሶቹ ጸሎቱን ያደርሱና በሲኦልም ትሠቃይ የነበረችው ነፍስ ትወጣለች ብለው ሕዝቡን ሰበኩ ። እንዲህ ከሆነ አንድ ሰው አባቱ ወይም እናቱ ቢሞቱበትና ገንዘብ በመክፈል ከሥቃይ ሥፍራ ለማስወጣት ከቻለ የተጠየቀውን ገንዘብ ሁሉ መክፈሉ አያጠራጥርም ።

## ማርቲን ሉተር ።

ማርቲን ሉተር መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ባጠና ቁጥር ቤተ ክርስቲያን መታደስ እንደሚገባት እየተገነዘበ ሄደ ። ከዚያም ፺፭ አንቀጾችን በጀርመን ቋንቋ በመጻፍ በዊትንበርግ ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ለጠፈ ። የቤተ ክርስቲያኑን ትምህርትና የጳጳሱን ሃሳብ ስለተቃወመ ከሮማ ቤተ ክርስቲያን አባልነት ተወገደ ። ይህንንም የሚገልጽ ደብዳቤ ከጳጳሱ እንደደረሰው አቃጠለው ። ስለዚህም ጳጳሱ በግዞት ሊያኖሩት ወደው ነበር ። ነገር ግን የሳክሶኑ አገረ ገዢ በነበሩት በፍሬደሪክ አማካኝነት ሊያመልጥ ችሎአል ። ማርቲን ሉተር መጽሐፍ ቅዱስ በላቲን ቋንቋ ተጽፎ በነበረ ጊዜ ጥቂት ሰዎች ብቻ አንብበው በመረዳታቸው የአብዛኞዎቹን ችግር በመገንዘብ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ጀርመን ቋንቋ ተረጎመ ።

## የሉተራን ቤተ ክርስቲያን ።

ማርቲን ሉተር የሮማ ቤተ ክርስቲያንን ጉድለት አወቀ ፤ እርሱም እንድትስተካከል እንጂ አዲስ ቤተ ክርስቲያን የማቋቋም ሃሳብ አልነበረውም ። ይሁን እንጂ ጳጳሱ ሉተርንና ተከታዮቹን ማሳደድ ጀመረ ። ሆኖም ማርቲን ሉተር በጀርመን ሕዝቦች ሁሉ ስለተደገፈ ሊነካው አልቻለም ። ቀስ በቀስም የሉተር ደጋፊዎች በስብሰባቸው ቀጠሉ ። ዛሬ በመላው ዓለም ተሰራጭተው ይገኛሉ ።

በሮም የተደረገው ለውጥና ሄንሪ የእንግሊዝ ንጉሥ ።

የሚነበቡ የመጽሐፍ ክፍሎች ፦ አጭር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ ፴፫ ፣ ፴፯

## ጥያቄዎች

1. ከጳጳሱ ይልቅ ራሱን የቤተ ክርስቲያን ራስ ያደረገው የትኛው የእንግሊዝ ንጉሥ ነው ?
2. ይኸው ንጉሥ በቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት ያመጣው ለውጥ ምን ድር ነው ? ____________________
3. የእንግሊዝ ንግሥት የነበረችው የሜሪ አንደኛው ሃይማኖት ምን ነበር ?

____________________

4. ለፕሮቴስታንቶች ያደረገችላቸው ነገር ምን ነበር ? ____________

5. በ፲፭፻፶ ዓ. ም. የእንግሊዝ ንግሥት የነበረችው ማን ናት ? ____________

ቤተ ክርስቲያን በ፲፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ።

የጭለማ ዓመታት ተብለው በሚታሰቡት ጊዜያት በቀሳውስቱ አስተማሪነት ሰዎች ለማንበብና ለመጻፍ በቁ ። ቅዳሴውም የሚከሄደው በላቲን ቋንቋ ነበር ። አንዳንዶች ቄሶች ሊሆኑ የቻሉት ለሮማዊው ጳጳስ ብዙ ገንዘብ እየሰጡ ነበር ። ይህም ገንዘብ ልክ የሌለው የሞተውን ቄስ የዓመት ገቢ የሚያህል እንደነበር ይታሰባል ። ይህም አሰጣጥ «አናቴስ» ሲባል ትርጓሜውም የዓመት ገቢ ማለት ነው ። ደግሞም ከተራው ሕዝብ ተለይተው የሚኖሩ መነኩሳት ነበሩ ። እነዚህም መነኩሳት ከከተማው ሕዝብ ገንዘብና የሚበላ ነገር እየለመኑ የዕለት ጉርሳቸውን በማግኘት ይኖራሉ ። በየገዳማቱ የሚኖሩት ወንዶችና ሴቶች የንጽሕና ኑሮ ይኖራሉ የሚባሉት ድሆችን የማይረዱና ለቤተ ክርስቲያን የማይጠቅሙ ሆነው ተገኝተዋል ። አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ጳጳሱን መታዘዝ ግድ ነበረባቸው ። የእንግሊዝ አገር ንጉሥ እንኳን እንዲታዘዝ ይጠበቅበት ነበር ። አንዳንድ የእንግሊዝ አገር ጉዳዮችም ለጳጳሱ ሲቀርቡ በቂም ገንዘብ ከከፈሉ የኃጢአት ይቅርታ ያገኛሉ ።

የቀሳውስቱንና የመነኩሳቱን የግድየለሽነት ኑሮ መኖር ሕዝቡ እያስተዋለ ሄደ ። የሮማም ጳጳስ እንደ እንግሊዝ ባሉት የውጭ አገሮች ላይ ሥልጣን ማግኘቱ ስሕተትና የማይገባ መሆኑን ተረዱ ።

የእንግሊዝ ከሮም ሥልጣን ሥር መውጣት ።

ለንጉሥ ሄንሪ ስምንተኛ የሟች ወንድሙን ሚስት እንዲያገባ የሮማው ጳጳስ ልዩ ፈቃድ ሰጠው ። ይህ ዓይነቱ ጋብቻ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው ጋር አይስማማም ። (ዘኁልቁ ፲፰ ፥ ፲፮ ሰው የወንድሙን ሚስት እንዳያገባ ይከለክላል ።) ሄንሪ የወንድሙን ሚስት ካገባ በኋላ አኒ . . . በሌይን የተባለችውን ሴት ለማግባት ስለወደደ የፊተኛው ጋብቻ ሕጋዊ አይደለም በማለት የፍቺ ደብዳቤ እንዲሰጠው ጳጳሱን ጠየቀው ። ጳጳሱ ግን ከቴሬን ከፈረንሣዩ መንግሥት ገዢ ከቻርለስ አምስተኛ ጋር ያላትን ዝምድና በማሰብ ተቃወመ ። ምንም እንኳን ጳጳሱ ቢቃወመው ንጉሥ ሄንሪ አንዴ ስላገባት መፍታት እንደማይገባው እርግጠኛ ነበር ።

የሮማው ጳጳስ ስሕተቱን መገንዘብ ስላልፈለገ ሄንሪ ወደፊት የሮማው ጳጳስ በእንግሊዝ አገር ላይ ምንም ሥልጣን እንደማይኖረው አወጀ ። በ፲፭፻፴፬ ዓ. ም. እ. ኤ. አ. የእንግሊዝም የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት የእንግሊዝ ንጉሥ የቤተ ክርስቲያን የበላይ ባለሥልጣን እንዲሆን ወሰነ ።

የካንተሪበሪው አርቺ ቢሾፕ የበላይ ሆኖ ሲሾም የእንግሊዝ አገር ቤተ ክርስቲያን «አንግሊካን» በመባል ታወቀች ።

## የቤተ ክርስቲያን መታደስ ።

የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ከሮማ ጳጳስ ሥልጣን ሥር እንደተላቀቀች ይከበሩ ስለነበሩት ብዙ በዓላት ይሰገድላቸው ለነበሩት ብዙ ምስሎች ፡ ሕግጋትና ደንቦች አወጡ ። አንዳንዶቹም የሐዋርያት ልብስና አጥንት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይሰገድላቸውና ይታመንባቸው ነበር ። እነዚህንም ያየ የኃጢአት ይቅርታ ያገኛል በማለት ከብዙ ሰዎች ገንዘብ መቀበሉ ቀረ ። መመነንን መጽሐፍ ቅዱስ ስለማይደግፈው እንዲቀር ተደረገ ። በየቅዱሳን ምስል አጠገብ ሻማ ማብራት ተከለከለ ። አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ሻማ በመሸጥ ብቻ ብዙ ገቢ አግኝተዋል ። አያሌ ገዳማት ተዘጉ ። መሬታቸውም ተሸጠ ። እ. ኤ. አ. በ፲፭፻፵፬ ዓ. ም. ቀሳውስቱም ከላቲን ይልቅ ሕዝቡን በእንግሊዘኛ እንዲያስተምሩ ተጠየቁ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በ፲፭፻፵፫ ዓ. ም. ንግሥት በሆነችው በቀዳማዊት ሜሪ ዘመን የወትሮው ልማድ እንደገና ተመልሶ ወደ አገሪቱ ገባ ። ነገር ግን የነገሠችው ለአምስት ዓመታት ብቻ ነበር ። ወደ ሦስት መቶ የሚሆኑ ሰዎች ፕሮቴስታንት ስለሆኑ በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ አደረገች ። ወዲያው የሮማውያን ሥልጣን አበቃ ። ዛሬ ንግሥት ኤልሳቤጥ ፪ኛ የቤተ ክርስቲያኑ የበላይ ተጠባባቂ ሲሆኑ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ የአገሩ ሃይማኖት ሆኖ ይኖራል ። በ፲፰፻፶፯ ዓ. ም. ሥራውን የጀመረው የሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ክፍል ነው ።

## የቤተ ክርስቲያን መለያየት ።

የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን እንኳን ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ ሆና አልኖረችም ። ጆን ዊስሊ የተባለ ቄስ ነበር ። እርሱም ደኅንነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ሲያስተምር ሌሎቹ ቄሶች ተቃወሙት ። ጆን ዊስሊና ተከታዮቹ ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ተገንጥለው ወጡና ሜቶዲስት የሚባል ማኅበር አቋቋሙ ። ባፕቲስት የተባሉት ደግሞ የሕፃናትን ጥምቀት የማይደግፉ ስለሆኑ ሰው ለአካለ መጠን ከደረሰ በኋላ ቢያምን ብቻ ሊጠመቅ ይችላል በማለት በአዋቂዎች ጥምቀት የሚያምኑ ናቸው ።

## የዘመናችን የወንጌል አስተማሪዎች ማኅበር ።

ልዩ ልዩ የወንጌል አስተማሪዎች ማኅበር የመጡት ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ወይም ክፍለ ሃይማኖት ነው ። ከባፕቲስት ወገን የሆነው ዊልያም ከሪ የመጀመሪያው ወንጌላዊ ነው ። አሁን የሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር በመባል የሚታወቀው ከእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የመጣ ሲሆን መከነ ኢየሱስና ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚባሉ አሉ ። እንደ ኤስ አይ ኤም ያሉትም የሚሰዮን ማኅበር ከተለያዩ ቤተ ክርስቲያን የመጡ ስለሆኑ በመሠረታዊ የሃይማኖት ትምህርት የሚስማሙ እንጂ የተወሰነ ሃይማኖታዊ ሕግ የላቸውም ። ሐድሰን ቴለር ቻይና ኢንላንድ ሚሽን የተባለ

ውን ድርጅት በመጀመሪያ በማቋቋም ኢንተርዲኖሚኔሽናል ማኅበሮች ወደ መታወቅ መጡ ።

አብያተ ክርስቲያናት እንዴት እንደተለያዩ ።

<u>የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ።</u>

በክርስቶስ ሰብዓዊና መለኮታዊ ተፈጥሮ የተነሣ መከፋፈል ።

የዳዊት ሊቭንግስቶን ወደ አፍሪቃ መምጣት ።

ምንባብ ፡— ስድስት ሚስዮናውያን ወደ አፍሪካ ገጽ ፳፩ — ፴፰
የጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልሞና
ዘሌዋውያን ፳፭ ፣ ፴፱ — ፶፭

<u>ጥያቄዎች</u>

1. የጳውሎስን መልእክት ወደ ፊልሞና ካነበብክ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ ።
   ሀ. ፊልሞና ማን ነበር ? ______________________
   አናሲሞስስ ? ______________________
   ለ. የጳውሎስ ሥራ ምን ነበር ? ______________________
2. እንዴት ባለ ሁኔታ አናሲሞስ ወደ ፊልሞና ሊላክ ቻለ ? ______________________
______________________

3. ገላትያ ፫ ፡ ፳፰ እንብበህ እምነታችን ከባርነት ቀንበር የሚያላቅቀን መሆኑን የሚያሳስቡ ሌላ ጥቅሶች ፈልግ ።

4. ባርያ የሆነ ዕብራዊ ነፃ ለመውጣት ስንት ዓመት ማገልገል ነበረበት ?

______________________________

5. እስራኤላውያን ባሮች እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ለምን ፈቀደ ? ዘሌዋውያን ቁጥር ፳፭ ______________________________

## የዳዊት ሊቪንግስቶን የቀድሞ ሕይወት ።

የዳዊት ቤተ ዘመዶች ስኮትላንድ በምትገኘው አንዲት ትንሽ ከተማ ውስጥ ይኖሩ ነበር ። እኒህ ቤተ ሰቦች በሀብት የበለጸጉ ባይሆኑም እግዚአብሔርን የሚፈሩና እምነታቸውን በአምላካቸው ላይ የጣሉ ነበሩ ። የዳዊት አባት መጠጥ መጠጣትን ፡ ሲጋራ ማጨስን የማይወድ ፣ ጥሩ ጠባይ የነበረው የሰንበት መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ ነበረ ። ዳዊት በ፲፰፻፲፫ ዓ. ም. ተወለደ ። በአሥር ዓመቱ በአንድ የጥጥ ፋብሪካ ውስጥ ይሠራ ነበር ። ድካሙንም ሳይቆጥር የማታ ትምህርት እየተከታተለ ራሱን በእውቀት ሊገነባ ቻለ ። ከጠዋቱ ፲፪ ሰዓት አንስቶ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ በፋብሪካ ውስጥ መሥራት ለዳዊት ቀላል አልነበረም ።

ዳዊት ሃያ ዓመት ሲሞላው ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ሰጠ ። በሃያ ሦስት ዓመቱ ስለ መድኃኒት ቅመማ ለማጥናት ወደ ግላስኮው ዩኒቨርሲቲ አመራ ። በዚያም ሳለ ግሪክን ጠንቅቆ ከማወቁ በላይ መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቅ ተማረ ። ለትምህርት የሚያስፈልገውን ወጭ ይከፍል የነበረው በፋብሪካው ውስጥ ሠርቶ ካፈራው ገንዘብ ነበር ። በመጨረሻም በ፲፰፻፵ ዓ. ም. ዶክተር በመባል በለንደን የሚስዮናዊ ማኅበር አባል በመሆን ከአንድ ሚስዮናዊ ጋር ወደ አፍሪካ መጣ ።

## ኑሮ በአፍሪካ ።

ሊቪንግስቶን አብሮአቸው የሚሠራቸውን ሰዎች ሊያውቅ ይመኝ ነበር ። ስለ ዚህም ከአውሮጳውያን ወገኖቹ በመለየት በአፍሪካ ዜጋዎች መካከል ብቻውን ጎጆ በማቆም ባሕላቸውንና ቋንቋቸውን ለማጥናት ስድስት ወራት ቆየ ።

በመጀመሪያ አገልግሎቱ ይኖርበት የነበረው ቀበሌ በተናካሽ አንበሶች የተወረረ በመሆኑ አንዱን በጥይት ከገደለው ሌሎቹ ድራሻቸው ይጠፋል ብሎ በማሰብ በአንዱ ላይ አነጣጥሮ ቢተኩስበት የተተኮሰበት ጥይት አልዘልቅ ብሎት ኖሮ ቶሎ አልሞት አለው ። ይህ በደም የተዘፈቀ አንበሳ ገንፍሎበት ዳዊት ላይ እመር ብሎ ወጥቶ እስከ መጨረሻው ድረስ እጁ በሽተኛ አድርጎታል ።

ሊቪንግስቶን ባርነትን ሲቋቋም የመጀመሪያ ጊዜው አልነበረም ። በደቡብ አፍሪካ የደች ተቀማጮች አፍሪቃውያንን እንደባሪያ ይገዙአቸው ስለነበረ በአካባቢያቸው እንዲሠራ ለዳዊት አልፈቀዱለትም ነበር ። ስለዚህ ለሚስዮናዊ ሥራው ቀና ይሆንልኛል ብሎ ወደገመተበት ወደ ሰሜናዊው ክፍል ለመዘር አስቦ ቤተሰቡን ወደ

አገሩ ላከቸው ። ለሚሲናዊ ጉዞውም ከብዙ መንከራተት በኋላ ፖርቱጋሎች ወደሚገዙት ክፍል አደረሰው ። በዚያም የባርያ ንግድ ይከሄድ ነበር ። ይሁን እንጂ ባርነትን ለመቋቋም የመጡትን የአገሩ የእንግሊዝን ሹማምንት በማግኘቱ ከእነርሱ ጋር መወዳጀት ጀመረ ። በአፍሪካ ምድር በቆየ በአሥራ አምስት ዓመቱ በ፲፰፻፷፫ ዓ. ም. ከብዙ ገዢዎች ጋር በመወዳጀት በሺህ የሚቆጠሩ በሽተኞችን ሊያክም በብዙ ቀበሌዎች ተዘዋውሮአል ። በዚያም የባርያን ንግድ አሰቃቂ ውጤት ተመልክቷል ።

## የታሪኩ ቀጥያ ።

ዳዊት በ፲፰፻፷፬ ዓ. ም. ስለ ችግሩና ስለ ሥራው ሁናቴ ለማመልከት ወደ እንግሊዝ አገር ሄደ ። ከሁለት ዓመት በኋላ ተመልሶ ወደ አፍሪካ መጣ ። በ፲፰፻፷፮ ዓ. ም. ሌሎች ስድስት ሚስዮናውያን በሥራው ስለተባበሩ የባሮች ንግድ ምን ያህል አሰቃቂ እንደሆነ ማስተዋል ችለዋል ። ከአዲሶቹ ሚስዮናውያን አንዱ ቢሾፕ ሜኬንዚ ባሪያዎችን ያሳድዱ የነበሩትን ቀማኞች እየተከታተለ ምርከኞቹን ከዚያ አሰቃቂ ሁኔታ ሊያድናቸው ይጥር ነበር ። ይሁን እንጂ አንድ ቀን ቢሾፕ ሜኬንዚ በጀልባው ሲመለስ ጀልባው ተበላሽታ ውኃ ውስጥ ገባ ። በዚህም ትኩሳት ይዞት ባለቤቱና እርሱ በዚሁ በሽታ ጠንቀ በመሞት በአንዲት የአፍሪቃ መንደር የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጸመ ። ልቭንግስቶን ይኸን የባርነት ቀንበር ከለጓደኞቹ እርዳታ ሊቋቋመው እንደማይችል በመረዳት ወደ እንግሊዝ አገር ተመልሶ በመሄድ የአረቦችንና የፖርቱጋሎችን ግፍ በዝርዝር ከሁለት ሺህ ለሚበልጡ ያገሩ ሰዎች አስረዳ ። ከዚህም በላይ የባርያ ነጋዴዎች ባሮቹን እስከ አረብ አገር ከዚያም ራቅ እስከ አለው እስከ ሕንድ አገር ድረስ ማድረሳቸውን ገለጸላቸው ። በተጨማሪም ደብዳቤ እንኳን ቢጽፍ በእነዚህ ነጋዴዎች ምክንያት አለመተላለፉን አስታወቃቸው ። ከዚህም ቀደም ቀኑን ሙሉ የጻፋቸው ፵፪ ደብዳቤዎች ቀልጠው እንደቀሩ አወራላቸው ።

## የአሟሟቱ ሁኔታ ።

የልቭንግስቶን ወሬ በሐገሩ በአውሮጳ ለአያሌ ወራት ስላልተሰማ ይፈልገው ዘንድ አሜሪካዊው የወሬ ወኪል ሄንሪ ስታንሌይ በድርጅቱ አማካይነት ተልኮ በ፲፰፻፸፩ ዓ. ም. ከዳዊት ጋር ተገናኙ ። ሄንሪ የዳዊት ልቭንግስቶን እምነትና ለሌሎች ያለው ፍቅር ልቡን ስለነካው ይዞለት ከመጣው ምግብና መድኃኒት ጋር ለአንድ ዓመት አብሮት መቆየት ወደደ ። ሄንሪ ስታንሌይ ተመልሶ ወደ አገሩ ከሄደ በኋላ ዳዊትን ትቶት የነበረው የብቸኝነት ስሜትና በሽታው ተነሣበት ። እ. ኤ. አ. ግንቦት ፩ ቀን ፲፰፻፸፫ ዓ. ም. ዳዊት እትንሿ ጎጆው ውስጥ አልጋው አጠገብ በጉልበቱ ተንበርክኮ በጸሎት ላይ ሳለ እንደሞተ የደረሱለት አፍሪቃውያን ጓደኞቹ አገኙት ። ወዳጆውም ልቡን ከመላው አካሉ ለይተው በአንድ ዛፍ ሥር ከቀበሩት በኋላ የቀረውን ሰውነቱን ግን ወደ ሐገሩ ወደ ኢንግላንድ ልከውት የሐገሪቱ ንጉሥና ንግሥት ወደሚቀበሩበት ወደ ታላቁ የሎንዶን ቤተ ክርስቲያን ልዩ ስሙ

ዌስት ምንስተር አቤይ በተባለው የመቃብር ሥፍራ ተቀበረ ። በመቃብሩም ላይ በዮሐንስ ፲ ፡ ፲፮ ላይ የሚገኘው ጥቅስ ተጽፎበት ነበር ።

«ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ ፡ እነርሱን
ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምጼንም ይሰማሉ ።»

## ሐድሰን ቴለርና ኦስ አይ ኤም ።

ከሚከተለው ታሪክ ስለ ሐድሰን ቴለር ምን እናጠናለን ? ሐድሰን ቴለር የአሥራ ዘጠኝ ዓመት ዕድሜ በነበረው ጊዜ በምሽት አንድ አሮጌ ጨርቅ ከለበሰ ሰው ኋላ ይጓዝ ነበር ። ሰውዬውም ሐድሰንን ሚስቱ ልትሞት ነው ፣ አብሮአት የሚጸልይ ሰው እፈልግ ነበር አለው ። ሐድሰን ቴለር መንፈሳዊ መጽሔት በሚያድልበት ወቅት እዚህ ቦታ መጥቶ ሰዎቹ መጽሔቱን በመቅደድ እንዳባረሩት ያስታውሳል ። ይሁን እንጂ አሁን በምሽት ሲመጣ ማንም ሰው የሚያውቀው አልመሰለውም ።

የከተማይቱም ስም ሑል ሲሆን ሰዎቹም ዓሣ በማጥመድ የሚኖሩ ትምህርት የሌላቸው ድሆች ነበሩ ። በሽተኛዋም ሴት ወደተኛችበት ክፍል እንደገቡ መሬት ላይ ተኝታ አምስት ትንንሽ ልጆችም ከበዋት በአጠገቧ ተቀምጠው አየ ። በበር የሚገባውን ብርድ የሚከላከል መጋረጃ እንኳን አልነበረም ። ሐድሰን በኪሱ የነበረው አንድ ብር ብቻ ቢሆንም ምንዛሪ ቢያገኝ ሊያካፍላቸው ይወድ ነበር ። ሆኖም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መሰከረላቸው ፤ ቆየትም ብሎ ስላለው ብርና ስለ ሰዎቹ ረሃብ እያሰበ ይጨነቅ ነበር ። አብሮአቸው ሊጸልይ አልቻለም ። ሐሳቡ ሁሉ ወዳለው ብር ይሄድ ነበር ። በመጨረሻም ሐሳቡን በመቁረጥ እንዲህ አለ ፣ «እኔ ብዙ ገንዘብ ያለኝ ይመስላችሁ ይሆናል ፤ ነገር ግን ያለችኝ ገንዘብ ይህች አንድ ብር ብቻ ነች ፣ እንካችሁ ምግብ ግዙበት ፣ ለእኔም እግዚአብሔር እንደሚያስብልኝ አልጠራጠርም አላቸው ።»

ከዚያም ጥቂት ስለ ሰማያዊ አባቱ ካወራላቸው በኋላ ወደ ቤቱ ሄደ ። እርሱም ጥቂት ለእራትና ለቁርስ የሚሆን ምግብ ነበረው ። ይህንንም ሲመገብ በጓንት ውስጥ አምስት ብር ተደርጎ ቤቱ ድረስ መጣለት ።

«ለድሀ የሚሰጥ ለእግዚአብሔር ያበድራል ።»

ሐድሰን ቴለር ለድሀ በመስጠቱ ጥሩ ወለድ እንዳገኘ ተሰማው ። ይህ ታሪክ በሆነ በሦስተኛው ዓመት ሐድሰን ቴለር ወደ ቻይና አገር ሄደ ። አገሩ የተረጋጋና ሰላም የሰፈነበት አልነበረም ። ወደዚያም መጓዝ አስቸጋሪ ነበር ። አንድ ሚስዮናዊም በጀልባ እንሂድ ባለው ጊዜ ሐድሰን ተስማምቶ ለጉዞአቸው የሚያስፈልጋቸውን ምግብ ፣ የሌሊት ምግብ ማዘጋጃ ዕቃ ፣ መጻሕፍትና በቻይና ቋንቋ የተጻፉ መንፈሳዊ መጽሔት ይዘው ጉዟቸውን ወደ ቻይና አመሩ ።

እከተማይቱም ወደብ እንደደረሱ መጻሕፍታቸውንና መንፈሳዊ መጽሔታቸውን ይዘው በመሄድ በመቅደስ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች አሰሙአቸው ። ቤተ መቅደሱ በልዩ ልዩ መልክ በተቀረጹ ጣዖታት ተሞልቶ ነበር ። እነዚህ ሚስዮናውያን የምስ

ክርነት ቃላቸውን ሰጥተው ወደ ሌላ ሥፍራ ሊያመሩ ሲሉ ጥቂት ቄሶች መጥተው ያሉበትን እንዲገቡኙ ጠየቋቸው ።

ሰዎቹም በገዳም ውስጥ ስውር በለ ሥፍራ በግርግዳ ላይ የሰው እጅ ማሳለፊያ የሚያህል ቀዳዳ አሳዩአቸው ። መስኮትና በር አልነበረውም ። በጭላንጭል የሰው ሥዕል ይታይ ነበር እንጂ ውስጡ በቂ ብርሃን አልነበረም ፤ ሰውዬውም እስኪ ሞት ከዚህ ሥፍራ አይንቀሳቀስም ነበር ። ሲሞት ያች ትንሿ ቀዳዳ ትዘጋና መቃብሩ ትሆናለች ።

የቻይናን ሕዝብ ቋንቋ ያውቅ የነበረው የወንጌል አስተማሪ ስለ ኢየሱስ መሰከረላቸው ። ሆኖም እነዚህ መነኩሳት ሰው ማንኛውንም ሃይማኖት ቢከተልና ማንኛውንም አምላክ ቢያመልክ ግድ አልነበራቸውም ። እነርሱም ጣዖት ሁሉ አንድ አምላክ እንደሆነ ይገምታሉ ። በስመ ሃይማኖትም ሁሉ ጥሩ ይመስላቸዋል ። ያስገበኙ ትንም ሁሉ ከተመለከተ በኋላ ሐድሰን ቴለር በመቃብር ውስጥ የሚኖረውን ቅዱስ የተባለውን ሰው ያስብ ነበር ።

«ጣዖቶቻቸው ከብርና ወርቅ የተገኙ የሰው ሥራ ናቸው ።
አፍ አላቸው አይናገሩም ፤ ጆሮ አላቸው ነገር ግን አይሰሙበትም ።
እጅ አላቸው ነገር ግን አይዳስሱበትም ።
እግር አላቸው ነገር ግን አይራመዱም ።» መዝ. ዳዊት ፻፲፭ (፻፲፫) ፥ ፬ — ፯

## ነገ ቢሆን ጊዜው አያልፍብህምን ?

ሚስተር ኒ የቻይና አገር ሰው ሲሆን በቻይና በጣም የታወቀ ቡድሂዝም ፥ ታኦይዝምንና የኮንፊሽስን ትምህርት አጠናቆ የሚያውቅ ነበር ። ይሁን እንጂ ሰው ሲሞት ነፍሱ ምን ትሆናለች ? ሰው እውነትን እንዴት ማግኘት ይችላል ? እያለ በአሳቡ እያወጣ እያወረደ ያስብ ነበር ።

አንድ ቀን በመንገድ ሲያልፍ የደወል ድምፅ ሰማ ። ቆም ብሎም አላፊውን ሰው ቢጠይቅ የኢየሱስ ሰዎች መሰብሰቢያ ነው በማለት ገለጹለት ። ደወሉ እንደተደወለ በውስጥ ያሉት ሰዎች የተቀደሰ መጻሕፍታቸውን ሲያነቡ ስብከትም ሲሰሙ አይቶ ሚስተር ኒም ከቅዱሳት መጻሕፍት የሚሰጠውን ትምህርት ለመስማት ወደ ጸሎት ቤት ገባ ። በዚያም ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁም የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል ። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ እንዲሁ ዓለሙን ወዶአልና የሚለውን ጥቅስ ሰምቶ ክርስቲያን ለመሆን በቃ ። ይፈልግ የነበረውም የዘላለምን ሕይወት ነው ። ከጥቂት ወራት በኋላ ሚስተር ኒ ሐድሰን ቴለርን እንዲህ ሲል ጠየቀው ። በዚያን ቀን ማነው የሰበከው ? ይህ መልክም ነገር ወደ እንግሊዝ አገር ከመጣስንት ጊዜ ሆኖታል ? እርሱም ብዙ ዓመታት ሆኖታል ሲል መለሰለት ። ሚስተር ኒ በመገረም ለብዙ ዓመት ይህንን የኢየሱስን ታሪክ እያወቃችሁ እስከ ዛሬ ሳትነግሩን መቆየት እንዴት አስቻላችሁ ? አባቴ ለሃያ ዓመታት እው

ነትን ሲፈልግ ቆይቶ ሳያገኝ ያለ አምላክና ያለ ተስፋ ሞተ ። የምሥራቹ ወንጌል የበራላቸው ሰዎች ላልሰሙት ለማሰማት ለምን በፍጥነት አይሄዱም ?

## ኤስ አይ ኤም ከ፲፱፻፴ ዓ. ም. በፊት ።

ዝግጅት ፦ የአፍሪካን አከለ ምድር የሚያሳየውን ካርታ ከሳልክ በኋላ የናይጀሪያ ፣ የሊብያና የሱዳን ፣ የኢትዮጵያን አገር ምልክት አድርግበቸው ። በተጨማሪም የእያንዳንዱን አገር ዋና ከተማ ለማወቅ ሞክር ።

### ሮውላንድ ቪ. ቢንግሃም ።

በ፲፰፻፺፪ ዓ. ም. ሮውላንድ ቢንግሃም ሕይወቱን ለእግዚአብሔር አደራ በመስጠት እግዚአብሔር ወደሚልከው ሥፍራ ሄዶ ለማገልገል ወሰነ ። ከአንድ ዓመት በኋላም እግዚአብሔር ሊሄድበት የሚገባውን ሥፍራ አሳየው ፤ በካናዳ አገር የነበረች ሴት ለወንጌል ሥራ ወደ ሱዳን አገር ስለሚሄደው ልጇዋ አጫወተችው ። በዚያን ጊዜ ሱዳን የሚባለው ክፍል ከሊብያ ወደ ታች የሣሃራን በረሃ ይዞ እስከ ሱማሊያ የሚደርሰውን ሰፋ ያለ ክፍል የያዘ ነበር ።

ቢንግሃም ዋልተር ጎዋስስና ቶማስ ኬንት የተባሉት ወንጌላውያን በ፲፰፻፺፫ ዓ. ም. ከእንግሊዝ አገር ወደ አፍሪካ ተጓዙ ። በዚያን ጊዜ በአፍሪካ የነበረው የበሽታ ዓይነት እምብዛም አይታወቅም ነበር ። ብዙም የወንጌል አስተማሪዎች ጥቂት ጊዜ እንደቆዩ ባልታወቀ በሽታ ይሞቱ ነበር ። በኅዳር ወር ፲፰፻፺፬ ዓ. ም. ዋልተር ጎዋንስ ሞተ ። በዚሁ ዓመት በታኅሣሥ ወር ቶማስ ኬንት ደግሞ ሞተ ። ሚስተር ቢንግሃም በወባ በሽታ እንደተያዘ ወደ አገሩ ወደ ካናዳ ተመለሰ ።

እንደ ዛሬው ዘመን የሚስዮን ማኅበር ስላልተቋቋመ እርዳታ ማግኘት ቀላል አልነበረም ። ሆኖም በቤተ ክርስቲያን ደጋፊነት ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አፍሪካ መጣ ። እንደገናም ወባ ስለያዘው ወደ አገሩ ለመመለስ አስቦ ነበር ። አብረውት የወጡት ሁለት ሰዎች ችግሩን መቋቋም አቅቷቸው ወደ አገራቸው ሲመለሱ በ፲፱፻፮ ዓ. ም. ናይጀሪያ ፖትጊ በምትባለው ሥፍራ ለመጀመሪያ ጊዜ ጣቢያቸውን አቋቋሙ ። በዚህን ጊዜ የወባ መከላከያ ተገኘ ።

በሮውላንድ ቢንግሃም አማካኝነት ኤስ አይ ኤም በአፍሪካ ውስጥ ሥራውን ሊጀምር ቻለ ። ሮውላንድ ቢንግሃም የመጀመሪያው የሚስዮኑ ሐላፊ በመሆን እስከ ዕለተ ሞቱ ማለት እስከ ፲፱፻፴፪ ዓ. ም. ድረስ አገልግሏል ።

### የኤስ አይ ኤም ፕሮግራም ።

ኤስ አይ ኤም በናይጀሪያ አገር ሥራውን ከጀመረ ወደ ሰማንያ ዓመታት ሊሆነው ነው ። በእነዚህም ጊዜያት ውስጥ ሐኪም ቤቶችን በማቋቋም ትምህርት ቤቶችን በመከፈት ሕዝቡን በብዙ ረድቷል ። የመጽሐፍ ቅዱስ ት / ቤቶች ፣ የሥጋ ደዌ መከላከያ ሐኪም ቤት አቋቁሟል ። የሚዘጋጀውም በዚሁ አገር ነው ። በናይጀ

ሪያም ከኤስ አይ ኤም ጋር ተባብሮ የሚሠራው ማኅበር የምዕራብ አፍሪካ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በመባል ይታወቃል። በኤስ አይ ኤም ተቆርቁረው የነበሩት ጣቢያዎች ሁሉ በምዕራብ አፍሪካ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲካሄዱ ተደርጓል።

ኤስ አይ ኤም በላይቤሪያ ትልቅ የራዲዮ ጣቢያ አለው። በዚህ ራዲዮ ጣቢያ የወንጌሉ መልእክት በተለያዩ ቋንቋዎች ለመላው የአፍሪካ ክፍለ ዓለም ይተላለፋል። በመካከለኛው አፍሪካ የተሰራጩት የኤስ አይ ኤም ወንጌል አስተማሪዎች ቁጥር ከአንድ ሺህ የሚበልጥ ነው። እነዚህም የወንጌል አስተማሪዎች የመጡት ከአሜሪካ፣ ከካናዳ፣ ከአውስትራሊያ፣ ከኒውዚላንድ፣ ከብሪቴን፣ ከጀርመን፣ ከፈረንሳይና ከስዊዘርላንድ ነው። ከተለያየ አገር እንደመጡ ሁሉ እንዲሁም የመጡበት ቤተ ክርስቲያን ልዩ ነው። አንዳንዶች ከበፕቲስትና ሜቶዲስት ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከፕሬስቢቴሪያን የመጡ ናቸው። ሆኖም በትምህርተ ሃይማኖት የሚለያዩባቸውን ጥቃቅን ነገሮችን ችላ በማለት መሠረታዊ በሆኑ ነገሮች ይስማማሉ።

## <u>የሥራው ዋጋ።</u>

እንዲህ ዓይነቱንም ሥራ በሚገባ ለማካሄድ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም መሥዋዕት አድርጎ መስጠት ይጠይቃል። ዋልተር ጎዋንትና ቶማስ ኬንት የተባሉት ወንጌላውያን በአፍሪካ ውስጥ አንድ ዓመት እንዳገለገሉ ሞቱ። አንድም ወንጌላዊ እንዲሁ በወባ ትንኝ ተነክሶ ሞተ። ሁለት ወንጌላውያንና ሦስት ልጆቻቸው ወደ አገራቸው ሲመለሱ ተገድለዋል። አንድ ሐኪምና አንድ አስታማሚ በልታወቀና ዛሬም መድኃኒት በልተገኘለት በሽታ ተይዘው ሞተዋል። በብዙው የሚስዮን ጣቢያ የልጆቻቸውና የራሳቸው መቃብር ይገኛል። በአዲስ አበባ ጉለሌ ሰፈርም ነፍሳቸው ከጌታ ዘንድ በሰማይ ስትሆን ሥጋቸው ግን የትንሣኤን ቀን በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

## <u>ሚስዮናውያን ወደ አፍሪካ ለምን ይመጣሉ ?</u>

የወንጌል አስተማሪዎች ወደ አፍሪካ የመጡበት ዋና ምክንያት ለሕዝቡ በማዘንና መድኃኒት ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ የሚለውን የጌታችንን ትእዛዝ ለመፈጸም ነው። ስለዚህም አንዳንዶች ወደ ሎንዶንና ቶሮንቶ ሲሄዱ ሌሎች ደግሞ ወደ ኒውዮርክና አፍሪካ መጥተዋል። ጳውሎስም የምሥራቹን ወንጌል እንዲያዳርስ በእግዚአብሔር በተጠራ ጊዜ እንዲህ አለ።

«ከሰማይም ለተገለጠልኝ ጥሪ እምቢ አላልኩም።»

እንደዚሁም የወንጌል አስተማሪዎች እግዚአብሔርን አለመታዘዝ አይቻላቸውም። እግዚአብሔር ወደሚልካቸው ሥፍራ ሁሉ ለመሄድ ዝግጁ ናቸው።

## ኤስ አይ ኤም በኢትዮጵያ ።

### ከጠላት ወረራ በፊት ።

ይህንን ክፍል በጥንቃቄ ከነበብህ በኋላ በምዕራፉ መጨረሻ ያለውን ጥያቄ ለመመለስ ሞክር ።

ዶክተር ቶማስ ላምቤ ከ፲፱፻፳፯ ዓ. ም. ጀምሮ እስከ ጠላት ወረራ ፲፱፻፴፬ ዓ. ም. ድረስ የኤስ አይ ኤም ሐላፊ ነበሩ ። ዶክተር ላምቤ የአሜሪካ አገር ተወላጅ ሲሆኑ እስከ ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. ወንጌልን በሱዳን አገር ሲያስተምሩ ቆይተዋል ። ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ በመዛወር የወንጌል ማስተማርን ተግባር በወለጋ ጠቅላይ ግዛት ቀጠሉ ። በዚያም በቆዩበት ወቅት ብዙ ጓደኞችን አፈሩ ። ከእነዚህም አንዳንዶቹ በኋላ የመከላከያ ሚኒስቴር የሆኑት ደጃዝማች ብሩ፣ ደጃዝማች መሸሻና ደጃዝማች ይገዙ ነበሩ ። እነዚህም ሰዎች የወለጋ ወይም የኤሉባቦር ጠቅላይ ገዥዎች እንደነበሩ ይታወሳል ።

ዶክተር ላምቤ ያፈሩዋቸው ሌላ ጓደኛ ደግሞ ራስ ናደው ነበሩ ። ዶክተር ላምቤ ራስ ናደውን ሲጎበኙ እግዚአብሔር በአንዲት ጥንዚዛ አማካኝነት ከራስ ተፈሪ መኮንን ጋር እንዲገናኙ አደረገ ። አንድ ቀን ራስ ናደው እንቅልፍ ላይ እንዳሉ አንዲት ጥንዚዛ ጆሮአቸው ገባች ፤ ራስ ናደውም ኃይለኛ ውጋት ተሰምቷቸው ሲቸገሩ ብዙ ሰዎች ሊረዱአቸው ሞከሩ ። ነገር ግን አልቻሉም ። በመጨረሻ በእኩለ ሌሊት ራስ ናደው ዶክተር ላምቤ ቤት ድረስ ሄደው እርዳታ እንዲደረግላቸው ጠየቁ ። ዶክተር ላምቤም መሣሪያ ስለነበራቸው ያላንዳች ችግር ጥንዚዛውን አወጡላቸው ። ራስ ናደውም የዶክተር ላምቤን አዋቂነትና አስፈላጊነት በመረዳት ከራስ ተፈሪ መኮንን ጋር እንዲተዋወቁ ደብዳቤ ጻፉላቸው ።

በሚቀጥለው ጊዜ ዶክተር ላምቤ ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ ደጃዝማች ብሩን በቤተ መንግሥት ስላዩዋቸው ተደሰቱ ። ዶክተር ላምቤ በቤተ መንግሥት ውስጥ እንኳን የሚያውቋቸውን ሰው እግዚአብሔር ስለሰጣቸው አመሰገኑት ። በዚያን ጊዜ በአዲስ አበባ ሐኪም ቤት ስላልነበረ ዶክተር ላምቤ ሐኪም ቤት እንዲያቋቁሙ በራስ ተፈሪ ተጠየቁ ። ዶክተር ላምቤ በሐሳቡ ተስማምተው ወደ አገራቸው ሄደው በቂ መሣሪያና ገንዘብ ይዘው መጡ ። የሆስፒታል መሥሪያም ቦታ እንደተሰጣቸው ሥራው ሁለት ዓመት የፈጀ ሆስፒታል ሠሩ ። ይህ ሥፍራ አሁን በአዲስ አበባ ጉለሌ ቀበሌ የዶክተር ላምቤ ሰፈር በመባል ይታወቃል ።

ዶክተር ላምቤና ባለቤታቸው እንደገና ወደ አገራቸው ወደ አሜሪካ ባደረጉት ጉዞ ይሠሩበት የነበረውን ሚስዮን ትተው «ዘ አቢሲኒያን ፍሮንቲየር ሚሽን» የሚባለውን ማኅበር አቋቁመው ወንጌልን እስከ ኬንያ ጠረፍ ድረስ ለማዳረስ ሞከሩ ። ነገር ግን ዶክተር ቢንግሃም ስለ አዲሱ ዶክተር ላምቤ ስለሚያቋቁሙት ማኅበር ሰምተው ከኤስ አይ ኤም ጋር እንዲሠሩ አሳሰቧቸው ፤ እንደዚሁም ሆኖ በ፲፱፻፳፯ ዓ. ም. የመጀመሪያዎቹ የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን አዲስ አበባ ገቡ ። እነርሱም

ዶክተር ላምቤና ባለቤታቸው፣ ሚስተር ራስማንና ባለቤታቸው፣ ሚስተር ሮድና ባለቤታቸው፣ የአውስትራሊያው ተወላጅ ሚስተር ግሌን ኬን ሲሆኑ ከአሜሪካ ደግሞ ሚስተር ክላረንስ ጳፍና ሚስተር አመን ናቸው።

ዘጠኙም ወንጌላውያን ዶክተር ላምቤ በጉለሌ ባሠሩት ሐኪም ቤት አቅራቢያ ተቀመጡ። በኋላም ዋና ከተማውን ትተው ወንጌልን ለማስተማር ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ወረዱ። ስንቃቸውንና ድንኳናቸውን ጭነው በበቅሎ ይጓዙ ነበር። በመጀመሪያ ወደ ማረቆ ከዚያም ወደ ሆሳዕና ወረዱ። በከንባታም ብዙ ሰዎች በደስታ ሊቀበሏቸው ወጡ። ዶክተር ላምቤም በወለጋ የተዋወቋቸውን ወዳጃቸውን ደጃዝማች መሸሻን የከንባታ ገዢ ሆነው አገኙአቸው። ደጃዝማች መሸሻ የወንጌል አስተማሪዎቹን በደስታ በመቀበል የሚስዮን ጣቢያ ለማቋቋም እንደሚችሉ አረጋገጡላቸው። ነገር ግን በመጀመሪያ ሌላው የዶክተር ላምቤ ወዳጅ ወደሚገኙበት ቦታ እንዲሄዱ አሳሰቡአቸው፤ በወላሞም አገረ ገዢ የነበሩትን ደጃዝማች ይገዙን አገኙዋቸው። ደጃዝማች ይገዙ በደስታ በመቀበል የሚስዮን ጣቢያ እንዲያቋቁሙ ፈቀዱላቸው። ሚስዮናውያኖቹ ግን የብላቴን ወንዝ በመሻገር ወደ ሲዳሞ አልፈው እስከ አገረ ሰላም ድረስ ሄዱ። አዲሱም አገረ ገዢ ደጃዝማች ብሩ ስለነበሩ ምቹ ሥፍራ ካገኙ የሚስዮናዊውን ሥራቸውን እንዲቀጥሉ አበረታቱአቸው።

ስለዚህም ሚስዮናውያኖቹ ጋርብቾ በሚባለው ሥፍራ ወንጌል የማስተማር ሥራቸውን ለመጀመር አቀዱ። ሚስተር ኬን በጋርብቾ ሲቆዩ ዶክተር ላምቤና ባለቤታቸው ከሌሎቹ ሚስዮናውያን ጋር ከሰዶ ከተማ ወጣ ብሎ ዳሞት ተራራ አጠገብ አቶና በሚባል ሥፍራ ቤት መሥራት ጀመሩ።

በሚቀጥለው ዓመት አዲስ ሚስዮናውያን ተጨመሩ። ስለዚህም ሚስ በርግስትን ሚስተር ሆርንና ዶክተር ላምቤ ሁለት አዲስ ጣቢያ ለመክፈት ወሰኑ። ይህም በሆሳዕናና በማረቆ ነበር። ሚስተር ጳፍ ሰዶን በመተው ወደ ሆሳዕና ሄደው ከዚያም ወዲያው በጋምቢዳ ሌላ ጣቢያ ከፈቱ።

የእግዚአብሔርም ሥራ እየተስፋፋ የሚስዮናውያኖቹም ቁጥር እየጨመረ ሄደ። በይርጋለም በደራሳ አገር ከዲላ በስተደቡብ በኩል ጠትቲ በምትባል ሥፍራ የሚስዮን ጣቢያ ተቋቋመ። በከንባታም ዱራሜ በምትባል ሥፍራ ሌላ ጣቢያ ተከፈተ። ፲፱፻፴ ዓ. ም. ለወንጌል ሥራ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ሚስተር አመንና ባለቤታቸው ወደ ጎፋ በመሄድ በቡልቂ አንድ የሚስዮን ጣቢያ አቋቋሙ። ሚስ በርግስትን ወደ ገሙ በመሄድ በጨንቻ አንድ ጣቢያ አቋቋሙ። በደብረ ማርቆስም ራስ እምሩ ሚስዮናውያኖቹን በረዳበት ሥፍራና በላሊበላ ራስ ካሣ የሚስዮናዊ ሐኪም በጠየቁበት ሥፍራም የሚስዮን ጣቢያ ሳይቋቋም አልቀረም። ስለዚህ ዶክተር እስኪምፕ የተባሉ ሴት ሚስዮናዊ ከሚስተርና ሚስስ አግለስቢ ከሌሎች ጋር ወደ ላሊበላ ሄዱ። ሚስ ብሌር ለዓይነ ስውራን ልጆች በደብረ ማርቆስ ት ቤት ከፈቱ። ዶክተር ሮበርት በሰዶ ሐኪም ቤት ሲያቋቁሙ ዶክተር ሑፐር ዛሬ የልዕልት ዘነበ ወርቅ የሥጋ ደዌ ሆስፒታል ተብሎ የሚጠራውን በአዲስ አበባ አቋቋሙ።

ትምህርት ቤቶች እንደ ተከፈቱ ጥቂት አማኞች ተገኙ ፡ ብዙ በረከት ለማግኘት ሲታሰብ አገሪቱ በጠላት እ. ኤ. አ. ጥቅምት ፫ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ተወረረች ።

<u>ጥያቄዎች</u>

1. ከጠላት ወረራ በፊት የኤስ አይ ኤም መሪ ማን ነበር ?__________
2. በኢትዮጵያ ሚስዮናዊ ከመሆኑ በፊት የት ይሠራ ነበር ?__________

____________________

3 የዶክተር ላምቤ ወዳጆች የነበሩትን የሁለት ኢትዮጵያውያኖች ስም ጻፍ ።

____________________

4. በመጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የሚስዮናውያን ቁጥር ስንት ነበር ?

____________________

5. የሁለቱን የመጀመሪያዎቹን የኤስ አይ ኤም ጣቢያዎች ስም ጻፍ ።

____________________

6. የኢትዮጵያን ካርታ ሣልና ከጠላት ወረራ በፊት የነበሩትን የኤስ አይ ኤም ጣቢያዎች አመልክት ። __________
7. ጣሊያኖች ኢትዮጵያን የወረሩት መቼ ነበር ?__________

<u>ኤስ አይ ኤም በጠላት ዘመን ።</u>

ይህንን ክፍል በጥንቃቄ ከነበብህ በኋላ በምዕራፉ መጨረሻ የሚገኙትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክር ።

ጠላት ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ዶክተር ላምቤ በአገራቸው በአሜሪካ ነበሩ ። ቢሆንም ወዲያው እንደተመለሱ ንጉሠ ነገሥቱ የቀይ መስቀል ማኅበርን እንዲያዘጋጁ ጠየቋቸው ። የኤስ አይ ኤም ሐኪሞች በሕክምና ሥራ ብዙ እርዳታ ሰጥተዋል ። ዶክተር እስኪምፕ ወደ ደሴ ሲሄዱ የቀሩት ሚስዮናውያን ከዶክተር ሑፐር ጋር በመተባበር የቀይ መስቀል ማኅበርን መሥርተው ከራስ ደስታ ወታደሮች ጋር ተሰለፉ ። ዶክተር ላምቤ አሥራ ስድስት የቀይ መስቀል ድርጅት አቋቁመው ቁስለኞቹን ያክሙ ነበር ። የመጀመሪያው የቀይ መስቀል ክፍል ወላጆቹ በቻይና ሚስዮናውያን የሆኑ በዶክተር ሐክማን የሚመራ ሲሆን እርሳቸውም በጣሊያን አኤሮፕላን የተጣለው ቦምብ እቀብራለሁ ሲሉ ሞቱ ። ብዙዎችም የፈጥኖ ደራሽ መኪናዎች በቦምብ ሲደበደቡ ብዙ መጣሪያዎች ተበላሽተዋል ። አንድ ጊዜ በነበረው ውጊያ የበሽተኛ ማመላለሻ መኪና እየነዱ ሲሄዱ በውስጡ የነበሩት ዶክተር ሂላንደር ሲቆስሉ የቀሩት ሞተዋል ።

በሲዳሞ ይኖሩ ከነበሩት ሚስዮናውያን ሁለቱ ማለት አንዱ ሚስት የነበረው ሌላው ደግሞ እጮኛ የነበረው ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ አስበው በመንገድ ላይ እንዳሉ ሁለቱ ሚስዮናውያንና አብረዋቸው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ጓደኞቻቸው በሽፍታ ተገደሉ ። በማረቆ የነበሩት ሁለት ሴት ሚስዮናውያን ሀብታቸው ሲዘረፍ በአንድ ኢትዮጵያዊ ረዳትነት በደህና ወደ አዲስ አበባ ለመድረስ በቅተዋል ።

ጣሊያኖችም አዲስ አበባ እንደደረሱ ከካቶሊኮች በስተቀር የቀሩትን ሚስዮናውያን ወደ አገራቸው ለመመለስ አሰቡ ። በደቡብ ኢትዮጵያ ከነበሩት ሚስዮናውያን አብዛኞዎቹ ወላሞ ሶዶ ተሰብስበው ወደ አዲስ አበባ በጣሊያን መኪና በማጓጓዝ ሚስዮናውያኖቹ አንድ ባንድ አገሪቱን ለቀው እንዲሄዱ አደረጉ ። አንዳንዶቹ አንድ ቀን ወደ ኢትዮጵያ እንመለሳለን ብለው ተስፋ በማድረግ ወደ ሱዳን አገር ሄዱ ። እንደዚያም ሲሆን በከንባታና በወላሞ ስለተውአቸው አማኞች ምንም አይሰሙም ነበር ።

ብዙ አማኞች ባይገኙም የመጀመሪያው የጥምቀት ሥነ ሥርዓት በታኅሣሥ ወር ፲፱፻፴፬ ዓ. ም. በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት ተፈጸመ ። የሚስዮን ጣቢያውም ከጋር ብቻ ወደ ሆሚቾ ሲዛወር ስምንት ሰዎች ተጠመቁ ። ይህ በሆነ በዓመቱ ሁለተኛው የጥምቀት ሥነ ሥርዓት በወላሞ ሶዶ ኦቶና በሚባለው ስፍራ ተፈጸመ ። ከእነዚህ በቀር ሦስት ሰዎች በጎፋ ሲጠመቁ ጥቂቶችም በአዲስ አበባ ተጠምቀዋል ። ጥቂቶቹም አማኞች ከከንባታ የመጡ ነበሩ ። የመጀመሪያ አማኞች ከሚባሉት ውስጥ አቶ ሽጉጤ (ሌላ ስማቸው ኢርጢሮ) ከንባታ የሆነ አቶ ዋንድሮ ፣ ከወላሞ አቶ ብሩ ፣ ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ የወላሞ ጸሎት ቤት መሪ ነበሩ ። ሚስዮናውያኖቹ በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. እንደወጡ አንድ መቶ የሚሆኑ ያመኑና የተጠመቁ አማኞች ነበሩ ። ደብዳቤም መጻፍ የማይቻል ነበር ። ጣሊያኖቹ በአገራቸው ቋንቋ የሚጻፈውን ብቻ ያስተላልፉ ነበርና ። ስለዚህ ሚስዮናውያኑ በአማኞቹ ዘንድ የነበረውን ሁኔታ ባያውቁም ውጤቱ በጣም አስደናቂ ነበር ። አቶ ሽጉጤ ክርስቲያን መሆናቸውን የሰሙ ሁሉ ሚስዮኖቹ ሥራ ስለሰጡት ነው በማለት ያሟቸው ነበር ። ከሚስዮኖቹ ጋር ይሠሩ ስለነበር ማመናቸው ለሌሎች አላስገረመም ። ሚስዮኖቹ ኢትዮጵያን ለቅቀው እንደ ወጡ አማኞቹ በእምነት ጸንተው የሚኖሩ መስሎ አልታያቸውም ። አማኞቹ ግን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማራቸውን ቀጠሉ ። ሰዎችም ስለዚህ የወንጌል ትምህርትን በብዙ ማወቅ ፈለጉ ፤ በመጨረሻም በከንባታና በወላሞ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ሆኑ ።

በሶዶ የጣሊያኑ አዛዥ ወታደሩን ታንኩንና ጠብመንጃውን ለማሳየት በወላሞ በገሙና ጎፋ የሚኖሩትን ሁሉ አስጠራ ። ይህም ትዕይንት በምሽት እንዳለቀ ሰዎቹ ከሩቅ ሥፍራ ስለመጡ ማደሪያ መፈለግ ነበረባቸው ። ስለዚህም አንዳንዶቹ ሰዎች ወደ ወላሞ ክርስቲያኖች ቤት በመሄድ የወንጌልን ቃል ሰሙና አመኑ ። ካመኑትም ውስጥ ከአቾሎ ጨንቻ ተራራ አጠገብ ይኖሩ የነበሩት አቶ ግምበ ነበሩ ። በገሙ ጸሎት ቤት ሲሠራ በመጀመሪያ በእርሳቸው ቤት አጠገብ ነበር ።

በኩሎ ከንታ በአንድ አርበኛ የሚመራ ጦር ነበር ። ጣሊያኖችም የኦሞ ወንዝ እስኪመልሳቸው ድረስ ወታደር በመላክ ለመማረክ ሞከሩ ። በምሽት ጣሊያኖች ወታደሮች ምሽጋቸውን ጥለው መሄድ ስለሌለባቸው ሊጎዷቸው አልቻሉም ። ይሁን እንጂ ብዙዎቹ የኩሎ ሕዝብ በጣሊያን ተባርረው ከኦሞ ወንዝ ማዶ በጥምባሮ በጥገኝነት ኖረዋል ። በወላሞ የነበሩትም አማኞች ይህንን ሲሰሙ አቶ ኢምበሊንና ሌሎችን ሰዎች ወንጌልን እንዲሰብኩላቸው ላኳቸው ። አንዳንዶች ሌሎችን ሰዎች ከመ

ኑትም ውስጥ የጥምባሮ ተወላጅ የነበረው አቶ አልዳዳ ሲሆን የኩሎ ሕዝብ ወደ አገራቸው ሲመለሱ አብረዋቸው ሄደ ።

በከንባታ አቶ አባ ጎሌ ሌሎቹም ክርስቲያኖች ከሥፍራ ወደ ሥፍራ እየተዘዋወሩ ሲያስተምሩ ጣሊያኖች ሊያቆሟቸው ሞከሩ ። ይሁን እንጂ የጌታን መንፈስ ሊያቆም የሚችል ማንም አልነበረም ። በወላሞ ብዙ አገልጋዮች የነበሩት ዳና ማጃ ክርስቶስን ተቀበለ ። ጸሎት ቤትም ተቋቋመ ።

በመጨረሻም ጣሊያኖች ከኢትዮጵያ ወጡ ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም እ. ኤ. አ. ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. አዲስ አበባ ገቡ ። የቀድሞዎቹ ሚስዮናውያን ተመልሰው ሲመጡ የአማኞቹ ቁጥር እየጨመረ ሄዶ ፲ ሺህ ደርሶ አገኙት ።

<u>ጥያቄዎች</u>

1. በኢትዮጵያ ስንት የቀይ መስቀል ድርጅቶች ነበሩ ? ______
2. በጠላት ዘመን በኢትዮጵያ የነበሩት አማኞች ያደረጉትን ሚስዮናውያኖቹ ለምን ማወቅ አልቻሉም ? ______
3. በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. በጠላት ወረራ ምክንያት ሚስዮናውያኖቹ አገሪቱን ለቀው ሲወጡ አምነው የተጠመቁት ክርስቲያኖች ቁጥር ስንት ነበር ?

   ______
4. ሚስዮናውያኖቹ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ የአማኞች ቁጥር ስንት ደረሰ ? ______
5. በጥምባሮ ጥገኛ ለነበሩት ሰዎች ወንጌልን ለመስበክ ከወላሞ ቤተ ክርስቲያን የተላከው ሰው ስሙ ማን ነው ? ______
6. ለመጀመሪያ ጊዜ ከተጠመቁት ሰዎች የአንዱን ስም ብቻ ጻፍ ።

   ______
7. ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ የገቡበትን ቀንና ዓ. ም. ጻፍ ። ______

<u>የኤስ አይ ኤም ሥራ በኢትዮጵያ ።</u>

የሚከተለውን ክፍል ካነበብህ በኋላ በመጨረሻ ለሚገኙት ጥያቄዎች መልስ ስጥ ።

በኢትዮጵያ ከ፬፻፺ የሚበልጡ የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን ሲኖሩ አንዳንዶቹም ሚስዮናውያን መላ የሕይወታቸውን ዘመን በአገሪቱ አሳልፈዋል ። በወላሞ ይሠሩ የነበሩት ሚስተር አመንና ሚስስ አመን እንዲሁም ሚስ በርግስተን አርባ ዓመታት ወንጌልን በማስተማር አገልግለዋል ። ሚስተር ኬን በ፲፱፻፳፭ ዓ. ም. ወደ አዲስ አበባ መጥተው እስከ አሁን ድረስ በአገልግሎት ላይ ይገኛሉ ።

ጸሎት ቤቶች ፡— ለኢትዮጵያ የሰጡት ጥቅም ምንድር ነው ? አዎን ከዚህ በፊት ወንጌልን ሰምተው ለማያውቁት ሰዎች አሰምተዋል ። ፍሬምናጦስና አዴስየስ በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክርስትናን እምነት ካስተዋወቁ ወዲህ ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት በመባል ታውቃለች ። ይሁን እንጂ እስከ ዛሬ ድረስ እንኳን ስለ ክርስቶስ ያልሰሙ ሰዎች አሉ ። በኤስ አይ ኤም ሺ.ህ ፺፱ ጸሎት ቤቶች ፻፳ ሺህ አምነው የተጠመቁ ሰዎች ሲኖሩ በየሰንበቱ ለጸሎት የሚሰበሰቡትና የቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑት ቁጥራቸው ብዙ ነው ።

ትምህርት ቤቶች ፡— ትምህርት ቤት መክፈትና ትምህርት መስጠት የሚስዮናውያን ተግባር እንደሆነ ሁሉ ኤስ አይ ኤም ደግሞ በአዲስ አበባ አንድ ትልቅ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲያቋቁም ፴፰ ከስድስት ሺህ የሚበልጡ ተማሪዎችን የያዘ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉት ። በዱራሜ ሶዶና ዲላ ስምንት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ ። በሶዶ አንድ የመርሃ ዕውራን ትምህርት ቤት ሲገኝ በጠቅላላው ፯ ሺህ ፭፻ ተማሪዎች በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ ።

በዚህ ብቻ ሳይወሰን ኤስ አይ ኤም የማኅበር ጸሎት ቤቶች የየራሳቸው መሠረተ ትምህርት ቤቶች እንዲኖራቸው ረድተዋል ። ጸሎት ቤቱ የአንደኛን ክፍል ትምህርት ማስተማር ሲችል ሚስዮኑ ደግሞ ሁለተኛ ሌላ ከፍተኛ ክፍል ይከፍትና በማስተማር ደረጃውን ከፍ ያደርጋል ። ዛሬ ጸሎት ቤቶቹ ፴፪ መሠረተ ትምህርት ቤቶች ሲኖሯቸው ፴ ሺ.ህ የሚሆኑ ተማሪዎች አላቸው ።

ከዚህ ሌላ አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች አሉ ። የጸሎት ቤት ሐላፊ ለሚሆነው ሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ማግኘት ጠቃሚ ነው ። የኤስ አይ ኤም የማኅበር ትምህርት ቤቶች እንዳሉ ሁሉ የኤስ አይ ኤምና የማኅበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ደግሞ አሉ ። ፳ የሚሆኑ የማኅበሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ ፻፵ የኤስ አይ ኤም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች አገልግሎታቸውን በማበርከት ላይ ናቸው ። በጠቅላላው ፫ ሺ.ህ የሚሆኑ ወንዶችና ሴቶች መጽሐፍ ቅዱስን ሲያጠኑ ፣ ጅማ በሚገኘው ምላተ ጸጋ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በከፍተኛ ደረጃ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በመስጠት ለወደፊት የጸሎት ቤት መሪዎችንና መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችን ያዘጋጃል ።

ሕክምና ፡— ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሄደው እንዲያስተምሩ ብቻ ሳይሆን በሽተኞችንም ደግሞ እንዲፈውሱ አዟቸዋል ። ዶክተር ላምቤ በመጀመሪያ መጥቶ ይህንን ሥራ እንደጀመረ ብዙዎች በዚህ የሥራ መስክ በመሠማራት ብዙ በረከት ሰጥተዋል ። ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ድውያንን ፈውሱ ለምጻሞችን አንጹ (ማቴ. ፲ ፡ ፰) እንዳለ ሁሉ ኤስ አይ ኤም በሥጋ ደዌ ለተያዙ ሰዎች ሁለት ሆስፒታሎች ሲኖሩት ሌላም ሆስፒታሎችና ፳፭ ክሊኒኮች አቋቁሞአል ። በወላሞ ሶዶ ድሬሰሮችን የማሰልጠኛ ት / ቤት አለው ።

ፊደል ማስተማር ፦ አገሪቱ የሥልጣኔ ሥራ እንዲበራላትና ሁሉም ማንበብና መጻፍ እንዲችል ፣ ከመጻሕፍትና ከጋዜጣ የሚገኘውን ጥቅም እንዲያውቁ ፣ ስለ ጤና አጠባበቅ ስለ እርሻ ዘዴ እንዲረዱ ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል አንብበው እንዲጠቀሙ ፤ ለአዲስ አንባብያን የሚሆኑ መልመጃዎች በሥነ ጽሑፍ ድርጅታችን በየጊዜው እየተዘጋጁ ይወጣሉ ። አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑት ወገኖች ቱፕና ለማስተማር የሚረዱ ሥዕላዊ መግለጫዎች ተዘጋጅተዋል ። ፳፻ ሺህ ሥዕላዊ ፊደል በመሸጣቸው ብዙ ሰዎች እንደተማሩ መገመት እንችላለን ።

ሥነ ጽሑፍ ፦ ሰዎች የፊደላቱን ዘር ለይተው ካወቁ በኋላ በሚያነቡት ነገር እንዲጠቀሙ የቃለ ሕይወት ሥነ ጽሑፍ ድርጅት ተቋቋመ ። በዚህ ድርጅት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ታትመዋል ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ጂዖግራፊ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ፣ የአፍሪካ ጂዖግራፊና ሚስዮናውያኖቹም አማርኛን ለመማር የሚረዳቸው ትልቅ የአማርኛን ሰዋስው የያዘ መጽሐፍ ታትሞ ወጥቶአል ።

እ. ኤ. አ. ከ፲፱፻፳፯ ዓ. ም. ጀምሮ ብዙ ሚስዮናውያን በኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ አንዳንዶች ሕይወታቸውን አሳልፈዋል ። ሚስ ቤሲ ማርቲን በኢትዮጵያ ውስጥ ከሞቱት ሚስዮናውያን የመጀመሪያይቱ ሲሆኑ ሚስተር ክሊፍ ምቸል እና ሚስተር ቶም ዴቨርስ በሽፍታ ተገድለዋል ። በበሽታ የሞቱ የሚስዮናውያን ልጆችም በአንዳንድ የሚስዮን ጣቢያ መቃብራቸው ይታወቃል ።

ሚስዮናውያኖቹ በኢትዮጵያ በቆዩበት ጊዜ ብዙ ተግባሮችን አከናውነዋል ። በሚቀጥለው ትምህርታችን ኤስ አይ ኤም ገንዘቡን እንዴት እንደሚያገኝና ሚስዮናውያኖቹ ከየት እንደመጡ እናነባለን ።

ጥያቄዎች

1. ስንት የሚሆኑ ጸሎት ቤቶች ከኤስ አይ ኤም ጋር ባልደረባ በመሆን ይሠራሉ ? __________

2. በኤስ አይ ኤም የሚመሩትን ሦስት ዓይነት ትምህርት ቤቶች ጻፍ ።
   ሀ. __________
   ለ. __________
   ሐ. __________

3. በጂማ ምላተ ጸጋ መጽሐፍ ቅዱስ ት / ቤት ስንት ተማሪዎች አሉ ?
   __________

4. ማንበብና መጻፍ መቻል ሊረዳ የሚችልበትን ሦስት መንገዶች ጻፍ ።
   ሀ. __________
   ለ. __________
   ሐ. __________

## የኤስ አይ ኤም የሥራ አመራር ዘዴ ።

ይህንን ክፍል በጥንቃቄ ከነበብህ በኋላ በመጨረሻ ያሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክር ።

ኤስ አይ ኤም ፪፻፶ የሚሆኑ የወንጌል አስተማሪዎች በኢትዮጵያ ሲኖሩት በናይጄሪያ ፣ ላይቤሪያ ፣ ጋና ፣ ዳሆሚ ፣ አፐር ቮልታ ፣ የናይጀሪያ ሪፓብሊክ ፣ አይቮሪ ኮስት ፣ ሱዳንና ሶማልያ ናቸው ። በጠቅላላው ሺህ ፫፻ የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን አሉ ። እንደምናውቀው ሁሉ ሚስዮኑ ሆስፒታል ፣ ትምህርት ቤቶችና የራዲዮ ጣቢያ አለው ። ሚስዮናውያኖቹ የሚመጡት ከየት ነው ። ለየትምህርት ቤቱ ማውሪያ የሚሆነው ገንዘብ ሁሉ ከየት ይመጣል ?

ሚስዮናውያን ፦ ሚስዮናውያኖቹ የመጡት ከየት ነው ? ሚስዮናውያኖቹ የመጡት ከአሜሪካ ፣ ከናዳ ፣ አውስትራሊያ ፣ ኒውዚላንድ ፣ ግሬት ብሪትን ፣ ጀርመን ፣ ፈረንሳይ ፣ ስዊዘርላንድ ነው ። በየክፍለ አገሩ መማክርት ስለአሉ የሚስዮኑ ባልደረባ ለመሆን የሚሹትን ሁሉ መምሪያ ይሰጣሉ ።

ከእነዚህ ሁሉ በበላይነት የሚሠራ አጠቃላይ መማክርት ሲኖር የሚሰበሰቡትም በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ ነው ። በዚህም ስብሰባ ከምሥራቅና ከምዕራብ አፍሪካና ከሌላም ሥፍራ የሚገኙት እንደራሴዎች ይሰበሰባሉ ።

ከዚህ በስተቀር ሁለት መማክርት በምሥራቅና ምዕራብ አፍሪካ ሲገኙ እነርሱ በየስድስት ወሩ በመሰብሰብ ስለሚስዮኑ የሥራ አመራር አቅድ ያወጣሉ ። ሚስዮናውያኖቹ ሥራ መሥራት በሚገባቸው ቦታ ይደለደላሉ ። ሆስፒታሉ የት መሠራት እንዳለበት ትምህርት ቤት የትና መቼ መከፈት እንዳለበት ያስባሉ ። ይሁን እንጂ ሚስዮናውያኖቹ ይህን ሁሉ ሥራ ሲያከናውኑ የሚከፍላቸው ማን ነው ? ምዕመናኑ የኤስ አይ ኤም ባልደረባ ሲሆኑ በየወሩ የተወሰነ ደመወዝ መቀበልን ፈጽሞ ይተዋሉ ። ብዙዎቹ በአገራቸው የትምህርት ቤት ዲሬክተር ፣ የሆስፒታል አስተዳዳሪ ፣ የቢሮ ሠራተኛ በነበሩ ጊዜ ጥሩ ደመወዝ ቢኖራቸውም ሚስዮናዊ ሆነው ወደ ሌላ አገር ለመሄድ ሲያስቡ ክርስቲያን ጓደኛ በመፈለግ እንዲረዱአቸው ያደርጋሉ ። እንዲህ ከሆነ ሀብታም ጓደኞች ያሉት ብዙ ሲያገኝ ጥቂት ድሀ ጓደኞች ያሉት ደግሞ ጥቂት በማግኘት የሚጎዳ ይመስላል ። ይሁን እንጂ ሚስዮናውያኖቹ የተገኘውን እኩል በመካፈል ለመኖር ተስማምተዋል ። የሚስዮኑ የበላይ ተጠባባቂ የሆነ ሰውና ተራው ሚስዮናዊ እኩል ደመወዝ አላቸው እንጂ የሚበላለጥ አይደለም ።

የትምህርት ቤት ዲሬክተሮች የሆኑ ሰዎች ብዙ ገንዘብ እንደሚያገኙ የታወቀ ቢሆንም ሚስዮናዊ ሰው ዲሬክተር ሆነ የጣቢያ ሐላፊ የበለጠ ገንዘብ አያገኝም ። ሚስዮናውያን በየወሩ ስንት እንደሚያገኙ የተረጋገጠ አይደለም ። ቢሆንም በየወሩ ፪፻ ብር ያህል አያጡም ። ከዚህ ሌላ ሰውዬው ያገባ ከሆነ ለባለቤቱና ለልጆቹም ለመኖሪያ የሚሆን ገንዘብ ይሰጠዋል ።

ትምህርተ ሃይማኖት ፡— በኤስ አይ ኤም ውስጥ የሚሠሩት ሚስዮናውያን የሚመጡት ከተለያየ አገርና ጸሎት ቤት ነው ። አንዳንዶቹ ባፕቲስት ሌሎች ሜቶዲስት ናቸው ። ሆኖም በአንድ ዓይነት መሠረታዊ ሃይማኖት በመስማማት ይሠራሉ ። መሠረተ ሃይማኖታቸውም እንደሚከተለው ነው ። ደኅንነት የሚገኘው በመስቀል ላይ በሞተው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው ።

እግዚአብሔር አንድም ሦስትም ነው ። ይኸውም እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በመባል ይታወቃል ።

መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ በተመሩ ሰዎች እንደተጻፈና የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን ።

መንግሥተ ሰማያት ለአማኞች እንደተዘጋጀና የማያምኑትን ገሃነመ እሳት እንደሚጠብቃቸው እናምናለን ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ለመውሰድ እንደሚመጣ እናምናለን ።

አንዳንድ ሚስዮናውያን ስለ ዲያቆናት ተግባርና ስለ መንፈሳዊ አገልግሎት ልዩ ልዩ ሥርዓት ቢከተሉም መሠረታዊ በሆነ ዋና ነገር ይስማማሉ እንጂ ጥቃቅን በሆኑት ነገሮች በመከራከር ጊዜያቸውን አያሳልፉም ።

ሕንፃና የማሠሪያው ገንዘብ ፡ ለሕንፃ ማሠሪያ የሚሆን ገንዘብ ከየት ይመጣል ? የአስተማሪዎች ደመወዝ ከየት ይከፈላል ? መልሱ የሚስዮናውያኖቹ ጓደኞች ናቸው ። የሚስዮኑ ኮሚቴ (መማክርት) አዲስ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ መክፈት ቢያስፈልግ ለየሚስዮናውያኖቹ ዘመዶችና ረዳቶች ጉዳዩ ይደርስና ገንዘብ እንደላኩ ትምህርት ቤት ይሠራል ።

ለመምህራን የሚሆነው ደመወዝ ከየትምህርት ቤቱ ገቢ ይሆናል ። አንዳንድ ሰዎች ሚስዮናውያን የሚከፈሉት በአሜሪካን ወይም በእንግሊዝ ወይም በኢትዮጵያ መንግሥት የሚመስላቸው ቢኖሩም ሚስዮናውያን በአገራቸው ጸሎት ቤት በመላክ በጓደኞቻቸውና በዘመዶቻቸው የሚረዱ መሆናቸውን እንዲያውቁ እንወዳለን ።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ሚስዮናውያን ሀብታም ይመስላሉ ። አንድ ሚስዮናዊ መኪና ቢኖረው የላከው የጸሎት ቤት እንደገዛለት እንወቅ ፣ ለቤንዚንም የሚሆነውን የሚስዮናዊው ጓደኞች ይከፍላሉ ፤ ሚስዮናዊ ዘመዶቹን ለመጠየቅ ሲመለስ ጓደኞቹ ልብስ ይገዙለታል ። ደግሞ የላከው ጸሎት ቤት ወደ አፍሪካ ሲመለስ የሚያስፈልገውን ዕቃ ይገዛለታል ። ብዙዎቹ ሚስዮናውያን የግል የሆነ ቤት ወይም መሬት የላቸውም ። የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን መናኝ ናቸው ።

ጥያቄዎች

1. በኤስ አይ ኤም ስንት ሚስዮናውያን አሉ ? ____________________
2. ኤስ አይ ኤም አጠቃላይ መማክርት አለው ? ____________________
3. የኤስ አይ ኤም ሚሰዮናዊ ደመወዙን እንዴት እንደሚያገኝ ግለጽ ።

____________________________________________

4. ኤስ አይ ኤም ከሚያምንባቸው መሠረተ ሃይማኖት ሁለቱን ብቻ ግለጽ ።

ሀ. ____________________________________________

ለ. ____________________________________________

5. ፊልጵስዩስ ፪ ፥ ፮ — ፲፩ ከነበብህ በኋላ ከፍ ያለው የእግዚአብሔር የመጥራቱ ዋጋ ምን ይመስልሃል ? ____________________

____________________________________________